www.chilot.me



፯/ በከተማው ወይም ባገር ውስጥ የስልኩ መሥመር በሚዘረጋበት ጊዜ በማናቸውም ቦታና ርስት የሥልኩን መሥመር ለመዘርጋት (ለመሳብ) ቦርድ ሥልጣን አለው ። እንዲሁም በሕንፃዎችና በቤቶች ላይ መስቀያና ወገል ለማድረግ ግድ ሲሆንበት የቤቶቹን ሁናቴ ሳያበላሽ ሊተከል ይችላል ።

፰/ ቦርዱ የስልክ መሥመር ሠራተኞችና ጠባቂዎች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የማናቸውንም ሰው መብትና ጥቅም ሳያበላሹ በማናቸውም ቦታ እንዲተላለፉ ተፈቅዶላቸዋል ።

፱/ ማናቸውም ሰው የሚኒስቴሩን ሥራ የሚያዘገይ ፣ የሚያሰናክልና የሚያበላሽ ወይም በ፰ኛው፣ በ፯ኛውና በ፰ኛው ቁጥር የተከለከለውን የሚሠራ ከጥፋተኛ ተቆጥሮ በተመለከረበት ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

በ፬/፱ (፲፱፻፹፯) አ. ፫፻፮ ሥን. ሐ. አን. ፱ (ሀ) ፤ ፲፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ ተሻሻለ ፤ በወ. መ. ሕ. ፲፯/ በተ. የ. ፩ (፲፱፻፶፱) አን. ፫፻፶፩ ፣ ፫፻፷፬ ፣ ፯፻፵ ፣ ፯፻፶፰ (በዚህ እንቀጽ ለሚያስቀጡት ተግባሮች ቅጣትን በመደንገግና እንደዚሁም የዚህን እንቀጽ የቅጣት ድንጋጌዎች በግልጽ ሳይነገር በመሻር) በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.chilot.me



# ክፍል ፳፫

# ንግድና እንዱስትሪ

## ሀ/ የንግድ ሕግ (በጠቅላላ)

፲፱/፫ (፲፱፻፶፪) አ. ፻፷፮ *

የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የንግድ ሕግ. አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

በንጉሠ ነገሥት ግዛታችን በንግድ ረገድ በተደረገው እርምጃ አዲስ የንግድ ሕግ ማወጅ አስፈላጊ ሆኖ ስለአገኘነው ፤

በእኛ መሪነት ይህ የንግድ ሕግ እንዲዘጋጅ አድርገን የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ቤቶቻችን ስለተቀበሉት ፤

በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፴፬ኛውና በ፹፰ኛው አንቀጽ የተጻፈውን ተመልክተን ፤ የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶቻችን የመከሩበትን አይተን ፤ ቀጥሎ ያለውን አውጀናል ።

፩/ ይህ ሕግ «የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የንግድ ሕግ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ልዩ መጽሐፍ ሆኖ በተለይ በወጣው በቁጥር ፫/ ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. ነጋሪት ጋዜጣ ውስጥ የታተመው ይህ ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የንግድ ሕግ ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

፫/ በሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ስለ ኪሣራና ስለንግድ ማኅበር የወጣው አዋጅ ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጀምሮ በዚህ ተሽሮአል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም.

---

የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

የንግድ ሕግ ፤ ፲፱/በተ. የ. ፫ (፲፱፻፶፪) አ. ፻፷፮ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልተጨመረም ።

www.chilot.me



፫/ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ የሚሠራው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ያቋቋመውን የዋናውን ጽሕፈት ቤት አድራሻ ፤

፬/ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ የሚሠራው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያካሂደውን ዋና ሥራ ፤

፭/ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ የሚሠራው ሰው በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያዋለውን ካፒታል (ዋና ገንዘብ) ልክ ፤

ለ/ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ የሚሠራው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ከዋለው ካፒታል (ዋና ገንዘብ) በያንዳንዱ ፩ሺህ (አንድ ሺህ) የኢትዮጵያ ብር አንድ ብር መክፈል ፤ ስለሆነ ግን ይህ የሚከፈለው ገንዘብ በምንም አኳኋን ከአሥር የኢትዮጵያ ብር ማነስ የለበትም ።

፪/ የመጀመሪያ ወይም ተሻሽሎ የተሰጠ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ፤ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ የሚሠራውን ሰው እውነተኛ ሁኔታ የማይገልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ከዚህ በላይ በተዘረዘረው የመጀመሪያ መግለጫ ዓይነት ተሻሽሎ የተዘጋጀ ሌላ መግለጫ ማቅረብ የግድ ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በመጀመሪያ ፲፮/፬ (፲፱፻፶፱) ድ. ፳፮ ሆኖ ወጣ ፤ በ፴፩/፫ (፲፱፻፷፬) አ. ፪፻፱ አን. ፪ ፣ ፳፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፪ ተሻሻለ ።

አንቀጽ ፳ ።

ጠቅላላ ።

፩/ ማናቸውም ኩባንያ ወይም ለብቻው የንግድ ወይም የእንዱስትሪ ሥራ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ማናቸውንም ኮንትራት ከማድረጉ በፊት ፤ በዚህ አዋጅ እንደተወሰነው አስቀድሞ በንግድና በእንዱስትሪ ሚኒስቴር ካልተመዘገበ በቀር ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ባደረገው በማናቸውም ኮንትራት ላይ ማናቸውንም ውሳኔ ለማድረግ መብት አይኖረውም ። ይህ ግዴታ በኩባንያው ወይም የንግድ ወይም የእንዱስትሪ ሥራ በሚሠራው ሰው ወራሽ ፤ የዚሁ ወራሽ ወይም የኩባንያው ወይም ለብቻው የንግድ ወይም የእንዱስትሪ ሥራ የሚሠራው ሰው መብት ይገባኛል በሚል በማናቸውም ሰው ላይ የጸና ይሆናል ።

፪/ ማናቸውም ኩባንያ ወይም ለብቻው የንግድን ወይም የእንዱስትሪን ሥራ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ፤

ሀ/ በንግድና በእንዱስትሪ ሚኒስቴር ሳይመዘገብ ማናቸውንም ሥራ ሲሠራ ቢገኝ ወይም ፤

ለ/ ተመዝግቦ ሳለ የተመዘገበበት ያልሆነ ሥራ ሲሠራ ቢገኝ አጥፊ ሆኖ ይቆጠራል ።

መብቱ በሚፈቅድለት ፍርድ ቤትም በተመሰከረበት ጊዜ የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ። ከዚህም በላይ ፍርድ ቤቱ ይህን ሰው ወይም ኩባንያ ይህን ያልተፈቀደውን ሥራ እንዲያቆም ለማዘዝ ይችላል ። ይህም ሁኔታ የንግድና የእንዱስትሪ ን ሚኒስቴር ኋላ ይህን ሰው ወይም ኩባንያ ሥራ እንዲሠራ ፈቃድ እንዳይሰጠው አይከለክለውም ።

www.chilot.me



፪/ ትርጉም ፤

በዚህ አዋጅ ውስጥ በሌላ አኳኋን በአነባበቡ ካልተለወጠ በቀር ፤ ከዚህ በታች ያሉት አርእስቶች ትርጉም በየግርጌአቸው እንደተመለከተው ነው ፤

ሀ/ «ከብት» ማለት የቀንድ ከብት ፣ በግ ፣ ፍየል ፣ የጋማ ከብት ፣ ግመል ፣ አሳማ ፣ ዶሮና እንደዚሁም ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም «ከብት» በሚል መደብ ውስጥ የሚጨመሩ መሆናቸውን የእርሻ ሚኒስትራችን በማስታወቂያ የሚያወጣቸው ማናቸውም ሌላ ከብቶች ቁጥር ነው ፤

ለ/ «የከብት በሽታ» ማለት የቀንድ ከብት የደስታ በሽታ ፤ የአፍና የእግር በሽታ ፣ የሳንባ በሽታ ፤ የአባ ሰንጋ ፤ አባ ጉርባ ፤ የቀንድ ከብት ሳንባ በሽታ ፤ የፈረስ የዕጢ በሽታ ፤ የውሻ እብደት በሽታ ፤ ትኩሳት ፣ የበግ ኩፍኝ ፣ የፍየል እከክ ፤ የአሳማ ትኩሳት ፣ የአሳማ ተላላፊ በሽታ ፤ እከክ ፤ የበግና የፍየል የሆድ ትል በሽታ ፣ እንዲሁም ስለዚሁ አዋጅ አፈጻጸም ፤ በሽታ በሚል መደብ ውስጥ የሚጨመሩ መሆናቸውን የእርሻ ሚኒስትራችን በማስታወቂያ የሚያወጣቸው ማናቸውም ሌሎች የሚራቡና ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች ቁጥር ናቸው ፤

ሐ/ «በድን» ማለት ከብት በድን ሲሆን የበድኑን ክፍልና ሥጋ ፣ አጥንቶችን ፤ ሌጦን ፤ ቆዳን ፤ ሸሆናዎችን ፤ ቀንዶችን ፣ ጠጉርን ፤ ሆድ ዕቃውን ወይም የከብቱን ሌላውን ክፍል ይጨምራል ፤

መ/ «ጠባቂ» ማለት የማናቸውም የከብቶቹ ሙሉ ባለንብረት የሆነ ባለቤት ወይም በሽርክና የሆነ ሰው ወይም ከብቱን ለመጠበቅ አላፊነት ያለውን ሰው ይጨምራል ፤

ሠ/ «የከብት ሕክምና ዲሬክተር» ማለት ይህንን ሥራ ለመምራት የተሾመ ማናቸውም የእርሻ ሚኒስቴር ሹም ነው ፤

ረ/ «መኖ» ማለት ድርቆሽና ለከብት ምግብ የሚሆን እህል ወይም ሌላ ማናቸውም ለከብት የሚሆን ምግብ ነው ፤

ሰ/ «ጉዝጓዝ» ማለት ሣር ወይም ሌላ ለከብቶች መኝታ ወይም ለሌላ አገልግሎት ጥቅም የሚውል ነው ፤

ሸ/ «የከብት ጤና መርማሪ» ማለት የከብት ከታቢ ወይም ይህንኑ ሥራ እንዲሠራ የእርሻ ሚኒስትራችን በማስታወቂያ የሚሾመው ማናቸውም ሰው ነው ፤

ቀ/ «የከብት ሐኪም» ማለት በከብት ሕክምና ትምህርት ምስክር ያገኘና የመቅደድ ችሎታ ያለው በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ እንዲሠራ ሥልጣን የተሰጠው የከብት ሐኪም ነው ።

www.chilot.me



## ፪/ የእንስሳ በሽታዎችን መራባት ለመመርመር የሚደረግ አፈጻጸም ።

### ፩/ በታመሙ ከብቶች ላይ ጠባቂው የሚፈጽመው ተግባር ፤

በበሽታ የተነደፈ ወይም በበሽታ ተነድፎአል ተብሎ የተጠረጠረ እንስሳ ቢኖርና ይህንኑ ጠባቂው ሲረዳ ፤

ሀ/ ለባለቤቱም ወይም ለመንደሩ ሹም ወይም በአቅራቢያው ለሚገኘው አውራጃ ፤ ወረዳ ፤ ወይም ምክትል ወረዳ ገዥ ማስታወቅ አለበት ። ከብቱ በባሕር የሚጓዝ የሆነ እንደሆነ ፤ ወደቡ ላይ እንደደረሰ ለጉምሩክ ባለሥልጣኖች ያስታውቃል ። ጉዞው በምድር የሆነ እንደሆነ ግን በአቅራቢያው ለሚገኘው ፖሊስ ያስታውቃል ።

ለ/ እነዚህንም ከብቶች በበሽታ ካልተነደፉት ወይም በሕመም ካልተጠረጠሩ ከብቶች ለይቶ መያዝ አለበት ።

### ፪/ የከብት በሽታ መግባቱን ስለማስታወቅ ፤

ከብቶች የሚቃወም በሽታ በግዛቱ ውስጥ መግባቱን ሲያረጋግጥ የአውራጃው ገዥ ፤ የወረዳው ገዥና የምክትል ወረዳ ገዥ በግዛቱ ውስጥ የሚገኙ ባላባቶችና የከብት ጠባቂዎች ሁሉ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ማድረግ አለባቸው ።

### ፫/ በሽታ መኖሩን ለከብት ሐኪም ስለማስታወቅ ፤

ማናቸውም የመንደር ሹም ፤ ባላባት ፤ የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣን ፤ የአውራጃ ፤ ወረዳና የምክትል ወረዳ ገዥ በበሽታ የተነደፈ ወይም ተነድፎአል ተብሎ የተጠረጠረ ከብት መኖሩን ሲሰማ በአቅራቢያው ለሚገኘው የከብት ሐኪም ወዲያውኑ ያስታውቃል ። የከብት ሐኪሚ የተባለው በሽታ መኖሩንና ዓይነቱንም ጭምር ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ትእዛዝ እርምጃ በማድረግ በሽታው መኖሩን ሲያረጋግጥ ለከብት ሕክምና ዲሬክተር ወዲያውኑ ያመለክታል ።

### ፬/ በበሽታ የተነደፉት ከብቶች ስለማረድ ፤

ሀ/ በአባ ሰንጋ ፤ በከብት ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ፤ በውሻ በሽታ የተነደፈውን ማናቸውንም ከብትና በፈረስ ዕጢ በሽታ የተነደፈውን የጋማ ከብት እንዲገደል ለማድረግ ፤

ለ/ ከላይ በተነገረው በሽታ ተነድፎአል ተብሎ የተጠረጠረውን ማናቸውንም ከብት ወይም ከታመሙ እንስሳት ጋር ግንኙነት የነበረውንና ለበሽታ መራባት ወይም መተላለፍ ምክንያት ሊሆን የሚችለውን መታመሙ እስኪታወቅ ለተወሰነ ጊዜ በተለይ ቦታ ለብቻው እንዲጠበቅ ለማድረግ የከብት ሐኪም ለማዘዝ ይችላል ።

## ፫/ የሹማምንቶች ሥልጣን ።

### ፭/ በበሽታ የሞቱ እንስሶችን በድን ስለማስወገድ ፤

በተላላፊ በሽታዎች ምክንያት ከብት የሞተ እንደሆነ በድኑና ይተኛበት የነበረውን ጉዝጓዝ ፤ እበቱን ወይም ለምግቡ ቀርቦለት የነበረውን ርካሽ ሣር ስለመቅበር ወይም ስለ ማቃጠል ወይም ስለማስወገድ ማናቸውም የአውራጃ ፤ የወረዳ ፤ የምክትል ወረዳ ገዥ ፤ የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣን ወይም የከብት ሐኪም ወይም የከብት ጤና መርማሪ ትእዛዝ መስጠት ይችላል ።

www.chilot.me



፱/ **ስለምርመራ ፣ ስለክትባትና ስለመድኃኒት መርጨት ሥልጣን ፤**

ማናቸውም የከብት ሐኪም በማናቸውም ጊዜ ከብት እንዲመረመር ፣ እንዲከተብ ፣ መድኃኒት እንዲረጭ ፣ እንዲነከርና ፣ እንዲታጠብ ፤ ወይም በሽታው እንዳይተላለፍ አስፈላጊ መስሎ የታየው እንደሆነ ለተወሰነ ጊዜ በተገለለ ቦታ ለምርመራ ተለይቶ እንዲጠበቅ ማድረግ ይችላል ።

፲/ **ምርመራ የማድረግ ሥልጣን ፤**

ማናቸውም የከብት ሐኪም በሽታ በተጠረጠረበት ቀበሌ ለምርመራና በሽታውን ለማወቅ ከማናቸውም ከብት ላይ የደም ጠብታ ለመውሰድ ወይም አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዓይነት ምርመራ ለማድረግ ይችላል ።

፲፩/ **የከብቶች ትርዕይት ወይም ስብሰባ ፣ ወይም እርድ ፤ ይህንንም የመሳሰለውን የመከልከል ሥልጣን ፤**

የከብት ሕክምና ዲሬክተር የከብት በሽታ እንዳይስፋፋ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው በማናቸውም ሥፍራ የከብት ትርዕይት እንዳይደረግ ፣ በገበያም ሆነ ወይም በግለኛ ሥፍራ ላይ ለሽያጭ እንዳይሰበሰብ ፣ ለምግብ የሚሆን የቀንድ ከብትም እንዳይታረድና ሥጋው ወይም የከብቱ ማናቸውም አካል እንዳይሸጥ ለማድረግ ይችላል ።

፲፪/ **ወደሚመረመር ሥፍራ የመግባት ሥልጣን ፤**

ሀ/ ማናቸውም የአውራጃ ፣ የወረዳ ወይም የምክትል ወረዳ ገዥ ፣ የማዘጋጃ ቤት ባለ ሥልጣን ወይም የከብት ሐኪም ወይም ጤና መርማሪ ከብቶችና የከብት በድን ፣ ጉዝጓዝ ፣ እበት ወይም የከብት ምግብ አለበት ተብሎ ወደ ተጠረጠረበት ወደ ማናቸውም መሬት ፣ ሕንፃ ፣ ዛኒጋባ ፣ ሥፍራ ወይም ተሽከርካሪ መኪና ውስጥ ለመግባትና በውስጡ ያለው ከብት በበሽታ የተነደፈ መሆኑን ፣ እንደዚሁም በዚህ አዋጅ መሠረት ስለንጽሕናና ስለመድኃኒት መርጨት ጉዳይ የተሰጡትን ደንቦችና ትእዛዞች በትክክል መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ መመርመር ይችላል ።

ለ/ የማናቸውም እንስሳ በድን ፣ ጉዝጓዝ ፣ እበት ወይም መኖ ጠባቂ በአንቀጽ ፲፪ በፓራግራፍ (ሀ) በተመለከተው መሠረት ሲጠየቅ አቅርቦ ማስመርመር አለበት ።

፲፫/ **አስፈላጊ የሆኑትን ሥራዎች የማስፈጸም ሥልጣን ፤**

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣው ደንብ ወይም ትእዛዝ ማናቸውንም ተግባር ወይም ሥራ እንዲያደርግ ተጠይቆ ፣ ሳይፈጸም የቀረ እንደሆነ የወረዳው ገዥ ወይም የከብት ሐኪሙ በሰውየው ኪሣራ ሥራው እንዲፈጸም ለማድረግ ይችላል ።

፬/ **በሽታ ያለባቸው ሥፍራዎች ።**

፲፬/ **በሽታ ያለባቸውን ሥፍራዎች በበሽታ ተነድፈዋል ብሎ የማስታወቅ ሥልጣን ፤**

የእርሻ ሚኒስትራችን ስለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ውስጥ የከብት በሽታ አለበት የተባለውን ማናቸውንም ሥፍራ እየለየ በማናቸውም ጊዜ በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ሊገልጽ ይችላል ።

www.chilot.me



መ/ የከብት ሐኪም ወይም የከብት ጤና መርማሪ በዚያው ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም ከብት ተስማሚ መስሎ በታየው ዓይነት ምልክት እንዲደረግባቸው ሊያዝዝ ይችላል ።

ሠ/ በተላላፊ በሽታ ታመው የሞቱት ከብቶች በድን አንድ ሜትር ተኩል ጥልቀት ባለው ጉድጓድ ውስጥ በባለ ከብቱ ኪሣራ መቀበር ወይም መቃጠል አለበት ።

## ፩/ ደንቦች ።

### ፲፱/ የእርሻ ሚኒስትራችን ደንቦች ለማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል ፤

የእርሻ ሚኒስትራችን ስለዚህ አዋጅ መልካም አፈጻጸም ከዚህ ቀጥሎ ስለተመለከቱት ጉዳዮች ደንቦች ማውጣት ይችላል ።

ሀ/ በበሽታ የተነደፉትን ወይም ተነድፈዋል ተብለው የተጠረጠሩትን ወይም ከበሽታ ያልተጠበቁትን በተለይም ማናቸውም በሽታ ሊነድፋቸው የሚችለውን ከብቶች ስለመመርመር ፤ ስለመከላከል ፤ ስለመከተብ ፤ በመድኃኒት ስለመርጨት ፤ ስለማዛወር ፤ ምልክት ስለማድረግ ፤ ስለመንከር ፤ ስለመሞከርና ስለማረድ ፤

ለ/ በሽታ አለበት በተባለ ሥፍራ ወይም በአካባቢው ወይም በሽታ ካለበት ሥፍራ ተዛውሮ የሚገኘውን የከብት በድንና ምግቡ የነበረውን ርካሽ ማር ፤ ሌላውንም ጉዝጓዝ ፤ መሣሪያ ፤ እበት ፣ ወይም ሌሎችን እነዚህን የመሳሰሉትን ስለማስወገድ ፤ ስለመቅበር ወይም ስለማከም ፤

ሐ/ የተቀበሩት በድኖች ተቆፍረው እንዳይወጡ ስለመከልከል ፤

መ/ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ከብቶችና የከብት በድን ፤ ጉዝጓዝ ፤ እበት ወይም የከብት ምግብ ሲዘዋወር ስለመቆጣጠር ፤

ሠ/ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሚላኩት ወይም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡት ከብቶች ጤና የሚረጋገጥበትን በገለልተኛ (የኳራንቲን) ጣቢያ ስለሚፈጸመው አሠራር ፤

ረ/ በበሽታ የተነደፉትን ወይም በበሽታ ከተነደፉት ከብቶች ጋር ግንኙነት አድርገዋል የተባሉትን ወይም በበሽታ ሊነደፉ ይችላሉ ተብለው የተጠረጠሩትን ከብቶች በተለይ በተወሰነላቸው ሥፍራ የሚመረመሩበትንና የሚጠበቁበትን ገለልተኛ (የኳራንቲን) ደንብ ስለማውጣት ፤

ሰ/ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ስለሚላኩትና ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገቡት ከብቶች መኖና ጉዝጓዝ መከልከል ወይም ደንብ ማውጣት ፤ እንዲሁም የሚገባበትንና የሚወጣበትን አኳኋን ስለመወሰን ፤

ሸ/ የከብቶችን መኖሪያ ሠፈር ወይም የታሰሩበትን ወይም የሚጠበቁበትን ሕንፃዎችና ሥፍራዎች የሕዝብ መገበያያዎችን ፤ መነገጃ ሥፍራዎችን ፤ ለከብቶቹ መጓጓዣ የተደረገውን ማናቸውንም የተሽከርካሪዎች ወይም የምድር ባቡር ማረፊያ ሥፍራዎችን ስለማንጻትና መድኃኒት ስለመርጨት ፤

ቀ/ በበሽታ ከተነደፈ ከብት ወይም ተነድፈዋል ተብለው ከሚጠረጠሩ ወይም በሽታው ካለበት ሥፍራ ላይ ከሚገኙት ከብቶች ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉትን ሠራተኞች ልብሳቸውንና ዕቃቸውን ጭምር መድኃኒት ስለመርጨትና ስለማንጻት ፤

በ/ ማናቸውም የከብት ክትባት መድኃኒት ወይም የቀንድ ከብት ደስታ ከሚባለው በሽታ ወይም ከሌላ በሽታ የሚገኘውን ሲረም ወይም ቫይረስ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስለማስገባት ፤ ወይም በአገር ውስጥ መሥራትን ስለመቆጣጠር ወይም ስለ መከልከል ፤

www.chilot.me



የከብቶችና ከከብቶች የሚገኙት ውጤቶች ፤ እንዲሁም የቆዳና የሌጦ ዓይነቶች መሻሻልና መጠናቸውም እየበረከተ እንዲሄድ ማድረግ ለንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ኤኮኖሚ የሚጠቅም መሆኑን ተረድተን ፤

ለዚሁም ዓላማ አፈጻጸም ለአርቢዎች ፤ ለነጋዴዎች ፤ ለአዘጋጇዎች መምሪያና ርዳታ መስጠት ፤ አስፈላጊ የሆኑትም አገልግሎቶች እንዲቋቋሙ ማበረታታትና ለሥራቸውም መቃናት አስፈላጊ የሆነው ደንብ እንዲወጣ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበን ፤

ይህንንም ተግባር ከፍጻሜ ለማድረስ የሚቻለው በሕግ አስፈላጊው ሥልጣን ተሰጥቶት ይህንኑ ሥራ የሚከታተል ድርጅት በማቋቋም መሆኑን አውቀን ፤

በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፳፯ኛው አንቀጽ የተመለከተውንና የሚኒስትሮች ምክር ቤታችን የመከረበትን ዓይተን ቀጥሎ ያለውን አዘናል ።

፩/ <u>አጭር አርእስት</u>

ይህ ትእዛዝ «የ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. የከብት ርባታና የሥጋ ቦርድ ትእዛዝ ተብሎ» ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ <u>ቦርዱን ስለማቋቋም</u>

ከዚህ ቀጥሎ «ቦርድ» እየተባለ የሚጠራ ፤ በዚህ ትእዛዝና በሌሎችም አግባብ ባላቸው ሕጎች በተመለከተው አኳኋን በዲሬክተሮች ቦርድና በዋና ሥራ አስኪያጅ አማካይነት ሥራውን የሚያከናውን አንድ ራሱን የቻለ «የከብት ርባታና የሥጋ ቦርድ» የተባለ ድርጅት በዚህ ትእዛዝ ተቋቁሟል ።

፫/ <u>ትርጉም</u>

ከዚህ ትእዛዝ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በቀር ፤ «ተረፈ ሥጋ» ማለት ፤ ከሥጋ በስተቀር ከታረዱ ከብት የሚገኙ ማንኛውንም ዋጋ ያለውን ሁሉ የሚጠቀልል ነው ። ይኸውም ወተትን አይጨምርም ።

«ቆዳ» ማለት ፤ የቀንድ ከብትና የግመል ቆዳ ነው ።

«ከብት» ማለት ፤ የቀንድ ከብት ፤ በግ ፤ ፍየል ፤ ግመል ፤ ፈረስ ፤ አህያ ፤ በቅሎና እነዚህን የመሳሰሉ እንስሳት ናቸው ።

«ሥጋ» ማለት ፤ ለምግብ የሚውል የቀንድ ከብት ፤ የበግ ፤ የፍየል ፤ የግመል ፤ የዶሮና እነዚህን የመሳሰሉ እንስሳት ሥጋ ነው ።

«ዶሮ» ማለት ፤ ለምግብነት የሚያገለግል ለማዳ አእዋፍ ነው ።

«አዘጋጅ» ማለት ፤ ከብትን ፤ ዶሮንና እንቁላልን ፤ ሥጋንና ተረፈ ሥጋን በሚሸጡበት መልክ የሚያዘጋጅ ማንኛውም ሰው ነው ።

«አርቢ» ማለት ፤ ከብትንና ዶሮን የሚያረባ ገበሬ ነው ።

«ሌጦ» ማለት ፤ የበግና የፍየል ቆዳ ነው ።

«ነጋዴ» ማለት ፤ ከብት ፤ ዶሮ ፤ ሥጋ ፤ እንቁላልና ተረፈ ሥጋ የሚገዛና የሚሸጥ ሰው ነው።

፬/ <u>የቦርዱ ተግባርና የሥራው ዓላማ</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባሮችና ዓላማዎች ይኖሩታል ፤

ሀ/ ጤናማና ምርጥ የሆነ ከብት ፤ ዶሮ ፤ ሥጋ ፤ እንቁላልና ተረፈ ሥጋ እንዲረባና ገበያም እንዲያገኝ ማበረታታት ፤

www.chilot.me



ለ/ ስለከብት ፣ ዶሮ ፣ ሥጋ ፣ እንቁላልና ተረፈ ሥጋ ርባታ ፣ ዝግጅት ፣ መጓጓዣና ገበያ መረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት ፤

ሐ/ የከብት መንጋዎች የሚጓዙበት መንገድ ፣ የውሃ ቦታና የገበያ ድርጅት በተሻሻለ አኳኋን እንዲደራጅ ማድረግና ይህንኑም መቆጣጠር ፤

መ/ በከብትና በዶሮ ርባታ ማጓጓዣ ዝግጅትና በገበያም በኩል ምርምርና ጥናት እንዲደረግ ማነቃቃት ፤

ሠ/ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የከብትና ሕክምና መሥሪያ ቤት የከብት ክትባትና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን በሚፈጽምበት ጊዜ ፤ አስፈላጊ ሆኖ የሚጠይቀውን ርዳታ መስጠትና የከብት ሕክምና ተግባሮች በተስፋፋ ሁኔታ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ረገድ መተባበር ፤

ረ/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ማስታወቂያ በማውጣትና በኢንተርናሽናል የንግድ ትርኢት ተካፋይ በመሆን ፣ የከብት ፣ የዶሮ ፣ የሥጋ ፣ የእንቁላልና የተረፈ ሥጋ ገበያ እንዲስፋፋ ማድረግ ።

፭/ ኃላፊነት ፤

ቦርዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ለሚከተሉት ተግባሮች ኃላፊ ይሆናል ።

ሀ/ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባሮች ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎች (ፖሊሲዎች) እና የሥራ እቅዶች (ፕሮግራሞች) ማውጣትና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፤

ለ/ የሥራ መመሪያዎችንና ፕሮግራሞችን በሚገባ ለማከናወንና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን የአስተዳደር ድርጅት ማቋቋም ፤

ሐ/ ባጀቱን ማዘጋጀት ፤

መ/ በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባሮች ማከናወን ።

፮/ አቋም ፤

ቦርድ የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ይሆናል ፤

ሀ/ የዲሬክተሮች ቦርድ

፩/ የቦርዱ ሥልጣን ሁሉ ለአንድ የዲሬክተሮች ቦርድ የተሰጠ ይሆናል ።

፪/ የዲሬክተሮች ቦርዱም ፤

የእርሻ ሚኒርትር ወይም ሚኒስትሩ ሥልጣን የሚሰጠው ወኪሉ በሊቀ መንበርነት ከሕዝብ ጤና ጥበቃ ፣ ከንግድና እንዱስትሪ ፣ ከገንዘብና ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስትሮች በየሚኒስትሮቻቸው የሚመረጡ አንዳንድ አባሎች እንደዚሁም አግባብ ካላቸው የእንዱስትሪ ክፍሎች ጋር በመመካከር የእርሻ ሚኒስትሩ ከነጋዴዎች ፣ ከአዘጋጂዎችና አርቢዎች መካከል የሚመርጣቸው የነጋዴዎች ፣ የአዘጋጂዎችና የአርቢዎች አንዳንድ ወኪሎች ፣ በአባልነት ይገኙበታል ። የነጋዴዎቹ ፣ የአዘጋጂዎቹና የአርቢዎቹ ወኪሎች ሆነው የሚመረጡትም ለሁለት (፪) ዓመት ያገለግላሉ ፤ እንደገናም ለመመረጥ መብት ይኖራቸዋል ።

፫/ የዲሬክተሮች ቦርዱም የራሱን የሥራ አፈጻጸም የውስጥ ደንብ ያወጣል ።

ለ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤

በዲሬክተሮች ቦርድ አሳሳቢነት እኛ ለምንወስነው ጊዜ የሚያገለግል አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ በኛ ይሾማል ። እሱም የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ጠቅላላ መምሪያ መሠረት የቦርዱን ሥራ ያከናውናል ፤

www.chilot.me



## ፫/ የቦርዱ ሥልጣን ፤

ቦርዱ የከብትን ፣ የዶሮን ፣ የሥጋን ፣ የእንቁላልንና የተረፈ ሥጋን አሠራር ፣ አገልግሎት ፣ አያያዝ ፣ እንቅስቃሴ ፣ አሻሻጥ ወደ ውጭ አገር ሲላክና ከውጭ አገር ሲመጣ (ኢምፖርትና ኤክስፖርት) ለመቆጣጠርና ለመምራት ሥልጣን አለው ።

ከዚህም በቀር ቦርዱ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ከላይ በተሰጠው ሥልጣን ብቻ ሳይወሰን ቀጥሎ ያሉትን ጭምር ለመፈጸም ሥልጣን አለው ።

ሀ/ የርባታ ጣቢያዎች ፣ መጋዘኖች ፣ ገበያ ፣ የገበያ ቦታዎች ፣ በረቶች ፣ የከብት ማጠጫ ኩሬዎች አስፈላጊ ሆነው ሳለ ፣ ካሁን ቀደም በግል ድርጅቶች በኩል ተደራጅተው ያልተገኙ ሲሆን ፣ እነዚህን ለመሥራት ፣ ለመያዝ ፣ ለማከራየትና ለማስተዳደር ፣ እንደዚሁም በቂ የሆኑ የማዘጋጃ ድርጅቶች በነዚህ ከሥፍራዎች እንዲቋቋሙ ለማበረታታት ፤

ለ/ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ለመበደር ፣ ለማበደር ፣ በዋስትና ለማስያዝ ፣ ለመሸጥና ለመለወጥ ፤

ሐ/ የከብትና የዶሮ ገበያዎችን ለመመደብና ለመምራት ፤

መ/ ከብት ፣ ዶሮ ፣ ሥጋ ፣ እንቁላልና ተረፈ ሥጋ ወደ ውጭ አገር ሲላክና ከውጭ አገር ሲመጣ የሚያገለግሉ የኳራንቲን ጣቢያዎችን አቋቁሞ እንዲሠራ ከከብት ሕክምና መሥሪያ ቤት ሲጠየቅ በጥያቄው መሠረት ለመፈጸም ፤

ሠ/ ከብት በሚገኝበት መጀመሪያ ገበያ አንሥቶ እፋብሪካውና ትራንስፖርት ጣቢያው እስኪደርስ በተቻለ መጠን ግጦሽና ውሃ የሚገኝበትን ሁኔታ ተከትሎ መንገድ ለማደራጀት ፤

ረ/ የከብት ፣ የዶሮ ፣ የሥጋና የእንቁላል እንዱስትሪ በጠቅላላው እንዲስፋፋና እንዲሻሻሉ የሚረዱ ዘዴዎችን ለማውጣት ፤ በተለይም በዚህ ብቻ ሳይወሰን ፣ አርቢዎችና አዘጋጂዎች በቀረጥ ወይም በግብር መክበድ ምክንያት ይህ ንግዳቸው እንዳይስፋፋ የሚታወኩ ሲሆን ፣ ችግራቸው የሚቃለልበትን ሐሳብ ለመንግሥት ለማቅረብ ፤

ሰ/ ለአገሪቱ ጠቅላላ ኤኮኖሚ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የከብት ፣ የዶሮ ፣ የሥጋ ፣ የእንቁላልና የተረፈ ሥጋ መነሻ ዋጋ እንዲወሰን ለመንግሥት ሐሳብ ለማቅረብ ፤

ቀ/ የከብት ፣ የዶሮ ፣ የሥጋ ፣ የእንቁላልና የተረፈ ሥጋ ትክክለኛ ሚዛንና ደረጃቸውም የሚወሰንበትን ሁኔታ ለማዘጋጀት ፣ ለማቋቋምና ይኸንኑም በሥራ ላይ ለማዋል ፤

በ/ በአገር ውስጥ በሚሠራው ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ በሚላከው ከብት ፤ ሥጋ ፤ ዶሮ ፤ እንቁላልና ተረፈ ሥጋ ሊከፈል የሚገባውን የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን ፤ ለማስከፈልና ለመሰብሰብ ፤ ስለሆነም በዚህ አኳኋን የሚወሰነው ያገልግሎት ዋጋ በማንኛውም ምክንያት ከዚህ በታች ከተመለከተው መጠን መብለጥ የለበትም ፦

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቆዳ | | $ 0.20 | በአንድ ቆዳ |
| ሌጦ | | $ 0.08 | » ሌጦ |
| በሬ | በቁም | $ 1.50 | በያንዳንዱ |
| | የታረደ | $ 1.50 | » |
| በግና ፍየል | በቁም | $ 0.40 | » |
| | የታረደ | $ 0.40 | » |

www.chilot.me



፬/ <u>የወጪ ንግድ ፈቃድ ፤</u>

ማንኛውም ሰው ከብት ፣ ዶሮ ፣ ሥጋ ፣ እንቊላል (በቅርፊቱ ውስጥ እንዳለ ፣ በፈሳሽነት ወይም በደረቁ) ፣ ቆዳ ፣ ሌጦና ሌሎችም ተረፈ ሥጋዎች ከከብት ርባታና የሥጋ ቦርድ የተሰጠው ሕጋዊ የሆነ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ ከሌለው በቀር ከኢትዮጵያ ሊያወጣ አይችልም ።

፭/ <u>የውጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ አሰጣጥ ፤</u>

፩/ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፫ የተጻፉት ሁኔታዎች ተጠብቀው ፣ የውጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ የሚሰጠው በቦርዱ አስተያየትና ቦርዱ በየጊዜው በሚወስናቸው ሁኔታዎችና ቁጥጥሮች መሠረት ሲሆን ፣ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ሊሠሩ የሚችሉበትንም ሥፍራ ይወስናል ።

፪/ ማናቸውም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የተሰጠ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ ለሦስት ዓመት የሚሠራ ሆኖ በቦርዱ አስተያየት ሊታደስ ይቻላል ። ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የተሰጠ ወይም የታደሰ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ ሊወሰድ ፣ ሊሠረዝ ፣ ሊሻር ወይም ሊሻሻል ይችላል ።

፫/ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ የሚሰጥበት ፣ የሚወሰድበት ወይም የሚሠረዝበት ሁናቴ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

ሀ/ ጤናማና ምርጥ የሆነ የከብት ፣ የዶሮ ፣ የሥጋ ፣ የእንቊላል ፣ የቆዳ ፣ የሌጦና የሌሎችንም ተረፈ ሥጋዎች ገበያና አሠራር ለማበረታታት የሚቻል ሲሆን ፤

ለ/ በአንዳንድ ቦታዎች ከብቶችንና ዶሮዎችን እንዳያልቁ ለመጠበቅ ፤

ሐ/ አዘጋጂውና ነጋዴው ቦርዱ ያወጣቸውን ደንቦችና ደረጃዎች የተከተሉ ሲሆንና በአዋጁ መሠረት የተወሰነውን ያገልግሎት ዋጋ በጊዜው ሲከፍሉ ነው ።

፬/ ማንኛውም በዚህ ደንብ መሠረት የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ እንዲኖረው የሚያስፈልግ ሰው ፣ ፈቃዱን ሥልጣን የተሰጠው የቦርዱ ሠራተኛ በጠየቀው ጊዜ ማቅረብ አለበት ።

፭/ በቂ የሆነ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች ከኢትዮጵያ ውጪ የሚልክ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፮ መሠረት ይቀጣል ።

፮/ ይህ ደንብ <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ታትሞ ከወጣበት ከሦስት ወር በኋላ ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ. ም.

www.chilot.me



## ሐ/ ሌሎች እህሎችና ጥራጥሬዎች ፤

የእህሉቹ (ከስንዴ በስተቀር) ወይም የጥራጥሬዎቹ ብዛት ምንም ያህል ቢሆን የተደባለቀ መሆኑ ሲገመት በዓይነቱ ውስጥ ከሚገኘውና ወደ ዱቄት ለመለወጥ ከሚችለው ልዩ ነገር ከሞላው ሚዛኑ በመቶ አምሳው (50%) ብቻ ከድብልቅ ይቆጠራል ፤ ዳሩ ግን በዓይነቱ ውስጥ የሚገኘውና ወደ ዱቄት ለመለወጥ የማይችለው ልዩ ነገር ሞላው ሚዛኑ ከቆሻሻ ይቆጠራል ።
ለዚህ ለንዑስ አንቀጽ (ሐ) ምክንያት ፦

፩/ «ወደ ዱቄት ለመለወጥ የሚችል ልዩ ነገር» ሲባል እህል ወይም ጥራጥሬ ተብሎ ዘሩ ተሠይሞ ከቀረበው በስተቀር ማናቸውንም ተፈጭተው ወደ ዱቄት ለመለወጥ የሚችሉትን እህልና ጥራጥሬ ሁሉ ይጨምራል ፤

፪/ «ወደ ዱቄት ለመለወጥ የማይችል ልዩ ነገር» ሲባል እንክርዳድ ፤ ኰርጠብና ሌሎችንም የአረም ፍሬዎች ፤ ድንጋይ ፤ አሸዋ ፤ አፈር ፤ ጉድፍ ፤ ገለባ ፤ እድፍ ወይም ተፈጭቶ ወደ ዱቄት ለመለወጥ የማይችሉትን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ ይጨምራል ።

## መ/ የከብት ቀለብ

የከብት ቀለብ ብዛቱ ምንም ያህል ቢሆን ድብልቅነቱ ሲገመት በዓይነቱ ውስጥ የሚገኘውና ወደ ዱቄት ለመለወጥ የማይችለው እንደ ድንጋይ ፡ አሸዋ ፡ አፈር ፡ ጉድፍ ፡ ገለባ ፡ እድፍ ፡ አቧራ ያለ ወይም ለከብት ቀለብ የማይስማማ ማናቸውም ነገር ሁሉ ከቆሻሻ ይቆጠራል ።

፳/ የተፈቀደለት እህል አበጣሪ የሆነ ሁሉ ባበጠረው ለማናቸውም ልዩ ልዩ እህል ፡ የዘይት ፍሬ ፤ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ በሠንጠረዥ (ሀ) እንደተመለከተው አድርጎ ወደ ውጭ አገር የሚላክ እንደሆነ (ወደ ውጭ አገር መላኪያ ምስክር ወረቀት) እንዲሰጥ ለአገር ውስጥም እንደሆነ በሠንጠረዥ (ለ) እንደተመለከተው አድርጎ (የአገር ውስጥ ምስክር ወረቀት) የሚል የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ታዟል ።

፳፩/ የተፈቀደለት ባለወፍጮ የሆነ ሁሉ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ለፈጨው ልዩ ልዩ ዱቄት ሁሉ በሠንጠረዥ (ሐ) በተመለከተው መሠረት (ወደ ውጭ አገር መላኪያ ምስክር ወረቀት) የሚል የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ታዟል ። እንደዚሁ ያለውም የምስክር ወረቀት በተመደበው የምርመራ ሥርዓት መሠረት ፤ የታወቀ ኬሚስት ዓይነቱን ከመረመረበት ምርመራ ጋር መስማማት አለበት ።

፳፪/ የተፈቀደላቸው እህል አበጣሪዎች እንዲበጠሩ ሕዝብ የሚያቀርብላቸውን እህሎች ፤ የዘይት ፍሬዎች ፤ ጥራጥሬዎችና የከብት ቀለብ ሁሉ ማበጠር አለባቸው ። ሊበጠሩ የቀረቡለትንም ሁሉ የተፈቀደለት እህል አበጣሪው በቀረቡለት ተራ ያበጥራል ።

፳፫/ እያንዳንዱ የውጭ አገር መላኪያ የምስክር ወረቀት እንደሚከተለው ለማከፋፈል እንዲመች ስድስት ላይ መጻፍ አለበት ፤

ሀ/ ዋናውንና መጀመሪያውን ኮፒ የተፈቀደለት እህል አበጣሪው ወይም የተፈቀደለት ባለ ወፍጮው ወዲያው ለእህሉ ፤ ለዘይቱ ፍሬ ፤ ለጥራጥሬው ፤ ለከብቱ ቀለብ ፤ ወይም ለዱቄቱ ባለቤት ወይም ለወኪሉ ይሰጣል ። የተባሉትም ዋናውና መጀመሪያው ኮፒ የሚወስንዋቸውን እህል ፤ የዘይት ፍሬ ፤ ጥራጥሬ ፤ የከብት ቀለብ ወይም ዱቄት ለሚገዛው ሰው ይተላለፉና ከዚያ ወዲያ ከሌሎች የመርከብ ማስጫኛ ሠነዶች እንደ መርከብ ደረሰኝ ካሉት ጋር ለውጭ አገር ገዢ ወይም ለባንኩ ይተላለፋሉ ።

ለ/ ሁለተኛው ኮፒ በተፈቀደለት እህል አበጣሪ ወይም በተፈቀደለት ባለወፍጮ እጅ ይቀራል ።

ሐ/ ሦስተኛው ኮፒ በተፈቀደለት እህል አበጣሪ ወይም በተፈቀደለት ባለወፍጮ ቀድሞ ነገር ለእህሉ ባለቤት ወይም ለባለሥልጣን ወኪሉ ይሰጣል ። ይህም የተባለው ሦስተኛ ኮፒ ጽሑፉ የሚወስናቸውን እህል ፤ የዘይት ፍሬ ፤ ጥራጥሬ ፤ የከብት ቀለብ

www.chilot.me



ወይም ዱቄት ለሚገዛው ሰው ይተላለፍና ከዚያ ወዲያ የተባሉትን እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ፣ የከብት ቀለብ ወይም ዱቄት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ ባደረገው ሰው እጅ ይቀራል ።

መ/ አራተኛውና አምስተኛው ኮፒ በተፈቀደለት እህል አበጣሪ ወይም በተፈቀደለት ባለ ወፍጮ ለባለቤቱ ወይም ለባለሥልጣን ወኪሉ ይሰጣሉ ። ከዚያ በኋላ እነዚህ የተባሉት ኮፒዎች ጽሑፋቸው የሚወስናቸውን እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ፣ የከብት ቀለብ ወይም ዱቄት ለሚገዛው ሰው ይተላለፋሉ ፤ በመጨረሻም የተባሉት ዕቃዎች ወደ ውጪ አገር በሚላኩበት ጊዜ ለጉምሩክ ይቀርባሉ ።

፱/ የአገር ውስጥ ምስክር ወረቀት የሆኑት ሁሉ በጥንድ ይወጣሉ ፤ ዋናው ለባለቤቱ ተሰጥቶ ኮፒው በተፈቀደለት እህል አበጣሪ ወይም በተፈቀደለት ባለወፍጮ እጅ ይቀራል ።

፲/ ለውጭ አገር መላኪያ ምስክር ወረቀት የወጣላቸው እህሎች ፣ የዘይት ፍሬዎች ፣ ጥራጥሬ ዎች ፣ የከብት ቀለቦች ወይም ዱቄቶች ሁሉ በከረጢቶች ውስጥ ተከተው ከረጢቶቹ በእርሳስ ወይም በብረት ማኅተም ይዘጋሉ ፤ በማኅተሙም ላይ የባለ ፈቃድ እህል አበጣ ሪው ወይም የተፈቀደለት ባለወፍጮው ስምና የምስክር ወረቀቱ ቁጥር ይኖርበታል ። ከከረጢቱ ማናቸውም ክፍል የሚሰፋበት ክር አንድ ዓይነት መሆን አለበት ። እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ በአያሌው ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተፈ ለገ እንደሆነ ከቦርዱ ጋር ልዩ ድርጅት ይደረጋል ።

፲፩/ ቦርዱ ልዩ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬና የከብት ቀለብ የሆነ ሁሉ የተመደበውን ሙሉ ክብደት ለመስጠት ቀጥሎ ባለው ልክ በከረጢት ይከተታል ፤—

| | | |
|---|---|---|
| እህል ፣ ጥራጥሬና የከብት ቀለብ ፩ ከረጢት ከነከረጢቱ | ፻፩ | ኪ/ግ/ |
| የዘይት ፍሬ (ከኑግና ከጉሎ ሌላ) ፩ ከረጢት ከነከረጢቱ | ፺፩ | » |
| ኑግና የጉሎ ፍሬ ፩ ከረጢት ከነከረጢቱ | ፻፲ | » |
| የተፈሰፈሰ ለውዝ ፩ ከረጢት ከነከረጢቱ | ፻፩ | » |

የተቀባዩ አገር ሕግ ሚዛኑ ከዚህ የበለጠ እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ በአንድ ከረጢት ለመከተት በሚፈቅድበት ከፍ ያለ ሚዛን ለመከተት ከቦርዱ ልዩ ፈቃድ ለማግኘት ይቻላል ።

፲፪/ የተፈቀደላቸው እህል አበጣሪ የሆኑ ሁሉ ባበጠሩት እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ የተገኘውን እንክርዳድ ወይም ለጉዳት የሚሰጡትን የአረም ፍሬዎች ሁሉ እንዲያጠፉ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ፤ ደግሞም ታዞዋል ።

፲፫/ እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ ፣ ለማስበጠር የሚከፈለው ዋጋ በሆን ጠረዥ (መ) እንደተመደበው ይሆናል ።

፲፬/ የጉምሩክ ሹማምንቶች በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ውስጥ በ፭ኛና በ፯ኛ አንቀጽና በሠንጠረዥ (ሀ) ና (ሐ) እንደተመለከተው ወደ ውጭ አገር ለመላኪያ በወጣው እውነ ተኛ የምስክር ወረቀት ኮፒ ያልተወሰኑትን እህሎች ፣ የዘይት ፍሬዎች ፣ ጥራጥሬዎች ፣ የከብት ቀለቦች ወይም ዱቄቶች ወደ ውጭ አገር እንዳይላኩ ለመከልከል በዚህ ማስታ ትቂያ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ።

፲፭/ በሚገባ የተሾሙ የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ወኪሎች የተፈቀደለት እህል አበጣሪ ፣ ወይም የተፈቀደለት ባለወፍጮ ፣ የምስክር ወረቀት ያወጡላቸውን እህሎች ፣ የዘይት ፍሬዎች ፣ ጥራጥሬዎች ፣ የከብት ቀለቦች ወይም ዱቄቶች ከእነዚህ ደንቦች ጋር መስማማት አለመስማማታቸውን ለማረጋገጥ በማናቸውም በሚገባ ጊዜያትና ሥፍራ ገብተው ሊመ ረምሩና ሊቆጣጠሩ በዚህ ማስታወቂያ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ።

፲፮/ የእነዚህን ደንቦች ቃላት ማናቸውንም ተላልፎ የተገኘ ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

የተጠቀሰው ሕግ

የወ.መ.ሕ. ፲፰/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) እን. ፫፻፭፬ ፣ ፫፻፭፭ ፣ ፬፻፭፭ ፣ ፭፻፲፩ ፣ ፭፻፲፪ ።

www.chilot.me



## ሠንጠረዥ «ሀ»

የምስክር ወረቀት ቁ...............

ለውጭ አገር

### የምስክር ወረቀት ስለኢትዮጵያ እህል ፣ የዘይት ፍሬ

ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ ጥራት ።

እኔ/እኛ ..................................................በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ስለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሠረት የተፈቀደለት እህል አበጣሪ ከዚህ በታች ብዛቱ የተዘረዘረ ..............................መበጠሩንና ከ..................................የበለጠ ድብልቅ እንደሌለበት መረጋገጡ በዚህ እመስክራለሁ ።

ሁተታ

| ከ ረ ጢ ቶ ች | | |
|---|---|---|
| ቍጥር | ሚዛን | ምልክት |
| | | |

..........................................

ቀን

..........................................

የተፈቀደለት እህል አበጣሪ

የፊታድ ቁጥር ................

## ሠንጠረዥ «ለ»

የምስክር ወረቀት ቁ...............

ለአገር ውስጥ

### የምስክር ወረቀት ስለኢትዮጵያ እህል ፣ የዘይት ፍሬ ፣

ጥራጥሬ ፣ ወይም የከብት ቀለብ ጥራት ።

እኔ/እኛ ....................................በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ስለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሠረት የተፈቀደለት እህል አበጣሪ ከዚህ በታች ብዛቱ የተዘረዘረ....................................መበጠሩንና ከ ..............................የበለጠ እንደሌለበት መረጋገጡን በዚህ እመስክራለሁ ።

www.chilot.me



ሀተታ

| ክ ሬ ጢ ቶ ች | | |
|---|---|---|
| ቁጥር | ሚዛን | ምልክት |
| | | |

..........................
የተፈቀደለት እህል አበጣሪ

..........................
ቀን

የፈቃድ ወረቀት ቁጥር ..........................

ሥንጠረዥ «ሐ»

የምስክር ወረቀት ቁጥር ..........................

ለውጭ አገር

የምስክር ወረቀት ስለዱቄት ።

እኔ/እኛ ........................................በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ስለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሠረት የተፈቀደለት ባለወፍጮ ከዚህ በታች ብዛቱ የተዘረዘረ............................................ከ.................................. በመቶ የማይበልጥ እርጥበት እመድም በመቶ ..........................የማይበልጥ እንደሌለበት መረጋገጡን በዚህ እመሰክራለሁ ።

ሀተታ

| ክ ሬ ጢ ቶ ች | | |
|---|---|---|
| ቁጥር | ሚዛን | ም ል ክ ት |
| | | |

..........................
የተፈቀደለት ባለ ወፍጮ

..........................
ቀን

የፈቃድ ወረቀት ቁጥር ..........................

www.chilot.me



ሠንጠረዥ «መ»

ለማበጠርና በደረጃ ለመመደብ

የሚከፈለው ዋጋ

በኩንታል የሚከፈለው የኢትዮጵያ ብር

ከፍተኛ ዋጋ

| | |
|---|---|
| **እህል** | |
| ስንዴ | 0.75 |
| ገብስ | 1.00 |
| በቆሎ | 1,00 |
| ማሽላ | 1,00 |
| **ጥራጥሬ** | |
| አተር | 1.00 |
| ባቄላ | 1.00 |
| አደንጓሬ | 1.00 |
| ምስር | 1.00 |
| ሽንብራ | 1.00 |
| **የዘይት ፍሬ** | |
| ኑግ | 1.00 |
| ሰሊጥ | 1.00 |
| ተልባ | 1.00 |
| ሱፍ | 1.00 |
| ጐመንዘር | 1.00 |
| የጉሎ ፍሬ | 1.00 |
| ሰናፍጭ | 1.00 |

የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ

ጠቅላላ ፈቃድ ፪ኛ ቁጥር

በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ስለማቋቋም የወጣው አዋጅ ለኢትዮጵያ የእህል ቦርድ የሰጠውን ሥልጣንና ይህንኑ ተከታትሎ በየጊዜው የወጡትን ደንቦች በመከታተል ፡—

፩/ በሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የወጣው ጠቅላላ ፈቃድ ቁ. ፩ በዚህ ተሰርዞዋል ፤

፪/ ከዚህ በታች በዚሁ ውስጥ በ፫ኛው ክፍል እንደተመለከተው ካልሆነ በስተቀር ቀጥለው የተዘረዘሩትን ብቻ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ተፈቅዶዋል ፡—

ሀ/ ስንዴ በመቶ ከሦስት (፫) የበለጠ ድብልቅ የሌለበት ፤

ለ/ የዘይት ፍሬ (ከጉሎ ፍሬ በስተቀር) በመቶ ከሦስት (፫) የበለጠ ድብልቅ የሌለበት ፤

ሐ/ የጉሎ ፍሬ በመቶ ከአንድ (1%) የበለጠ ድብልቅ የሌለበት ፤

መ/ ሌሎች እህሎችና ጥራጥሬዎች በመቶ ከሦስት (3%) የበለጠ ድብልቅ የሌለባቸው ፤

www.chilot.me



ሠ/ የከብት ቀለብ በመቶ ከአምስት (5%) የበለጠ ድብልቅ የሌለበት ይኸውም እነዚህ የተባሉት እህሎች ፥ የዘይት ፍሬዎች ፥ ጥራጥሬዎችና የከብት ቀለቦች ቦርዱ ባወጣቸው ደንቦች መሠረት በተፈቀደለት እህል አበጣሪው ወደ ውጭ አገር ለመላክ ተመስክሮላቸው እንደሆን ነው ።

፫/ ከዚህ በላይ በዚሁ ውስጥ በ፪ኛው ክፍል የተመለከተው ውሳኔ ሳይከለከል ቀጥለው ያሉት እህሎች ፥ የዘይት ፍሬዎች ፥ ጥራጥሬዎች ፥ ወይም የከብት ቀለቦች ከተፈቀደለት እህል አበጣሪ ፥ ወደ ውጭ አገር መላኪያ የምስክር ወረቀት ሳያስፈልጋቸው ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ይችላሉ ፤

ሀ/ በአዲግራት ፥ በአድዋና በድሬዳዋ ፥ በቅለው ከእነዚህ ቦታዎች ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እህሎች ፥ የዘይት ፍሬዎች ፥ ጥራጥሬዎች ወይም የከብት ቀለቦች ፥ ይኸውም የሚረጋው እስከ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. ድረስ ነው ፤

ለ/ የሺያጭ ውል ለመፈጸም ወደ ውጭ አገር ለመላክ የቀረቡ እህል ፥ የዘይት ፍሬ ፥ ጥራጥሬ ወይም የከብት ቀለብ (፩) ውሉ የተደረገው ይህ ጠቅላላ ፈቃድ ከሚጸናበት ቀን አስቀድሞ እንደሆነና (፪) በውሉም ውስጥ የእህሉ ፥ የዘይት ፍሬው ፥ የጥራጥሬ ወይም የከብቱ ቀለብ ጥራት ተመርምሮ በውሉ ውስጥ ከተመለከተው መቶኛ ያነሰ ድብልቅነት ያለባቸው ሆነው ቢገኙ ለኛው የበለጠ ዋጋ ይሰጠዋል ። ድብልቅነታቸውም ከተመለከተው መቶኛ በዝቶ ቢገኝ ያነሰ ዋጋ ይሰጠዋል ፤ የሚል ቃል የሌለበት እንደሆነ በ(፩) ና (፪) የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን ከተፈቀደለት እህል አበጣሪ የምስክር ወረቀት አለማስፈለጉን ለጉምሩክ ሊመሰክር ሥልጣን የተሰጠው የምንዛሬ ተቆጣጣሪ ማረጋገጥ አለበት ።

የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ

ጠቅላላ ፈቃድ ፫ኛ ቁጥር

በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ ስለማቋቋም የወጣው አዋጅ ለኢትዮጵያ የእህል ቦርድ የሰጠውን ሥልጣንና ይህንኑ ተከታትሎ በየጊዜው የወጡትን ደንቦች በመከታተል በመቶ ከአሥራ ሁለት ተኩል (12½%) የሚበልጥ እርጥበትና በመቶ ነጥብ ሰባት (0.7%) የሚበልጥ አመድ የሌለበትን ዱቄት ቦርዱ ባወጣቸው ደንቦች መሠረት የተፈቀደለት ባለወፍጮ አረጋግጦ የውጭ አገር መላኪያ ምስክር ወረቀት ከሰጠ የተፈቀደለት ላኪ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ይችላል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ

www.chilot.me



## ፲፱/፰ (፲፱፻፶፪) መ. ፪፻፳፯*

## የኢትዮጵያ የእህል ማኅበር ቻርተር

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

እህሎችን ፣ ጥራጥሬዎችንና የዘይት ፍሬዎችን የሚገዛ ድርጅት በማቋቋም በግብርና ሥራ ላይ ያለው ሕዝባችን የደከመበትን ሰብል በዓለም ገበያ ዋጋ መሠረት የሚሸጥበት የተረጋገጠ ገበያ እንዲያገኝ ፤

እህሎች ፣ ጥራጥሬዎች ፣ የዘይት ፍሬዎችና ሌሎችም የእርሻ ሰብሎች በብዛት እንዲዘሩና ወደ ውጭ አገር እንዲወጡ ለማድረግ ፣ የእህሎችን ዓይነት በማሻሻልና በማብዛት ደህና ዋጋ የሚያገኙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ገበሬዎችን ለማበረታታት ፤

ከዚህ የሚከተለውን አዘናል ።

### አንቀጽ ፩

### የኢትዮጵያ የእህል ማኅበር መቋቋም

ከዚህ በታች «ማኅበር» እየተባለ የሚጠራ አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኢትዮጵያ የእህል ማኅበር በዚህ ተቋቁሟል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፫/፲፮ (፲፱፻፶፮) ት. ፴፩ አን. ፪ ተሻሻለ ።

### አንቀጽ ፪

### የማኅበሩ ዓላማ

የማኅበሩ ዓላማ የእርሻ ሰብሎችን ዋጋ እንዲረጋጋ በማድረግ ፣ ዓይነታቸውን በማሻሻልና ወደ ውጭ አገርም እየተላኩ የሚሸጡበትን ሁኔታ በማደራጀት ፣ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ የእርሻ ሰብል በሰፊው እንዲመረት ማበረታታት ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፫/፲፮ (፲፱፻፶፮) ት. ፴፩ አን. ፪ ተሻሻለ ።

### አንቀጽ ፫

### የማኅበሩ ሥልጣን

ማኅበሩ የሥራ ዓላማውን ለመፈጸም ካለው መብት በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለመፈጸም ሥልጣን አለው ።

---

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፫/፲፮ (፲፱፻፶፮) ት. ፴፩ ፤ ፳፯/፳ (፲፱፻፷) ት. ፶፫ ተሻሻለ ።

www.chilot.me



ሀ/ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ምቹ በሆኑ ሥፍራዎች የእህል መግዣና መሸጫ ጣቢያዎች ለማቋቋምና ሥራውን ለማካሄድ ፤

ለ/ የእርሻ ሰብሎችን ለመግዛት ፤

ሐ/ የእርሻ ሰብሎችን ወደ ውጭ አገር ለሚያወጡ ማናቸውም ሰዎች ፤ ኩባንያዎች ፤ ማኅበሮችና ወኪሎች መሸጥ ፤

መ/ የእርሻ ሰብሎችን ወደ ውጭ አገር ለማውጣት ወይም በሀገር ውስጥ መሸጥ ፤

ሠ/ የእርሻ ሰብሎችን ለመግዛት ፤ በደረጃ ለመለየት ፤ ለማበጠር ፤ ለማስፈጨት ፤ ትራንስፖርት ለማድረግ ፤ በመጋዘን ለማስቀመጥ ፤ ለመሸጥና በጠቅላላው በትርፍም ሆነ በሌላ ጉዳይ በእርሻ ለመነገድና ይህን የመሳሰለውን ለመሥራት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ፤ ዕቃ ወይም ሌላ ዓይነት ካፒታል በሥራ ላይ ለማዋል ፤

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት ፤ እጅ ለማድረግ ፤ ለመያዝ ፤ ለመሸጥ ፤ ለሌላ ለማዛወር ፤ ለመለወጥ ፤ እሲዞ ገንዘብ ለመበደር ፤ በሌላ አኳኋን ዋስትና ለማድረግ ፤ ለማከራየት ወይም በማናቸውም በሌላ አኳኋን እንዳስፈለገው ለማድረግ ፤

ሰ/ ለመክሰስም ፤ ለመከሰስም ፤

ቀ/ ከማናቸውም መንግሥት ወይም ከመንግሥትም መሥሪያ ቤት ወይም ሰው ወይም በሕግ ከተቋቋመ ማኅበር ጋር ማናቸውንም ዓይነት ኮንትራት ለመዋዋልና ለመፈጸም ፤

በ/ ከማናቸውም ሰው ወይም በሕግ ከተቋቋመ ማኅበር ገንዘብ ለመበደር ፤ ገንዘብ የሚያስቀብሉ ሠነዶች ፤ የገንዘብ ማዘዣዎች ፤ ሐዋላዎች ፤ ቦንዶች ፤ ሊሸጡና ሊለወጡ የሚችሉ ሠነዶችና በዋስትናም ሆነ ያለዋስትና የገንዘብ ብድር የተሰጠባቸው ወይም በሌላ አኳኋን የተያዙ የባለዕዳነት ማስረጃዎች በየጊዜው ለመውሰድ ፤ ለመቀበል ፤ ለማስተላለፍ ፤ ለማስከፈል ፤ ለማዘጋጀትና ለማውጣት ፤

ተ/ ማናቸውንም ዓይነት ዕቃዎችና አስፈላጊ ነገሮች ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ፤

ኀ/ ቤቶች ፤ መጋዘኖች ፤ ጐተራዎች ፤ የእህል ማንሻና ማድረቫ ማከናወኛዎች ሌሎችም ሥራዎች ለመሥራትና ለማደራጀት ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

በ፳፫/፲፯ (፲፱፻፶፯) ት. ፴፩ እን. ፪ ተሻሻለ ።

በድሮው አጻጻፍ «ሸ» ና «ቸ» የተባሉት ፊደላት ለንዑስ አንቀጾች ተራ መስጫ አያገለግሉም ነበር። ስለዚህ አሁን በዚህ የማይገኙበት ምክንያት በጥንቱ ልማድ ስለቀሩ ነው እንጂ የተዘለሉ አንቀጾች የሉም።

## አንቀጽ ፬

## ስለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት

ሀ/ የማኅበሩ ዋና ጽሕፈት ቤት በአዲስ አበባ ነው ።

ለ/ የዲሬክተሮች ቦርድ ሲወስን ማኅበሩ በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ አገርም ሌሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ፤ የእህል መግዣና መሸጫ ማከናወኛዎች ሊኖሩት ይችላል ።

www.chilot.me



፩/ ይህ ደንብ «የ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. የቡና ማበጠርና በደረጃ የመመደብ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ፈቃድ የተሰጣቸው ቡና አበጣሪዎችና በደረጃ መዳቢዎች ቡና ሲያበጥሩና በደረጃ ሲመ ድቡ በሠንጠረዥ «ሀ» የተወሰነውን የቡና አመዳደብ ደንብ መፈጸም አለባቸው ።

፫/ ፈቃድ የተሰጠው እያንዳንዱ ቡና አበጣሪና በደረጃ መዳቢ ስላበጠረውና በደረጃ ስለመ ደበው ስለእያንዳንዱ ክፍል ቡና አንድ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት ። ወደ ውጭ አገር የሚወጣ ቡና የሆነ እንደሆነ በሠንጠረዥ «ለ» በተወሰነው ፎርም መሠረት የወጪ ምስክር ወረቀት ይሰጣል ። ቡናው ለሀገር ውስጥ ጉዳይ የሚውል የሆነ እንደሆነ በሠንጠረዥ «ሐ» በተወሰነው ፎርም መሠረት ለሀገር ውስጥ ጉዳይ የሚያገለግል የም ስክር ወረቀት መስጠት አለበት ።

፬/ እያንዳንዱ የወጪ የምስክር ወረቀት በስድስት ኮፒ ተጽፎ ከዚህ እንደሚከተለው ይከፋ ፈላል ።

ሀ/ መጀመሪያ ቡና አበጣሪውና በደረጃ መዳቢው ዋናውንና የመጀመሪያውን ኮፒ ለቡናው ባለቤት ወይም ሥልጣን ለተሰጠው ወኪሉ መስጠት አለበት ። ከዚያ በኋላ ይህ ዋናውንና የመጀመሪያውን ኮፒ የተወሰነውን ቡና ለገዛው ሰው ተላልፎ በመጨረሻ ዕቃውን በመርከብ ለመላክ ከሚያስፈልጉት ሌሎች ሠነዶች ጋራ በውጭ አገር ቡናውን ለገዛው ሰው ወይም ለእርሱ ባንክ መላክ አለበት ።

ለ/ ሁለተኛውን ኮፒ ቡና አበጣሪና በደረጃ መዳቢው ለራሱ ማስቀረት አለበት ።

ሐ/ ሦስተኛውን ኮፒ ቡና አበጣሪውና በደረጃ መዳቢው ለቡናው ባለቤት ወይም ሥል ጣን ለተሰጠው ወኪሉ መስጠት አለበት ። ከዚያ በኋላ ይህ ሦስተኛው ኮፒ የተወ ሰነውን ቡና ወደሚገዛው ሰው ተላልፎ በመጨረሻ ቡናውን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር በሚልከው ሰው እጅ ይቀራል ።

መ/ አራተኛውንና አምስተኛውን ኮፒ ደግሞ ቡና አበጣሪውና በደረጃ መዳቢው ለቡ ናው ባለቤት ወይም ሥልጣን ለተሰጠው ወኪሉ መስጠት አለበት ። ይህ አራተኛ ውና አምስተኛው ኮፒ የተወሰነውን ቡና ወደሚገዛው ሰው ተላልፎ በመጨረሻ ቡናው ወደ ውጭ አገር በሚላክበት ጊዜ ከጉምሩክ ዲክላራሲዮን ጋር ለጉምሩክ መቅረብ አለበት ።

፭/ ለሀገር ውስጥ ጉዳይ የሚያገለግለው የምስክር ወረቀት በሁለት ኮፒ ተጽፎ የመጀመሪ ያው (ዋናው) ለቡናው ባለቤት ተሰጥቶ ኮፒው በተፈቀደለት በቡና አበጣሪውና በደረጃ መዳቢው እጅ መቀመጥ አለበት ።

፮/ የውጭ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ቡና ሁሉ በጆንያው ላይ የደረጃው ዓይነትና የምስ ክር ወረቀቱ ቁጥር ያለበት ማኅተም እንዲታተምበት ያስፈልጋል ። ከዚህ በኋላ እንደዚህ ያለው ቡና በቀጥታ የቡናው ባለቤት ወደወሰነው ጉምሩክ ጣቢያ መሄድ ይችላል ። ቡናው በቀጥታ ለአንድ የውጭ አገር ገዥ የማይላክ እንደሆነ ወደ ውጭ እስቲወጣ ድረስ በጉምሩክ መጋዘን መቆየት ይችላል ።

፯/ የተፈቀደለት እያንዳንዱ ቡና አበጣሪና በደረጃ መዳቢ ብዛትና ደረጃው እኩል ለሆነ ቡና በእርሱ የተሰጠውን ማናቸውንም የምስክር ወረቀት ኮፒ ሁሉ ከተረከበ በኋላ ባለቤቱ ለይቶ በሚወስነው ልክ እንደገና አዲስ የምስክር ወረቀት ለመስጠት በዚህ ደንብ ተፈቅዶለታል ።

፰/ የተፈቀደለት እያንዳንዱ ቡና አበጣሪና በደረጃ መዳቢ በእርሱ የተሰጠውን የማናቸው ንም የምስክር ወረቀት ኮፒ ሁሉ ከተረከበ በኋላ ባለቤቱ ለይቶ ያስታወቀውን ማናቸ ውንም ደረጃ ለመስጠት ማናቸውንም አስቀድሞ በደረጃ የተመደበውን ቡና እንደገና ለመመደብ በዚህ ደንብ ተፈቅዶለታል ።

www.chilot.me



፲/ የጉምሩክ ሹማምንቶች በዚህ ደንብ በ፳ኛው ክፍልና በሠንጠረዥ «ለ» እንደተወሰነው የወጪ ዕቃ የምስክር ወረቀት ትክክለኛ ኮፒ ከሌለው ማናቸውንም ቡና ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዳይወጣ ለመከልከል በዚህ ደንብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ።

፲፩/ በሚገባ የተሾሙ የኢትዮጵያ ቡና ቦርድ ወኪሎች ከአንድ የተፈቀደለት ቡና አበጣሪና በደረጃ መዳቢ የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ማናቸውንም ቡና ከዚህ ደንብ ጋራ የተስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ በማናቸውም ደንበኛ ጊዜ ወይም ሥፍራ ለመመርመርና ለመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ።

፲፪/ ከዚህ ደንብ ማናቸውንም ቃል የሚተላለፍ ሁሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተወሰነው ቅጣት ይፈጸምበታል ።

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በወ.መ.ሕ. ፲፯/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) አን. ፫፻፶፬ ፣ ፫፻፶፭ ፣ ፫፻፷፬ ፣ ፫፻፷፭ በግ. ሳ. ተሻሻለ ። (እነዚህ አንቀጾች ከሀገር ስለሚወጡ ሸቀጦች እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ ተመሳሳይ ነገሮች የወጡትን ሕጎችና ደንቦች ለሚጥሱ የሚሰጠውን ቅጣት ይገልጻሉ ።)

፲፫/ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም. በቁጥር ፻፷፩ ና በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. በቁጥር ፻፺፯ የወጡት የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች ቀርተው ይህ ተተክቷል ።

፲፬/ ይህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይጸናል ።

## ሠንጠረዥ «ሀ»

## የቡና ጥራትና ደረጃ መለያ ዝርዝር ።

፩/ የእርጥበቱ ክብደት በመቶ አሥራ አንድ ተኩል (11.5.%) ያነሰ ካልሆነ በቀር የተበጠረና በደረጃ የተመደበ ቡና ነው ተብሎ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይቻልም ።

፪/ ከዚህ ጋር በተሰጠው የደረጃ ሠንጠረዥ መሠረት ቡናው የተጣራና በደረጃ የተመደበ ቡና ካልሆነ በቀር የተጣራና በደረጃ የተመደበ ቡና ነው ተብሎ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይቻልም ።

፫/ ከመሻገት ወይም ከበቆልትነት ወይም ይህን በመሳሰለው ምክንያት ጉድለትን ከሚያመጡ ነገሮች ነፃ ካልሆነ በቀር የተበጠረና በደረጃ የተመደበ ቡና ነው ተብሎ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይቻልም ።

፬/ የተጣሩና በደረጃ የተመደቡ ለመሆናቸው የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ቡናዎች ከዚህ በታች እንደተመለከተው ባገር ፣ በደረጃ ተለይተው እንዲመደቡ ያስፈልጋል ።

ሀ/ የሐረር ፣ የሲዳሞ ፣ የጂማ ፣ ወይም የነቀምቴ ቡና ነው እየተባለ መጠራቱን እስከ ዛሬ በንግድ የተለመደውን ሳይለቅ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ቡናው የመጣበትን አገር ለይቶ የሚያመለክት መሆን አለበት ።

ለ/ ለዓይነት በሚቀርበው ሦስት መቶ (፫፻) ግራም ቡና ውስጥ በሚገኘው ጉድለት መጠን በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት የሚወሰን ስምንት (፰) ደረጃ የያዘ የቡና መደብ እንዲኖር ተፈቅዶአል ።

ደረጃ

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | ከ ዜሮ—፫ | ጉድለት |
| ፪ | » ፬—፲፪ | » |
| ፫ | » ፲፫—፳፭ | » |

www.chilot.me



የተጠቀሱትን ዓዋጅና ደንቦች መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘረው ቡና በእኔ ወይም በእኔ ተጠባባቂነት በደንብ የተበጠረና የደረቀ፣ በደረጃም የተመደበና ከመሻገት፣ ከበቀልትነት ወይም ይኸንን በመሳሰለ ምክንያት ጉድለትን ከሚያመጡ ነገሮች ነፃ የሆነና እንዲሁም ደግሞ የእርጥበት ክብደት በመቶ ከአሥራ አንድ ተኩል (11.5%) ያነሰ መሆኑን እያረጋገጥኩ እመሰ ክራለሁ ።

አገር ..........................

ደረጃ ..........................

ይህ የምስክር ወረቀት የቡናውን ክብደት፣ የጆንያውን ቁጥር፣ ምልክትና ቀኑን ሌሎችንም የመለያ ምልክቶች ሁሉ ይጨምራል ።

ፊርማ ................

የፈቃድ ቁጥር ................

## ሠንጠረዥ «ሐ»

### ለሀገር ውስጥ ለሚሆን ቡና ጥራትና ደረጃ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ።

ቡና ስለማበጠርና ስለመመደብ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. በወጣው ዓዋጅ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ደንብ መሠረት እኔ.....................ቁጥሩ ............የሆነ ፈቃድ ወረቀት የተሰ ጠኝ የተጠቀሱትን ዓዋጅና ደንቦች መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን ቡና በእኔ ወይም በእኔ ተጠባባቂነት በደንብ የተበጠረና የደረቀ በደረጃም የተመደበና ከመሻገት፣ ከበቀ ልትነት ወይም ይኸንን በመሳሰለ ምክንያት ጉድለት ከሚያመጡ ነገሮች ነፃ የሆነና እንዲሁም ደግሞ የእርጥበት ክብደት አሥራ አንድ ተኩል (11.5%) ያነሰ መሆኑን እያረጋገጥሁ እመሰክ ራለሁ ።

አገር ......................

ደረጃ ......................

ይህ የምስክር ወረቀት የቡናውን ክብደት፣ የጆንያውን ቁጥር፣ ምልክትና ቀኑን ሌሎችንም የመለያ ምልክቶች ሁሉ ይጨምራል ።

ፊርማ ........................

የፈቃድ ቁጥር ........................

አዲስ አበባ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ. ም.

www.chilot.me



፫/ የቦርዱ ተግባር ከዚህ የሚከተለው ነው ፤

ሀ/ ስለቡና ማበጠርና ደረጃ ስለመስጠት በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. የወጣው አዋጅ መፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚቻልበትን ዘዴ ለማድረግና ይህ ድንጋጌ በሙሉ ተፈጻሚ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን ውሳኔ ለማድረግ ፤

ለ/ ስለቡና ጉዳይ የወጡትን ሕጎች ሁሉ በየጊዜው ለማጥናትና ስለቡና ንግድና እንዱ ስትሪ የወጡት ሕጎች ሁሉ ሊስፋፉ የሚችሉበትን አስተያየት ለንግድና እንዱስትሪ ሚኒስትራችን ማቅረብ ፤

ሐ/ በኢትዮጵያ የበቀለውን ቡና ደረጃ ለማሻሻል ምን ዓይነት ሕግና አስተዳደር ዘዴ ማድረግ እንደሚገባ ለማረጋገጥ ከቡና ተካዮች ፤ ከቡና ነጋዴዎችና ላኪዎች ጋር መመካከር ፤

መ/ የቡና አተካከልና አለቃቀም የሚሻሻልበትን ዘዴ የተለየ አስተያየት በመስጠት ፤ በማስተማርና እየሞከሩ በማሳየት ዘዴ በጹሑፍ ፤ በምክር ወይም በሌላ አኳኋን ለሀገር ውስጥ ጉዳይም ሆነ ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ የቡናውን ዓይነት ለማሻሻል የሚያስፈልገውን ዘዴ ሁሉ ማድረግ ፤

ሠ/ ለቡና ንግድ የሚያገለግለውን የገበያ መረጃና እስታትስቲክ መሰብሰብ ፤

ረ/ የቡና ሥራ በኅብረት የሚሠራበትንና የሚሸጥበትን ዘዴ ማበረታታት ፤

ሰ/ ታክስ በሕግ ስለመወሰን አስተያየት ማቅረብ ፤

፬/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ የተመለከቱትን ተግባሮቹን ለመፈጸም እንዲችል ቦርዱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሥልጣኖች አሉት ።

ሀ/ ደንቦችን ለማውጣት ከተሰጠው ሥልጣን በስተቀር ቡና ስለማበጠርና ደረጃ ስለ መስጠት በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በወጣው አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡት ሕጎች ሁሉ ለንግድና እንዱስትሪ ሚኒስትራችን በተሰጡት ሥልጣኖች ሁሉ ለመሥራት ፤

ለ/ ለሥራው አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሆነውን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመከራየት ፤ ባለንብረት ለመሆን ፤ በንብረቱ ለመገልገልና ለመሸጥ ፤

ሐ/ መጋዘኖችን ፤ ቡና የሚያዘጋጁና የሚያበጥሩ ፋብሪካዎችን ፤ የገበያ ሥፍራዎችን ፤ የመሞከሪያና የመመርመሪያ ጣቢያዎችንና የቡና አተካከልንና አለቃቀምን ዘዴ ለማ ሳያ የሚያስፈልጉትን ሥፍራዎች ለማዘጋጀት ፤ ለመሥራት ፤ ሥራውን ለማካሄድ ወይም ለማከራየት ፤

መ/ ገንዘብ ለመበደርና የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና ለማስያዝ ፤

ሠ/ ስለቡና አተካከልና አለቃቀም ዘዴ የሚያስፈልገውን ምርመራና እንዲሁም ስለቡና አበቃቀል ስለማዘጋጀትና ስለመሸጥ ጉዳይ ነክነት ያላቸውን ማናቸውንም ሥራዎች ለመፈጸም ፤

ረ/ ችሎታ ያላቸውን ቡና አበጣሪዎች በደረጃ መዳቢዎችና እንስፔክተሮች ጭምር ሠራተኞች ለመቅጠር ፤

ሰ/ በአዲስ አበባና በሌሎችም ቡና በሚያበቅሉ ክፍለ ሀገሮች የቡና ገበያዎችን ለይቶ ለመወሰን ፤ ለማቋቋም ፤ ሥራውን ለማካሔድ ፤ ለመቆጣጠርና በእነዚህ ሥፍራዎች ቡና ለማዘጋጀት ፤ ለማከማቸትና ለቡና ንግድ በቂ የሆኑ ማከናወኛዎችን ለማቋቋም ፤

ሸ/ በአዲስ አበባ የቡና መለወጫና መሸጫ ድርጅት ለማቋቋም ።

፭/ ፩/ ቦርዱ ሀሳብ ሲያቀርብና የሚኒስትሮቻችን ምክር ቤት በሐሳቡ ሲስማማበት የንግ ድና እንዱስትሪ ሚኒስትር በየጊዜው ደንብ እያወጣ በኢትዮጵያ ውስጥ የበቀለው ቡና ወደውጭ አገር ሲላክ በቡና ላይ የሚከፈለውን ቀረጥ ለመወሰን ሥልጣን

www.chilot.me



## በከፋ ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| ጂማ | አጋሮ |
| ቦንጋ | ሱንቱ |
| ማጂ | ቶባ |
| ጊምቢ | ሻቤ |
| ሰቃ | ኮንታ |
| ኮማ | ያሲ |
| ገነት | አይቶ |
| ኮላ | ባቡ |
| አቲናጉ | ሲያራ |
| ዎባ | ሴርኮ |
| ሲላሉ | ደብረ ወርቅ |
| | ሸቤ |

## በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| ይርጋ ዓለም | ዲላ |
| ወንዶ | ወናጐ |
| ይርጋ ጨፌ | ሀገረ ሰላም |
| ጨለለቅቱ | ሰዶ (ወላሞ) |
| | ማስሎ |

## በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| ጐሬ | መቱ |
| ኖጳ | ሁሩሙ |
| ሱጴ | ዶረኒ |
| ያዮ | ጋምቤላ |
| | ኩርሙክ |

## በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| ነቀምቴ | ግምቢ |
| ደምቢዶሎ | አንፊሎ |
| ግዳሚ | |

## በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| አርባጉጉ | ሸሸመኔ |
| ሐሰን ዑስማን | አላባ |

## በጐሙ ጐፋ ጠቅላይ ግዛት ፤

| | |
|---|---|
| ጨንቻ | ጊዶሌ |
| ባኮ | ቡልቺ |

## በጉጃም ጠቅላይ ግዛት ፤

ዘጌ

## በበጌምድር ጠቅላይ ግዛት ፤

ጐንደር

አዲስ አበባ ጥር ፳፭ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ.ም.

www.chilot.me



(የሚላክበት ወደብ ወይም አገር ስም)

በኩል ..........................................................................................

በ ፤ ወይም ገደማ ..........................................................................

ቀን ..............................

| ጥሬ ............. | የተቆላ........... | የሚሟሟ......... | ሌላ ዓይነት ............ (ይገለጽ) |
|---|---|---|---|

(ተገቢ በሆነው ሥፍራ የ X ምልክት አድርግ)

| የጭነቱ ምልክት ወይም ሌላ መለያ | ክብደት | የጭነቱ ክብደት | |
|---|---|---|---|
| | ኪ/ግ ወይም በንጥር | ጠቅላላ | የተጣራ |
| | | | |

አስተያየት ..........................................................................................

የአምራቹ አገር ጉምሩክ ማኅተምና የታተመበት ቀን
የምስክር ወረቀት ሰጪው ድርጅት

............................................... ...............................................

የባለሥልጣን ፊርማ ቀን ፤

ይህ የምስክር ወረቀት የተሰጠው በኢንተርናሽናል የቡና ስምምነት መሠረት ሲሆን የዚህ ወረቀት ዋናው ግልባጭ ቡናውን ወደ ውጭ ለመላክ ከሚያስፈልጉት ሠነዶች ጋራ መቅረብ አለበት ይህም ቡናውን ከጉምሩክ ለማውጣትና ለማግባት የሚያስፈልግ ይሆናል ።

## ሠንጠረዥ
## ፎርም ለ

## መልሶ የማውጣት ምስክር ወረቀት ።

መልሶ የሚያወጣው አገር ....................................ቁጥር ..........................
(በባለሥልጣን ተሞልቶ በደብዳቤ የሚጠቀስ)

ከዚህ በታች የተመለከተው ጥሬ ፤ የተቆላ ፤ የሚሟሟ ወይም ሌላ ዓይነት ቡና እላይ በተጠቀሰው አገር ተመልሶ የወጣ መሆኑን አረጋግጣለሁ ።

መርከብ (ወይም ሌላ መጓጓዣ) ..........................................................................

ከ ..........................................................................................

(የወደቡ ወይም ሌላ የማሳፈሪያው ቦታ)

ወደ ..........................................................................................

www.chilot.me



(የሚላክበት ወደብ ወይም አገር ስም)

በኩል ...........................................................................

በ ፤ ወይም ገደማ ...........................................................................

ቀን ..........................................

| ጥሬ ............ | የተቆላ.......... | የሚሚሚ........ | ሌላ ዓይነት ............ (ይገለጽ) |
|---|---|---|---|

(ተገቢ በሆነው ሥፍራ የ X ምልክት አድርግ)

| የጭነቱ ምልክት ወይም ሌላ መለያ | ክብደት | የጭነቱ ክብደት | |
|---|---|---|---|
| | ኪ/ግ ወይም ነጥር | ጠቅላላ | የተጣራ |

የምርት አገር የምስክር ወረቀት ቁጥር ...........................................................

አስተያየት ...........................................................................

በአምራቹ አገር ጉምሩክ ማኅተምና የታተመበት ቀን
የምስክር ወረቀት ሰጭው ድርጅት

.......................................................... ..........................................................

የባለሥልጣን ፊርማ ቀን

ይህ የምስክር ወረቀት የተሰጠው በኢንተርናሲዮናል የቡና ስምምነት መሠረት ሲሆን የዚህ ምስክር ወረቀት ዋናው ግልባጭ ቡናውን ወደ ውጭ ለመላክ ከሚያስፈልጉት ሠነዶች ጋራ መቅረብ አለበት ይህም ቡናውን ከጉምሩክ ለማውጣትና ለማግባት የሚያስፈልግ ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ክፍል ፪

## የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ የሚቋቋምበትና የሚሠራበት አኳኋን ፤

፫/ (፩) በዚህ አዋጅ እንደተጻፈው ውሳኔ የሚሠራ ከዚህ ቀጥሎ የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ እየተባለ የተጠራ የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ ተብሎ የተሰየመ ሥራ ቆሟል ።

(፪) ይህ የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ በዚሁ በሚጠራበት ስም ሊከስ ወይም ሊከሰስ ይችላል ።

፬/ (፩) ይህ የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ ከዚህ ቀጥሎ (ቦርድ) እየተባለ በተጠራው የሥራ አስኪያጆች ተቆጣጣሪነት ይሠራል ። በቦርዱም በኛ የተሾመ ዲሬክተርና ቁጥራቸው ከሁለት የማያንስ አባሎች ይኖሩበታል ።

(፪) ዲሬክተሩ ፤ «ቦርዱ» የሚሰጠውን ጠቅላላ ትእዛዝ እየተከተለ ለ«ቦርዱ» በተሰጠው ሥልጣን ይሠራል ፤ በዚሁ ሥልጣን መሠረት የሚሠራው ነገር ሁሉ «ቦርዱ» እንደ ሠራው ልክ ይቆጠራል ።

፭/ «ቦርዱ» አስፈላጊ የመሰለውን ያህል ሠራተኞች በሥራው ውስጥ ሊቀጥር ይችላል ።

## ክፍል ፫

## የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ አሳብ

፮/ በዚህ አዋጅ እንደተጻፈው ውሳኔ የላስቲክ ሥራ አዘጋጂ የሚሠራቸው ሥራዎች ቀጥሎ እንዳለው ይሆናል ፤

(ሀ) የላስቲክ አረግ መብጣት ፤ እጉን ማጠራቀም ፤ ማዶራጀትና ወደ ውጭ አገር መስደድ።

(ለ) በጠቅላላው የላስቲክ እኽ ለማጠራቀምና ወደውጭ አገር ለመስደድ ።

(ሐ) የላስቲኩን አረግ የሚበጡ ፤ እጉን የሚያጠራቅሙና የሚያዶራጁ ሰዎች ማስተማርና ማሠልጠን ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በተሻሻለው ሕገ መንግሥት ፤ ፲፭/፪ (፲፱፻፵፰) አ. ፻፵፱ አን. ፻፴ (ለ) ፤ ፩ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩—፻፴ በግ. ሳ. ተሻሻለ ። (በዚህ አንቀጽ ሥር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚስማሙትን አስፈላጊና ተገቢ የሆኑትን እርምጃዎች ለመውሰድ ይችላል ።)

፯/ የላስቲክ አረግ እኽ ለመግዛት ከ «ቦርዱ» የተሰጠ የፈቃድ ወረቀት ካልያዘ በተቀር ማንም ሰው ሊገዛ አይችልም ።

## ክፍል ፬

## የ«ቦርዱ» ሥልጣን

፰/ «ቦርዱ» ከአውራጃው ባለሥልጣን ጋራ እየተስማማ ፤

(ሀ) የታሰበው ሥራ ሊፈጸም የሚቻልበትን አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ያደርጋል ፤

(ለ) ሠፈሮችና ሥራው የሚሞከርባቸውን ጣቢያዎች እያደረጀ ያቋቁማል ፤

(ሐ) ለታሰበው ሥራ የሚያስፈልጉት ቤቶች የሚሠሩበትን እንጨት ይቆርጣል ፤

www.chilot.me



፮/ <u>አማካሪ ጉባዔ ፤</u>

፩/ እንስቲትዩት በእርሻ ሚኒስትራችን ወይም በወኪሉ ሊቀ መንበርነት የሚመራ (ከዚህ በኋላ «ጉባዔ» እየተባለ የሚጠራ) አንድ አማካሪ ጉባዔ ይኖረዋል ።

አባሎቹም ከሊቀ መንበሩ ሌላ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ የእንስቲትዩቱ ዲሬክተር (በጸሐፊነትም የሚያገለግል) ፤

ለ/ ከዚህ በታች ካሉት ስድስት መሥሪያ ቤቶች አንዳንድ አባል ፤

፩/ ከገንዘብ ሚኒስቴር ፤
፪/ ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የሶሺያል ሚኒስቴር ፤
፫/ ከንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ፤
፬/ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፤
፭/ ከኢትዮጵያ ቡና ቦርድ ፤
፮/ ከፕላንና የልማት ሚኒስቴር ፤

ሐ/ ጉባዔው በሚፈቅደው መሠረት በአባልነት ወይም በተመልካችነት ተከፋይ የሚሆኑ ፣ ወይም ደግሞ መረጃ ፣ ምክር ወይም እርዳታ የሚሰጡ ተጨማሪ ወኪሎች ፤ ኤክስፐርቶችና አማካሪዎች እንዲሁም በተጨማሪ በአባልነት የሚሠሩ የእርሻ የከብት እርባታና የደን ልማት ሥራ በሚያከናውኑ የግል ድርጅቶች የተወከሉ ሰዎች ፤

፪/ ጉባዔው ብሔራዊ የምርምር ጠቅላላ መምሪያ (ፖሊሲ) በማዘጋጀት በኩል እንስቲትዩቱን ይመክራል ። እንዲሁም የእንስቲትዩቱን ተግባር ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተግባር ጋር በማስማማትና ሥራው በሚገባ እንዲካሄድ እነዚሁ መሥሪያ ቤቶች ከእንስቲትዩቱ ጋር የሚተባበሩበትን መንገድ በመፈለግ ይረዳል ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

በ፳፩/፳፫ (፲፱፻፹፭) ት. ማ. ፵፮ አን. ፪ (፲፯ ፣ ፴፫)፣ (የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር የነበረውን የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የሶሽያል ሚኒስቴር እንዲባል በማድረግና ፣ ቀድሞ በፕላኒንግ ቦርድ ይሠራ የነበረውን ሥራ ሁሉ ለፕላንና የልማት ሚኒስቴር በማዛወር) በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

፯/ <u>ሥልጣን ፤</u>

ዓላማውንና የሥራ ኃላፊነቱን ለመፈጸም እንስቲትዩቱ የሚያስፈልገውን ሥልጣን ይኖረዋል ።

ከዚህ በላይ በጠቅላላ አነጋገር በተመለከተው ሳይወሰን ፤ በተለይ ከዚህ በታች የተዘረዘረው ሥልጣን ይኖረዋል ።

፩/ የሚንቀሳቀስንና የማይንቀሳቀስን ንብረት ለመግዛት ፣ ለመከራየት ፣ በመያዣነት ለመስጠት ወይም በሌላ መንገድ ባለቤት ለመሆን ፤ በርሱም ለመጠቀምና ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ፤

፪/ ለመክሰስና ለመከሰስ ፤

፫/ በኢትዮጵያና በውጭ አገር ከሚገኙ የመንግሥት ፣ መንግሥትን ነክና የግል ከሆኑ ሰዎችና ድርጅቶች ጋር ለመዋዋልና ለመስማማት ፤ እንዲሁም በተጨማሪ የእንስቲትዩቱን ሥራ የሚመለከት የአስተዳደር ፣ የሥራ አካሄድና የመቆጣጠር ልዩ ስምምነት ለማድረግ ፤

www.chilot.me



፩/ ይህ አዋጅ «የ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. የወርቅና የፕላቲንንም ገበያ የመቆጣጠር አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ወርቅ ወይም ፕላቲንም በተፈጥሯቸው እንዳሉ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ገንዘብ መሆናቸው በዚህ ሕግ ተወስኗል ። ከመሬት በላይ ፤ ከመሬት ውስጥ ፤ ወይም በወንዞች ፤ በጅረቶች ፤ በሐይቆች ወይም በሌላ የውሀ ጉድጓድ ውስጥ ፤ ወይም በታች የሚገኘው ወርቅ ወይም ፕላቲን ሁሉ በዚህ ውስጥ ይጨመራል ።

፫/ ከአሥር ወቄት ወርቅ በላይ የተጣራ ፤ ወይም ያልተጣራ ወርቅ ወይም ፕላቲን የወርቅ ወይም የፕላቲን ቁራጭ ፤ የወርቅ ወይም የፕላቲን አፈር ማኖርና ማስቀመጥ ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚገባውን ፈቃድ ካልተቀበለ ሕግ ከማፍረስ ይቆጠራል ።

፬/ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተለየ ፈቃድ ሳይኖረው ወርቅ ወይም ፕላቲን መሆኑን እያወቀ በንግድ ወይም በኰንትራት በማናቸውም አኳኋን ወርቅ ወይም ፕላቲን የሚያመላልስ ፤ ወደ አገር ውስጥ የሚያመጣ ወይም ከአገር ውጭ የሚልክ ይህን ሕግ ከመተላለፍ ይቆጠርበታል ።

፭/ ማናቸውም ሰው በወርቅ እንዳይነጋገድ ስለተከለከለ በእጁ ያለውን ወርቅ በገበያው ዋጋ ለመንግሥት ለመሸጥ ፤ ለጊዜም ባስፈለገው ጊዜ ከመንግሥት ለመግዛት ይችላል ።

፮/ ወርቅ ወይም ፕላቲን በማናቸውም አኳኋን ተደብቆ ወይም በሌላ የንግድ ዕቃ ወይም ነገር ውስጥ ተሸሽጎ ወይም በተሽከርካሪ ወይም በሌላ የማመላለሻ ዕቃ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ የንግዱ ባለቤት ወይም ባለቤቶች ወይም ዕቃው የተገኘበት የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም የሸቀጡ ባለቤት በዚህ ሕግ የተከለከለውን አፍርሷልና ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልግ በዚህ አኳኋን የተገኘው ወርቅ ወይም ፕላቲን ወይም የተገኘበት ተሽከርካሪ ወይም ሸቀጥ ሊያዝ የተገባ ነው ።

፯/ የገንዘብ ሚኒስቴር ሹማምንቶች ይህንን ሕግ ለማስፈጸም ሁል ጊዜ የሚላከውን የንግድ ዕቃ ሊመረምሩ ሥልጣን አላቸው ።

፰/ ባለገንዘቡ ይህንን ሕግ ሲተላለፍ የተያዘው ወርቅ ወይም ፕላቲን ሁሉ የመወረሱ አገባብ ሳይመረምር ይወረሳል ።

ይህን ሕግ ያፈረሰ ማናቸውም ሰው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ።

እንደዚህ ያለ ነገር እንዲገለጥ ለሚያመለክት ሰው ወይም ሰዎች ከመቀጫው ገንዘብ ግማሽ ሊሰጥ ይቻላል ፤ ነገር ግን እንደዚህ ያለ ነገር እንዲገኝ ላመለከቱት የመንግሥት ሹማምንትና ሠራተኞች በተለየ የገንዘብ ሚኒስቴር ካልፈቀደ በቀር ገንዘብ መክፈል አይፈቀድም ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

በ፬/፱ (፲፱፻፴፮) አ· ፫፻፲ ሥን· «ሐ» አን· ፱ (ሀ) ተሻሻለ ፤ በወ.መ.ሕ. ፲፮/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) አን· ፫፻፶፯ ፤ ፫፻፶፰ ፤ ፯፻፵፩ (ባለዋጋ ማዕድኖችን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በሚያዘው ቅጣት በመወሰን) በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

፱/ ይህ አዋጅ ማናቸውንም ሰው ወርቅ ወይም ፕላቲን ያለበት ለሰውነት ጌጥ የሚሆነውን ነገር ወደ ዱቄት ወይም ወደ እንክብልነት ካልተለወጠ በቀር ይህን የመሰለን ጌጥ ከማኖር ከመግዛት ወይም ከመሸጥ አይከለክልም ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ለ/ የዱር አራዊት

፫/፲ (፲፱፻፴፮) አ. ፳፩*

## የዱር አራዊትን ስለመጠበቅ የወጣ

## አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ቀጥሎ ያለውን አውጀናል ።

፩/ ይህ አዋጅ «የ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. የዱር አራዊት ጥበቃ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ «አራዊት» ማለት አዕዋፎችና ዓሶች ፤ የነርሱንም ጫጩቶች ፤ እንቁላላቸውንም ጭምር የሚጠቀልል ቃል ነው ።

«የዱር አራዊት» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ተዘርዝሮ የተወሰነ ማናቸውም ዓይነት የዱር እንስሳ ሁሉ ነው ።

«ከአደን የሚገኝ» ማለት ከማናቸውም ተዘርዝረው ከተመለከቱትና ከተጻፉት እንስሳዎችና አዕዋፎች የሚገኝ ማናቸውም ጥርስ ፤ የዝሆን ጥርስ ፤ አጥንት ፤ ጥፍር ፤ ኮቴ ፤ ቆዳ ፤ ቀንድ ፤ ጠጉር ፤ ላባና በዚህም ከተጠሩት ከማናቸውም አዕዋፍ የተገኘ እንቁላል ነው ።

፫/ ማንም ሰው ቢሆን ከእርሻ ሚኒስትራችን ፈቃድ ካልተቀበለ በቀር ፤ አውሬ ለማደን ፤ ከነነፍሱ ለመያዝ ፤ ወይም ፎቶግራፍ ለማንሣት አይችልም ።

፬/ የእርሻ ሚኒስትራችን ከዚህ በታች ለተጻፉት ደንብ ማውጣት ይችላል ።

ሀ/ እንዳይታደኑ የሚፈለጉትን የአንዳንድ አራዊት ስም በዝርዝር መጻፍና ማስጠበቅ ፤

ለ/ የዱር አራዊት ሊታደኑበት የማይገባውን አንዳንድ መሣሪያ መከልከል ፤

ሐ/ የዱር አራዊት ማደንን ፤ ወይም ከነነፍሳቸው መያዝን መቆጠብ (መወሰን) ፤

መ/ የዱር አራዊት ተቆጥበው የሚኖሩበትን ቦታዎች መከለልና መቆጣጠር ፤

ሠ/ ያንዳንድ የዱር አራዊትን አደን መቀነስ ፤ ወይም በፍጹም መከልከል ፤

ረ/ ከአደን የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር ሺያጭና ግዥ ፤ ወይም መውሰድና ገንዘብ ማድረግ በሚሆነው ረገድ ሁሉ መቆጣጠር ፤ መወሰን ወይም መቀነስና በፍጹም መከልከል ።

ሰ/ የዱር አራዊት እንዳሉ ከነሕይወታቸው ወይም ታድነው የሚገኙት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዳይወጡ ፤ ወይም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ መከልከል ፤ መቆጣጠር ወይም መቀነስና መወሰን ፤

ቀ/ ልዩ ፈቃድ ሳያስፈልግ አጥፊ የሆኑት አራዊት እንዲታደኑ በደንቡ ውስጥ ዘርዝሮ ማውጣት ፤

በ/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተነገሩትን አንቀጾች ባንዳንድ ሰዎችና ነገዶች ላይ እንዳይፈጸምባቸው ማድረግ ፤

---

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፬/፱ (፲፱፻፴፯) አ. ፫፯ ተሻሻለ ፤ በወ. መ. ሕ. ፲፯/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



መ/ ደን በተሟላ አኳኋን ለመጠበቅና ለማስተዳደር አስፈላጊ የሆኑትን የደን ምርመራና ማስተዳደሪያ ጣቢያዎችንና የደን ኤክስፐርቶችን ፣ ቴክኒሽያኖችን ፣ ዘበኞችንና ሌሎች ሠራተኞችን ማሠልጠኛ ድርጅት ለማቋቋምና ለመቆጣጠር ፤

ሠ/ ሰደድ እሳት ፣ የተክል በሽታ ፣ ሥርቆት ፣ ወሰን መጋፋት ፣ ያለአግባብ ማባከን ፣ የሚያስጋ ጉዳት ፣ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥፋትና አደጋ በደኑ ሀብት ወይም በደኑ ውስጥ በሚገኙ የዱር አራዊት ላይ እንዳይደርስ አስፈላጊው ጥበቃ ይደረግ ዘንድ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ፤

ረ/ የጨረታ አቀራረብ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት ከመንግሥት ደን የሚገኘውን የደን ሀብት ሁሉ ዋጋው ከአንድ ሺህ የኢት/ብር ሲበልጥ በጋዜጣና በራዲዮ በማስ ታወቂያ ገልጾ በጨረታ ለመሸጥ የሚችል ሲሆን ፤ ግምቱ እስከ አንድ ሺህ ለሆነው ግን በሐራጅ ብቻ እንዲሸጥ ለማድረግ ፤

ሰ/ የመንግሥት ደን እጅ ካደረገ ከማንም ሰው በሕጉ መሠረት መብቱን ለማዛወር ፤

ሸ/ ከዚህ አዋጅ መንፈስ ጋር ለማስማማት ይቻል ዘንድ ከዚህ በፊት ውል (ኮንሴሽን) ከተሰጣቸው ሰዎች ጋር ውሉ እንዲሻሻል ለመነጋገር ፤

ቀ/ ወደ ደን የሚወስዱ ወይም በደን ውስጥ የሚያስተላልፉ መንገዶች ሁሉ ለመሥራት ወይም እንዲሠሩ ለማድረግ ፤

በ/ በሚኒስትሩ አስተዳዳሪነት ወይም ውል በሚሰጠው ሰው ኃላፊነት በመንግሥት ደን ውስጥ የመዝናኛ ምቾት ፣ እንደ ሕዝብ መናፈሻ ፣ ማረፊያ ቤት ፣ የዱር አራዊት ጥበቃ ክልል ፣ የድንኳን መትከያ ሥፍራ ፣ ይህንና የመሳሰሉትን ሁሉ ለማሠራት ወይም ፤

ተ/ በጠቅላላው ይኸንን አዋጅ በተግባር ላይ ለማዋል የሚበጅ መስሎ የታየውን ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ።

<u>የተጠቀሰው ሕግ</u>

የፍ. ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፱) አን. ፩ሺ፩፻፶፱—፷፯ ።

፰/ <u>ቅጣት ።</u>

ማንም ሰው ፡—

ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ (ሀ) በተመለከተው መሠረት የታወቀውን የወሰን ምልክት ቢያዛውር ፣ ቢያጠፋ ፣ ቢያበላሽ ወይም ቢያሳስት ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ለማስፈጸም ከሚኒስትሩ ወይም ከወከለው ባለሥልጣን ደንበኛ ፈቃድ የያዘ ወይም ፤ በአንቀጽ ፯ (ረ) በተመለከተው መሠረት ካልተፈቀደ በስተቀር ፤ በመንግሥት ደን ውስጥ የሚገኘው ማንኛውም የደን ሀብት የሚይዝ ፤ የሚያዛውር ፤ የሚያዘጋጅ ፤ በጥቅም ላይ የሚያውል ወይም የሚያጠፋ ፤

ሐ/ በመንግሥት ደን ውስጥ በችግኝ ጣቢያዎች ወይም በደን ተክሎች ውስጥ ለግጦሽ ከብት የሚያስማራ ፤ እሳት የሚለኩስ ወይም ይህን የመሳሰለውን ድርጊት ሁሉ የሚያደርግ ፤

መ/ ስለብሔራዊ መናፈሻዎች አያያዝ ፤ አጠባበቅና አኗኗር ፤ በዚህ አዋጅና በተከታታዩ ደንቦች የወጡትን የሚጥስ ፤

ሠ/ በዚህ አዋጅና በተከታታዩ ደንቦች የወጡትን አፈጻጸም የሚተናኮል ወይም የሚያስ ናክል ፤

እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ።

www.chilot.me



፭/ **ስለፈቃድ ።**

ሀ/ ማንኛውም ሰው ከዚህ በኋላ «የደን ሥራ ፈቃድ» እየተባለ የሚጠራውን ፈቃድ ከሚኒስትሩ ወይም ሚኒስቴሩ ከሚወክለው ባለሥልጣን አስቀድሞ ሳይቀበል ፤ ማንኛውንም የደን ሀብት መውሰድ ፤ እጥቅም ላይ ማዋል ፤ መሥራት ወይም ማባከን የለበትም ፤ ስለሆነም የደኑ ባለቤት ፤ ወኪሎችና ጭሰኞች በደኑ ክልል ውስጥ ወይም ከደኑ ቀጥሎ በሚገኝ መሬት ላይ ለሚውል ፤ ለራሳቸው የግል አገልግሎት መጠነኛ የማገዶ እንጨትና ለአጥር ወይም ለቤት ሥራ የሚሆን እንጨት ወይም መጠነኛ የሆነ የደን ሀብት ለቤታቸው ውስጥ አገልግሎት ለመውሰድ ፈቃድ እንዲቀበሉ አይገደዱም ። እንደዚሁም ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ የበቀለውን ለንግድ ተብሉ የተተከለውን ደን ሳይሆን ለግል መጠቀሚያው ራሱ የተከለውን ወይም ያስተከለውን የደን ሀብት ለመቁረጥ ፈቃድ እንዲቀበል አይገደድም ።

ለ/ የደን ሥራ ፈቃድ ጥያቄ በጽሑፍ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡት ደንቦች ውስጥ የሚመለከተውን ዘርዝሮ የሚያስረዳ መሆን አለበት ።

ሐ/ ሚኒስቴሩ ለደን ሥራ ፈቃድ የሚቀርበውን ጥያቄ እንደደረሰው በተቻለ ፍጥነት ለመፍቀድ ወይም ለመከልከል ይችላል ።

መ/ የደን ሥራ ፈቃድ የሚከለከልበት ምክንያት ተገልጾ በጽሑፍ መልሱ መስጠት አለበት ።

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ደን እንዲጠበቅ ካላስፈለገ በስተቀር ፈቃዱን መከልከል አይገባም ።

፩/ አፈሩን ለመጠበቅና ፤ በውሀ ከመጠረግና ከመሸርሸር በድርቀት ከመጐዳት ለመጠበቅ ፤

፪/ ምንጮችና ጅረቶች ሳይቋረጡ እንዲኖሩ ለማድረግ ፤

፫/ የኮረብታዎች አፈር እንዳይናድ ፤ ወይም የባሕር አካባቢ ሲሆን በባሕሩ ውሀ እንዳይሸረሸር ወይም አሸዋው እንዳይጠረግ ለመጠበቅ ፤

፬/ ስለብሔራዊ መከላከያ ጉዳይ ፤ ወይም

፭/ ስለሕዝብ ጤና ጉዳይ ።

ሠ/ የደን ፈቃድ የሚሰጠው ሰው በአንቀጽ ፭ ፊደል (መ) ለተመለከተው ጉዳት ጥበቃ በቂ ዛፎች ትቶ እንዲቆርጥና በተቆረጡትም ዛፎች ምትክ እንዲያለማ የሚያደርግ ሲሆን ብቻ ነው ።

ረ/ የደን ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ለሚያቀርብ ሰው ፤ ሚኒስቴሩ ለማመልከቻው ቢበዛ እስከ ፫ ወር ድረስ መልስ መስጠት አለበት ፤ ይሁን እንጂ እስከ ፫ ወር ድረስ ለጥያቄው መልስ ያልተሰጠው እንደሆነ ጥያቄው እንደተፈቀደ ይቆጠራል ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

የእንግሊዝኛው ቅጂ በአንቀጽ ፭ (ረ) «ቢበዛ እስከ ፫ ወር» የሚለውን «ቢያንስ እስከ ፫ ወር» ይላል ። ግን ያማርኛው ትክክለኛ ይመስላል ።

፮/ **የሚኒስትሩ ሥልጣን ።**

ሚኒስትሩ ፣ የግል ደን የሚለማበትን ፣ የሚጠበቅበትን ፣ የሚተዳደርበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን መቆጣጠርና መምራት አለበት ፤ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከዚህ በታች የተመለከቱትንም ያስፈጽማል ።

ሀ/ በደንቦቹ መሠረት የግል ደን ባለቤት ፤ በልዩ ምልክት ወሰኑ ተለይቶ እንዲታወቅ እንዲያደርግ ለማዘዝ ፤

www.chilot.me



ለ/ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት በተቋቋመው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ የግል ደን እንዲመዘገብ ለማስደረግ ፤ በተጨማሪም ሚኒስቴሩ የሚያቋቁመው የደን ማጠቃለያ ርስት መዝገብ ፤ ማንኛውም የደን መረጃ ሁሉ ተጠቃሎ እንዲመዘገብ ለማስደረግ፤

ሐ/ ባለማቋረጥ ለሁልጊዜ የደን ሀብት ማግኘት ይቻል ዘንድ ዘመናዊ የሆነው ጥበባዊ (ሳይንቲፊካዊ) ዘዴ በሚፈቅደው መሠረታዊ አሠራር በመጠቀም የግለኛ ደን የሚጠበቅበትን ፤ የሚተዳደርበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን የሚገልጽ ከዚህ አዋጅ መሠረት ደንብ እያወጣ ለማስፈጸም ፤

መ/ የደን ሀብት የሚሸጥበትን ወይም የሚሰጥበትን ተገቢ እርምጃ ለመወሰን ፤

ሠ/ ሰደድ እሳት ፤ የተክል በሽታ ፤ ሥርቆት ፤ ወሰን መጋፋት ፤ ያላግባብ ማባከን ፤ የሚያስጋ ጉዳት ወይም ማንኛውም ሌላ ጥፋትና አደጋ በግል ደን ወይም በግል ደን ሀብት ወይም በደኑ ውስጥ በሚገኙ የዱር አራዊት ላይ እንዳይደርስ አስፈላጊው ጥበቃ ይደረግ ዘንድ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ፤

ረ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሚኒስትሩ ፤

፩/ ለመኪና አገልግሎት ፈቃድ ከሚሰጥበት ቦታ እስከ ደኑ ድረስ ባለው ርቀት ደርሶ መልስ በኪሎ ሜትር ዜሮ ፲፭ ማንቲም ፤

፪/ ለሦስት ሰዎች ፤ ኤክስፐርት ፤ ረዳት ኤክስፐርትና ሾፌር አበል በቀን ከሃያ ብር (የኢት/ ፳) ሂሣብ ያልበለጠ የደኑ ባለሀብት ደኑን ሽጦ ከሚያገኘው ጥቅም ለማስከፈል ፤

ሰ/ በጠቅላላው ይህንን አዋጅ በተግባር ላይ ለማዋል የሚበጅ መስሎ የታየውን ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ።

<u>የተጠቀሰው ሕግ</u>

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) አን. ሺ፩፻፶፫—፹፯ ።

፯/ <u>ቅጣት ።</u>

ማንም ሰው ፡—

ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፮ (ሀ) በተመለከተው መሠረት የታወቀውን የወሰን ምልክት ቢያዛውር ፤ ቢያጠፋ ፤ ቢያበላሽ ወይም ቢያሳሳት ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፭ በተመለከተው መሠረት ካልተፈቀደ በስተቀር ፤ በግለኛ ደን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የደን ሀብት የሚወስድ ፤ የሚያዘጋጅ ፤ በጥቅም ላይ የሚያውል ወይም የሚያባክን ፤

ሐ/ በግለኛ ደን ውስጥ በችግኝ ጣቢያዎች ወይም በደን ተክሎች ውስጥ ፤ ለግጦሽ ከብት የሚያሰማራ ፤ እሳት የሚለኩስ ወይም ይህን የመሳሰለውን ድርጊት ሁሉ የሚያደርግ ፤

መ/ የዚህን አዋጅና በተከታታዩ ደንቦች የወጡትን አፈጻጸም የሚተናኮል ወይም የሚያሰናክል ፤

እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ ጥፋቱ በተረጋገጠ ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ።

www.chilot.me



## ፭/ ጥብቅ ደን ተብሎ ስለሚወሰነው መሬት የሚሰጥ ማስታወቂያ ።

ሀ/ ማንኛውም መሬት ጥብቅ ደን ተብሎ እንዲከለል በሚኒስትሩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ በተወሰነ ጊዜ ፤ የመሬቱ ባለቤት ለሆኑ ለማንኛቸውም ሰዎች ሁሉ ውሳኔው በሬኮማንዴ ደብዳቤ ይተላለፍላቸዋል ፤ መሬቱም በሚገኝበት አካባቢ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ይለጠፋል ።

ለ/ ማስታወቂያው የተቻለውን ያህል የተጣራ ሆኖ ጥብቅ ደን ስለሆነው መሬት ሁኔታ ፤ መጠንና ወሰን ፤ የሚለይ መሆን አለበት ። ባለመብቱም ማስታወቂያው ከደረሰበት ወይም ከተለጠፈበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ በዚሁ ቁጥር በፊደል (ሀ) በተመለከተው መሠረት መልስ መስጠት አለበት ። ስለሆነም በግምቱ ስምምነት ባልተገኘ ጊዜ ሚኒስትሩ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሊጠይቅ ይቻላል ።

## ፮/ የማስታወቂያ አቀባበል ።

ሚኒስትሩ ጥብቅ ደን ስለሆነው መሬት አመዳደብ ጉዳይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ፊደል (ለ) በተመለከተው መሠረት በተሾመው በሚኒስትሩ ባለሥልጣን አማካይነት የሚሰጠውን መልስ ተቀብሎ በዘጠና (፺) ቀኖች ውስጥ ውሳኔ ከመስጠት ከባለርስቱ ጋር ተነጋግሮ ተገቢውን ግምት እንዲያገኝ ያደርጋል ። ወይም በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት መሬቱን ለማዛወር ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ።

የተጠቀሰው ሕግ

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ.፪ (፲፱፻፶፪) አን. ሺ፬፻፳—፹፯ ።

## ፯/ የጥብቅ ደን አስተዳደርና አጠቃቀም ።

ጥብቅ ደን በሚኒስትሩ ተቆጣጣሪነት ሥር መተዳደርና ጥቅም ላይ መዋል አለበት ፤ ማንም ሰው በሚወጡት ደንቦችና ይህን በሚመለከተው ሕግ መሠረት ካልሆነ በስተቀር ፤ ከጥብቅ ደን ውስጥ የደን ሀብት መውሰድ ፤ ማዘጋጀት ፤ ማባከን ወይም ጥቅም ላይ ማዋል አይችልም ፤ ከሚኒስትሩም በሚሰጠው መምሪያ መሠረት ባለርስቱ በወሰደው የደን ሀብት ምትክ መልሶ ለማልማት ከቻለ የደኑን ሀብት ለመውሰድና እጥቅም ላይ ለማዋል አይከለከልም ።

## ፰/ የሚኒስትሩ ሥልጣን ።

ሚኒስትሩ ጥብቅ ደን የሚለማበትን ፤ የሚጠበቅበትን ፤ የሚተዳደርበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን መቆጣጠርና መምራት አለበት ፤ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከዚህ በታች የተመለከቱትንም ያስፈጽማል ፡—

ሀ/ የጥብቅ ደን ባለቤት ፡ በልዩ ምልክት ወሰኑ ተለይቶ እንዲታወቅ እንዲያደርግ ለማዘዝ ፤ የመንግሥት የሆነውን ጥብቅ ደን ግን በልዩ ምልክት ወሰኑ ተለይቶ እንዲታወቅ ያደርጋል ፤

ለ/ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት በተቋቋመው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ የጥብቅ ደን እንዲመዘገብ ለማስደረግ ፤ በተጨማሪም በሚኒስትሩ በሚቋቋመው የደን ማጠቃለያ ርስት መዝገብ ኑሮ ማንኛውም የደን መረጃ ሁሉ ተጠቃሎ እንዲመዘገብ ለማስደረግ ፤

ሐ/ ባለማቋረጥ ለሁልጊዜ የደን ሀብት ማግኘት ይቻል ዘንድ ዘመናዊ የሆነው ጥበባዊ (ሳይንቲፊካዊ) ዘዴ በሚፈቅደው መሠረታዊ አሠራር በመጠቀም ፤ የጥብቅ ደን የሚጠበቅበትን ፤ የሚተዳደርበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን የሚገልጽ ደንብ አያወጣ ለማስፈጸም ፤

www.chilot.me



## የተጠቀሰው ሕግ

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) እን. ሺ፩፻፺፭ ።

፭/ **የሥራ ፕላን ።**

፩/ ስለደኑ በተዘጋጀውና ሚኒስቴሩ በተስማማበት የሥራ ፕላን መሠረት ካልሆነ በቀር ግለኛ ደን ጥቅም ላይ መዋል አይችልም ።

፪/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፩ በተመለከተው መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ የደን ክፍል ደኑን ይመረምርና የሥራውን ፕላን ለማዘጋጀት አስፈላጊውን የደን መረጃ ይሰበስባል።

፮/ **የልማት ግዴታ ።**

፩/ የደን ሥራ ፈቃድ የጠየቀ ሰው የእርሻ ሚኒስቴር በሚሰጠው መምሪያ መሠረት ደኑን መልሶ ለማልማትና ለማከባከብ አስቀድሞ ግዴታ ካልገባ የደን መቁረጥ ፈቃድ አይሰጠውም ።

፪/ ከዚህ በላይ በቁጥር ፮ በንዑስ ክፍል (፩) በተመለከተው መሠረት የገባውን ግዴታ ያልፈጸመ ባለፈቃድ እንደሁኔታው የተሰጠው ፈቃድ የሚወሰድበት ከመሆኑም በላይ ሌላ የዛፍ መቁረጥ ፈቃድ አይሰጠውም ።

፯/ **የደን ሥራ ፈቃድ ።**

የደን ክፍል የሥራውን ፕላን እንዳጸደቀና ፈቃድ ጠያቂው ደኑን መልሶ ለማልማት ግዴታ እንደገባ ወዲያውኑ የደን ሥራ ፈቃድ ይሰጣል ፤ የደኑ ሥራ ፈቃድም በያመቱ ጥቅም ላይ የሚያውሉትን የደን ክፍሎችና የሚነሉትን የደን ሀብቶች ዓይነትና ብዛት ለይቶ መወሰን አለበት ።

፰/ **በሚቆረጡት ዛፎች ላይ ምልክት ስለማድረግ ።**

የሥራ ፕላን በተዘጋጀለትና ፈቃድ በተሰጠበት ደን ውስጥ የሚገኙት ዛፎች አስቀድሞ በእርሻ ሚኒስቴር የደን ክፍል ምልክት ካልተደረገባቸው በቀር ለመቁረጥ አይቻልም ።

፱/ **መሸጥ ።**

በደን ሥራ ፈቃድ መሠረት የደን ሀብቶችን የሚሸጡ የደን ሀብት ሻጭዎች ሁሉ የደኑን ሥራ ፈቃድ ቁጥር ፤ የተሸጠውን የደን ሀብት ዓይነትና ብዛት የሚያመለክት ደንበኛ ደረሰኝ ለገዥው መስጠት አለባቸው ። ማንም ሰው የደን ሥራ ፈቃድ ቁጥር የሚያመለክት ደረሰኝ ሳይኖረው የደን ሀብቶችን ጥቅም ላይ ማዋል ፤ ማዘጋጀት ወይም ይዞ መገኘት የለበትም ።

፲/ **የዛፎችን አቆራረጥ መመርመር ።**

የደን ክፍል የዛፎችን አቆራረጥ በየጊዜው ይመረምራል ።

፲፩/ **መዝገቦች ።**

ግለኛ ደን ጥቅም ላይ የሚያውል ማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ ያዋለውን የደን ሀብት የሚመዘግብበት ትክክለኛና የተሟላ መዝገብ ማቋቋም አለበት ።

፲፪/ **ቅጣት ።**

እነዚህን ደንቦች የተላለፈ ወይንም በቁጥር ፪፻፳፭/፲፱፻፶፯ ዓ.ም. በወጣው የግለኛ ደን አጠባበቅ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከተውን የጣሰ ማንኛውም ሰው ጥፋት እንዳጠፋ ተቆጥሮ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኋላ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

www.chilot.me



ለ ፫ ድምር (ለ.፩+ለ.፪)

| ለሳንቃ የሚሆን ግንድ<br>የዛፉ ዓይነት ፡ ቁጥር ፡ ሜ/ኩብ ፡ | ለልብጥ እንጨት የሚሆን ግንድ<br>የዛፉ ዓይነት ፡ ቁጥር ሜ/ኩብ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

ሐ/ በዚህ ሪፖርት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የሰነጠቀው እንጨት ልክ

| ለሳንቃ የሚሆን ግንድ<br>የዛፉ ዓይነት ፡ ቁጥር ፡ ሜ/ኩብ ፡ | ለልብጥ እንጨት የሚሆን ግንድ<br>የዛፍ ዓይነት ፡ ቁጥር ፡ ሜ/ኩብ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

መ/ በዚህ ሪፖርት የተጠቀሰው ጊዜ መጨረሻ ላይ የተከማቸው እንጨት (መ=ሀ+ለ—ሐ)

| ለሳንቃ የሚሆን ግንድ<br>የዛፉ ዓይነት ፡ ቁጥር ፡ ሜ/ኩብ ፡ | ለልብጥ እንጨት የሚሆን ግንድ<br>የዛፉ ዓይነት ፡ ቁጥር ፡ ሜ/ኩብ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

ቀን ________________ ሪፖርቱ ትክክለኛ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ

ፊርማ ________________

አዲስ አበባ መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ.ም.

መ/ መናፈሻዎች

፳፰/፩ (፲፱፻፳፭) ት. ፶፬

## የሸዋ ብሔራዊ ክልል ለማቋቋም የወጣ ትእዛዝ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ የዱር አራዊት ይጠበቁ ዘንድ እነዚህ የሐገሪቱ የተፈጥሮ ሀብቶች በቂ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችሉ ብሔራዊ ክልሎችን ማቋቋም በማስፈለጉ ፤

በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በኤረርና ከረዩ አውራጃ የመጀመሪያውን ብሔራዊ ክልል ማቋቋም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፳፯ኛው አንቀጽ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤታችን የመከረበትን ተመልክተንና ፈቅደን ቀጥሎ ያለውን አዘናል ።

www.chilot.me



፩/ **አጭር አርእስት ።**

ይህ ትእዛዝ «የ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. የአዋሽ ብሔራዊ ክልል ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ **የአዋሽ ብሔራዊ ክልል መቋቋም ።**

በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በኤረርና ከረዩ አውራጃ ውስጥ የሚገኘው ሥፍራ በሚከተለው ጂኦግራፊካል ሎንግቲውድና ላቲቲውድ መሠረት እንዲታወቅ ተወስኗል ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ/ | መነሻው | ከዜሮ ፫ ዲግሪ | ፶፮ ደቂቃ | ሰሜን ሎንግቲውድ |
| | | ፴፱ » | ፶፫ » | ምሥራቅ ላቲቲውድ |
| ለ/ | | ዜሮ ፱ » | ፵፰ » | ሰሜን ሎንግቲውድ |
| | | ፴፱ » | ዜሮ፯ » | ምሥራቅ ላቲቲውድ |
| ሐ/ | | ዜሮ ፱ » | ዜሮ፯ » | ሰሜን ሎንግቲውድ |
| | | ፵ » | ዜሮ፫ » | ምሥራቅ ላቲቲውድ |
| መ/ | እስከ | ዜሮ ፫ » | ፶፫ » | ሰሜን ሎንግቲውድ |
| | | ፵ » | ፶፫ » | ምሥራቅ ላቲቲውድ |

፫/ **አስተዳደር ።**

የአዋሽ ብሔራዊ ክልል መብቱ የተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤታችን በሚያወጣቸው ሕጎችና ደንቦች (ሁሉ) መሠረት ይተዳደራል ።

፬/ **ትዕዛዝ ስለሚጸናበት ጊዜ ።**

ይህ ትዕዛዙ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ፳፭/፳፱ (፲፱፻፷፮) አ. ፪፻፵፩

## የኅብረት ሥራ ማኅበሮችን ስለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ፍላጐታቸው ተመሳሳይ በሆነ ሰዎች መካከል የቁጠባንና የእርስ በርስ መደጋገፍን ልምድ የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማኅበሮች የሚቋቋሙበት ደንበኛ መሠረት መጣል እጅግ አስፈላጊና ሕዝባችንም የኅብረትን ሥራ ጥቅም የተረዳው መሆኑን ተገንዝበን ፤

ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግሥታችን አንቀጽ ፹፰ና ፺፰ መሠረት የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶቻችን መክረውበት ያቀረቡልንን ተመልክተንና ፈቅደን የሚከተለውን አውጀናል ።

### ማውጫ ።

### ክፍል ፩ መቅድም ።

አንቀጽ

፩/ አጭር አርእስት
፪/ ስለተሻረ ሕግ
፫/ ትርጓሜ
፬/ የኅብረት ሥራ ማኅበር ዓላማና ግብ
፭/ ሬጅስትራር

### ክፍል ፪ ስለማኅበሮች አቋቋምና አመዘጋገብ ።

፮/ የማኅበሮች ዓይነት
፯/ የማኅበር ስም
፰/ ስለማኅበር አቋቋም
፱/ ማመልከቻ ።
፲/ ስለአመዘጋገብ
፲፩/ ስለማኅበሮች በሕግ የሰውነት መብት ማግኘት
፲፪/ የመተዳደሪያ ደንቦችን ስለማሻሻል
፲፫/ ስለኃላፊነት መለወጥ ስለሀብትና ኃላፊነት ማዛወር ፣ ስለመነጣጠል ፣ ወይም ስለመቀላቀል

### ክፍል ፫ የማኅበር አባሎች መብታቸውና ግዴታቸው ።

፲፬/ ማኅበርተኛ መሆን ስለሚችሉ ሰዎች
፲፭/ በስም ማኅበርተኛ ስለሚሆኑ ሰዎች ፣
፲፮/ ስለማኅበርተኞች መዝገብ
፲፯/ ማኅበርተኛ ተገቢውን እስኪከፍል በማኅበርተኛነት መብት መጠቀም ስላለመቻሉ
፲፰/ ስለድምፅ አሰጣጥ
፲፱/ የአንድ ማኅበርተኛ ድርሻ የተወሰነ ስለመሆን
፳/ ድርሻን ወይም ጥቅምን ማዛወር የተወሰነ ስለመሆኑ

www.chilot.me



፳፩/ ማኅበርተኛ ሲሞት ጥቅሙን ስለማዛወር
፳፪/ ቀድሞ ማኅበርተኛ ስለነበረ ወይም በሞት ስለተለየ ማኅበርተኛ ኃላፊነት
፳፫/ ስለማኅበሩ የበላይ ባለሥልጣን
፳፬/ ስለጠቅላላ ጉባዔ
፳፭/ ስለልዩ ጠቅላላ ጉባዔ
፳፮/ ስለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
፳፯/ ሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስለመቆጣጠር
፳፰/ መዛግብትንና ሠነዶችን ስለመረከብ

## ክፍል ፫ የማኅበሮች ልዩ መብት ።

፳፱/ ማኅበሮች ስለሚያቀርቡት ክስ ቅድሚያ ስለመስጠት
፴/ የማኅበርተኛን ድርሻ ወይም ጥቅም አንድ ማኅበር ለመቀበል ወይም ለማገዳደር ስለመቻሉ
፴፩/ ድርሻን ወይም ጥቅምን ለማስከበር ወይም ለመሸጥ ስለአለመቻሉ
፴፪/ ስለመንግሥት እርዳታና ከታክስ ነፃ ስለመሆን

## ክፍል ፬ የማኅበሮች ንብረትና ገንዘብ ።

፴፫/ የማኅበር ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ
፴፬/ ስለተጣራው ትርፍ አከፋፈል
፴፭/ ገንዘብ በሥራ ላይ ስለማዋል
፴፮/ ስለመበደር ወሰን
፴፯/ ስለማበደር ወሰን

## ክፍል ፭ ስለሂሳብ ቁጥጥር ፣ ስለምርመራ ፣ ስለፍተሻ ።

፴፰/ ስለሂሳብ ቁጥጥር
፴፱/ ስለምርመራ
፵/ ስለመዝገብ ፍተሻ
፵፩/ የሂሳብ ቁጥጥርን የምርመራንና የመዝገብን ፍተሻ ሥራ ስለሚፈጽም ሰው ሥልጣን
፵፪/ በማኅበር ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ያደረገውን ሰው ስለማስከፈል

## ክፍል ፮ ስለእርቅ ።

፵፫/ ለእርቅ (ለአርቢትሬሽን) ስለሚቀርቡ ክርክሮች
፵፬/ ክርክርን ስለመጨረስ

## ክፍል ፯ ስለማኅበሮች መፍረስና ሂሳባቸውን ስለማጣራት ።

፵፭/ ስለማኅበር መፍረስ
፵፮/ ስለሂሳብ አጣሪ
፵፯/ የሂሳብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር
፵፰/ ከመዝገብ ስለመሠረዝ

www.chilot.me



፮/ «ሹም» ማለት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ፣ ም/ፕሬዚዳንት ፣ ጸሐፊው ፣ ሥራ አስኪያጁ ፣ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባል ፣ ግምጃ ቤቱ ፣ አስተዳዳሪው ፣ ወይም ሂሳብ አጣሪ ውና በደንብ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማኅበሩን ሥራ ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሰው ጭምር ማለት ነው ።

፯/ «የተወሰነ» ማለት በደንብ የተወሰነ ማለት ነው ።

፰/ «ሬጅስትራር» ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ መሠረት የሚሾመው ሰውና የሬጅ ስትራሩ ሥልጣን ተሰጥቶት የሚሠራ ማንኛውም ሌላ ሰው ጭምር ማለት ነው ፤

፱/ «ደንብ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፣ ሚኒስትሩ የሚያወጣቸው ደንቦች ማለት ነው ።

፲/ «የመተዳደሪያ ደንብ» ማለት የአንድ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብና ማሻሻያዎቹን ሁሉ ጭምር ማለት ነው ።

፲፩/ «ማኅበር» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የኅብረት ሥራ ማኅበር ማለት ነው ።

፲፪/ «ኃላፊነቱ የተወሰነ ማኅበር» ማለት ማኅበሩ ሲፈርስ ስለማኅበሩ ግዴታ ማኅበርተ ኞቹ ኃላፊ የሚሆኑት ከያዙት ድርሻው ውስጥ ላልከፈሉት ሂሳብ ብቻ ሲሆን ፣ ወይም ከድርሻቸው በላይ እንከፍላለን ብለው በመተዳደሪያ ደንባቸው በወሰኑት መጠን ኃላፊ ሲሆኑ ነው ።

፲፫/ «ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ማኅበር» ማለት ማኅበሩ ሁሉ ሲፈርስ ማኅበርተኞቹ እያንዳ ንዳቸው ፣ ወይም በአንድነት ሆነው ለማኅበሩ ግዴታዎች ሙሉ ኃላፊ የሚሆኑበት ማኅበር ማለት ነው ።

፲፬/ «ልዩ ውሳኔ» ማለት በስብሰባው ላይ ከተገኙት ማኅበርተኞች ውስጥ ሁለት ሦስ ተኛዎቹ በድምፅ ብልጫ ያጸደቁት ወይም በመተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠ ረት ቁጥራቸው ከዚህ በላይ የሆነ (ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሆነ) በቂ አባሎች (ኮረም) ያጸደቁት ውሳኔ ማለት ነው ።

፬/ <u>የማኅበሮች ዓላማና ግብ ።</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋሙ ማኅበሮች ዋና ዋና ዓላማዎችና ግቦች ፤

፩/ ለብድር ገንዘብ የሚከፈለውን ወለድና ሌላም ወጭ በመቀነስ ፤

፪/ ለሥራ ውጤትና (ፕሮዳክሽን) አላቂ ነገሮችን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የመሣሪያ ዎችንና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ ፤

፫/ አንድ ሰው ብቻውን ቢሠራ ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በኅብረት በመካፈል የያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ በመቀነስ ፤

፬/ የቴክኒክን ዕውቀት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ዘዴዎችን እንዲስፋፋ በማ ድረግ ፣ ወይም ፤

፭/ ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉትን ዘዴዎች ሁሉ በመከተል ፤

በኅብረት ሥራ መሠረታዊ ሐሳብና ለኅብረ ሰብ ትክክለኛ ፍትሕ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የኑሮ ደረጃንና ሥራን ከፍ ለማድረግ ፣ እንዲሁም በተሻለ ዘዴ የሥራን ውጤት (ፕሮዳክሽን) ለማግኘት እንዲቻል ማድረግ ነው ።

፭/ <u>ሬጅስትራር ።</u>

፩/ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ ለሚገኙ የኅብረት ሥራ ማኅበሮች አንድ ሬጅስትራርና ም/ሬጅስትራር በእኛ ይሾማሉ ። እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የኅብ

www.chilot.me



ረትን ሥራ በሚገባ ለማካሄድ ሬጅስትራሩን የሚረዱ ረዳት ሬጅስትራሮች በሚኒ ስትሩ ይሾማሉ ። እነዚህም ሰዎች በሙሉ በመንግሥት ሥራ ላይ ብዙ ጊዜ የቆዩና የሥራ ልምድ ያላቸው ቢቻልም በኅብረት ሥራ አስተዳደር ውስጥ የሠሩ ሰዎች ይሆናሉ ።

፪/ ም/ሬጅስትራርና ረዳት ሬጅስትራሮቹ በደንብ ተወስኖ በሚሰጣቸው የሬጅስትራሩ ሥልጣን መሠረት የሬጅስትራሩን ተግባሮች ይፈጽማሉ ።

## ክፍል ፪ ስለማኅበሮች አቋቋምና አመዘጋገብ ።

### ፯/ የማኅበሮች ዓይነት ።

ማኅበሮች በሁለት ዓይነት የተከፈሉ ይሆናሉ ።

፩/ ማኅበርተኞቹ ከአሥር ያላነሱ የግል ሰዎች ሲሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ማኅበር ይባ ላል ።

፪/ ከግል ሰዎችና በሕግ የሰው መብት ካላቸው ማኅበርተኞች ሌላ በተጨማሪ በትንሹ አንድ ሌላ ማኅበርተኛ የሆነበት የኅብረት ሥራ ማኅበር ሁለተኛ ደረጃ ማኅበር ተብሎ ይጠራል ። የእንደዚህ ያለውም ማኅበር ኃላፊነት ሁልጊዜም የተወሰነ ይሆ ናል ።

### ፰/ የማኅበር ስም ።

፩/ «የኅብረት ሥራ ማኅበር» የተባለው ቃል በማንኛውም ማኅበር ስም ላይ ተጽፎ መገኘት አለበት ።

፪/ «ኃላፊነቱ የተወሰነ» የተባለው ቃል ኃላፊነቱ በተወሰነ በማንኛውም ማኅበር ስም ላይ መጻፍ አለበት ።

፫/ የማንኛውም ማኅበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የማኅበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማን ኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት ። እንዲሁም በማኅበሩ ማስታወቂያዎች ፤ ደብዳቤ ዎች ሌሎች መግለጫዎችና ማኅበሩ ፤ ወይም በማኅበሩ ስም በሚፈረሙ የባንክ ሠነዶች ላይ ሁሉ መጻፍ አለበት ።

### ፱/ ስለማኅበር አቋቋም ።

፩/ አንድ ማኅበር የሚመሠረተው የመሥራች ጠቅላላ ስብሰባ በሚሰጠው ውሳኔ ነው ። መሥራቾች ስለማኅበሩ አቋምና አመዘጋገብ በተለይም ፤

ሀ/ ስለመተዳደሪያ ደንብ የቀረበውን ረቂቅ ያጸድቃሉ ።

ለ/ ስለማስመዝገቢያ የሚያስፈልገውን ማመልከቻ ያዘጋጃሉ ።

፪/ የአንድ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብ የሚዘጋጀው በደንብ በሚወሰነው መሠረት መሆን አለበት ። ይኸውም የመተዳደሪያ ደንብ ሚኒስቴሩ ለዓይነት እንዲያገለግል ያዘጋጀው የመተዳደሪያ ደንብ ሲኖረው ይኸንኑ ሊከተል ይችላል ።

### ፲/ ማመልከቻ ።

፩/ ማኅበርን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ ሬጅስትራሩ በሚወስነው ዓይነት ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት ። በማመልከቻውም ላይ በተለይ ፤

www.chilot.me



ሀ/ የማኅበሩ ስም ግቡና ሥራው የሚካሄድበት ሥፍራ ፤

ለ/ ለማቋቋም የታሰበው ማኅበር ኃላፊነት የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ መሆኑን ፤

ሐ/ የመጀመሪያ ደረጃ ማኅበር ሲሆን ፤ ከአሥር ያላነሱ አመልካቾች ስምና እነዚህም ሰዎች በአንቀጽ ፲፬ መሠረት ማኅበርተኛ ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለጫዎች ፤

መ/ የተዘጋጀው መተዳደሪያ ደንብ ሁለት ግልባጭና ፤

ሠ/ በደንብ በሚወሰነው መሠረት አስፈላጊ የሆኑት ሌሎች ዝርዝሮች ይገለጻሉ ።

፪/ ማመልከቻውን እያንዳንዱ የግል ማኅበርተኛና በሕግ የሰው መብት የተሰጠው ድርጅት ሕጋዊ ወኪል መፈረም አለበት ።

፫/ እንዲቋቋም የታሰበው ማኅበር በኤኮኖሚ ረገድ የሚያወጣው መሆኑን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሬጅስትራሩ መጠየቅ ይችላል ።

፲/ ስለአመዘጋገብ ።

፩/ ሬጅስትራሩ አንድ ማኅበር ለማስመዝገብ የቀረበለት ማመልከቻ በዚህ አዋጅና በደንቦቹ የተመለከተውን የፈጸመና የማኅበሩም ዓላማና ግብ በአራተኛው አንቀጽ መሠረት መሆኑን ካረጋገጠ ፤ ማኅበሩንና የመተዳደሪያ ደንቡን መዝግቦ ማኅበሩ የተመዘገበ ለመሆኑ ማስረጃ እንዲሆን ራሱ የፈረመበትን የምስክር ወረቀት ለአመልካቾች ይሰጣል ። በዚህም የምስክር ወረቀት ላይ ማኅበሩን የተመዘገበበትን ቀን ይጠቅሳል ።

፪/ በዚህ አንቀጽ (፲) በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ማኅበር መመዝገቡን በማረጋገጥ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ማኅበሩ ከመዝገብ ካልተሰረዘ በቀር ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል ።

፲፩/ ስለማኅበሮች በሕግ የሰውነት መብት ማግኘት ።

አንድ ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን እንሥቶ በሕግ የሰው መብት ይኖረዋል ።

፲፪/ የመተዳደሪያ ደንቦችን ስለማሻሻል ።

፩/ አንድ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንቡን በዚህ አዋጅ በደንብ በሚወሰነውና በመተዳደሪያ ደንቡ በተመለከተው መሠረት ማሻሻል ይችላል ።

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሬጅስትራሩ ቀርቦ ያልተመዘገበ ማንኛውም ማሻሻያ ሊጸና አይችልም ። ማኅበሩ ያዘጋጀው የማሻሻያ ረቂቅ በሁለት ኮፒ ለሬጅስትራሩ ቀርቦለት ማሻሻያው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ (፬) ከተመለከተው ዓላማና ግብ ጋር ተስማሚ መሆኑን ሬጅስትራሩ ካረጋገጠ በኋላ ፤ ማሻሻያውን ስለማጽደቁ ማስረጃ ይሆን ዘንድ በአንዱ ኮፒ ላይ ፈርሞና ያጸደቀበትን ቀን ጠቅሶ ለማኅበሩ ይሰጣል ። ይህም ማሻሻያው በተመለከተው ቀን በሕጉ መሠረት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሆናል ።

፲፫/ ስለኃላፊነት መለወጥ ፤ ስለሀብትና ኃላፊነት ማዛወር ፤ ስለመነጣጠል ወይም ስለመቀላቀል ።

፩/ አንድ ማኅበር አስፈላጊ የሆኑትን ግዴታዎች ሁሉ በመፈጸም ልዩ ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ በ፲፫ኛው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በማስመዝገብ ፤

ሀ/ የማኅበርተኞቹን ኃላፊነት ዓይነትና መጠን መለወጥ ፤

www.chilot.me



ለ/ ሀብቱንና (እሴት) ኃላፊነቱን በጠቅላላው ፡ ወይም በከፊል ለሌላ ማኅበር ማዛ ወር ፤

ሐ/ ማኅበሩን ነጣጥሎ ሁለት ወይም ከዚህ በላይ እንዲሆን ማድረግ ፤

መ/ ከአንድ ፡ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ማኅበሮች ጋር በመቀላቀል አዲስ ማኅ በር ማቋቋም ይችላል ።

፪/ ማኅበሩ ለአበዳሪዎቹና ውሳኔው በተሰጠበት ቀን በስብሰባው ላልነበሩ ማኅበርተ ኞች ውሳኔው እንዲደርስ ያደርጋል ። እንዲሁም ለአበዳሪዎቹና ለማኅበርተኞቹ ውሳ ኔው ከደረሳቸው ቀን አንሥቶ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ አለመስማማታቸውን ካልገለጹ በቀር በውሳኔው እንደተስማሙ እንደሚቆጠር ያስታውቃቸዋል ።

፫/ ሬጅስትራሩ እንዲህ ያለውን ውሳኔ የሚመዘግበው ፤

ሀ/ አበዳሪዎችና ማኅበርተኞቹ ሁሉ በውሳኔው የተስማሙ ፤ ወይም በዚህ አንቀጽ ፲፫ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት እንደተስማሙ የሚቆጠር ሲሆን ፡ ወይም ፤

ለ/ ያልተስማሙ ማኅበርተኞች ሂሳባቸው ተከፍሎዋቸው ከማኅበር የወጡ ሲሆኑ ፤ ወይም በውሳኔው ያልተስማሙ አበዳሪዎች ሂሳባቸው የተከፈለ ሲሆን ፡ ወይም ለእነዚህ ላልተስማሙበት ማኅበርተኞች ፤ ወይም አበዳሪዎች ሂሳባቸውን ለመ ክፈል በሬጅስትራሩ አስተያየት በቂ የሆነ ዋስትና የተሰጠ ሲሆን ነው ።

፬/ እንዲህ ያለው ውሳኔ ሲመዘገብ ፤

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ፲፫ ፤ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) መሠረት የተወሰነ ማንኛውም የማዛወር ተግባር ወዲያውኑ ይፈጸማል ።

ለ/ ሀብቱንና ኃላፊነቱን ያዛወረው ማኅበር ፤ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ የቀድሞው ማኅበር ፡ ወይም ማኅበሮች ተገቢ ሲሆን ከመዝገብ ይሰረዛሉ ።

ሐ/ ሬጅስትራሩ ተገቢ በሆነ በማንኛውም ጊዜ የልዩ ልዩ ውሳኔውን ኮፒ ትክክ ለኛነቱንና በፊርማው በማረጋገጥ ቀንና ዓመተ ምሕረት ጽፎበት ለማኅበሩ ይሰጣል ።

ይኸውም ልዩ ውሳኔ ሬጅስትራሩ በማረጋገጫው ላይ በገለጸው ቀን ለመሰጠ ቱና በሕጉ መሠረት ለመወሰኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል ።

## ክፍል ፫ የማኅበር አባሎች መብታቸውና ግዴታቸው ።

### ፲፬/ ማኅበርተኛ መሆን ስለሚችሉ ሰዎች ።

ማንኛውም ፤

፩/ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ችሎታ ያለው ሰው ወይም ፤

፪/ ሌላ ማኅበር ፡ ወይም ፤

፫/ ሚኒስቴር ፤ በቻርተር የተቋቋመ የመንግሥት ድርጅት ወይም ሌላ የመንግሥት መሥ ሪያ ቤት ካልሆነ በቀር ማኅበርተኛ መሆን አይችልም ።

### ፲፭/ በስም ማኅበርተኛ ስለሚሆኑ ሰዎች ።

፩/ በአንድ ማኅበር ማንኛውም ሰው ፡ ወይም በሕግ የሰው መብት የተሰጠው ድርጅት በስም ማኅበርተኛ እንዲሆን ማኅበሩ መፍቀድ ይችላል ።

www.chilot.me



፪/ በዚህ አዋጅ ወይም በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ሌላ ውሳኔ ከሌለ በቀር ፤ በስም ማኅበርተኛ የሆነ ሰው መብት ፤ ግዴታና ኃላፊነት እንደሌለው ማኅበርተኛ ነው ። ሆኖም በስም ማኅበርተኛ የሆነ ሰው ፤ በማንኛውም አኳኋን ከማኅበሩ ሀብት ፤ ወይም ትርፍ ድርሻ ሊኖረው አይችልም ።

፲፯/ ስለማኅበርተኞች መዝገብ ።

እያንዳንዱ ማኅበር መዝገብ ይኖረዋል ። ይኸውም መዝገብ «የማኅበርተኞች መመዝገቢያ» ተብሎ ይጠራል ። በመዝገቡም ውስጥ ፤

፩/ የእያንዳንዱ ማኅበርተኛ ስም ፤ አድራሻ ፤ ሥራ ፤

፪/ ማንኛውም ሰው ማኅበርተኛ የሆነበት ቀን ወይም ማኅበርተኛነቱን ያቋረጠበት ቀን ፤

፫/ የእያንዳንዱ ማኅበርተኛ ድርሻ ፤

፬/ በመተዳደሪያ ደንቡ አስፈላጊ ሆኖ የተወሰነው ማንኛውም ሌላ ዝርዝር ይጻፋል ።

፲፰/ ማኅበርተኛ ተገቢውን እስኪከፍል በማኅበርተኛነት መብቱ መጠቀም ስላለመቻሉ ።

ማንኛውም ማኅበርተኛ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት ለማኅበርተኛነት የሚያስፈልገውን ካልከፈለ ፤ ወይም በማኅበሩ ውስጥ ጥቅም ከሌለው በቀር በማኅበርተኛነቱ መብት ሊጠቀም አይችልም ።

፲፱/ ስለድምፅ አሰጣጥ ።

፩/ ማንኛውም ማኅበርተኛ ምንም ያህል ድርሻ ቢኖረው በማኅበሩ ስብሰባ ላይ የሚሰጠው ድምፅ አንድ ብቻ ነው ። ሆኖም ፤

ሀ/ በስም ማኅበርተኛ የሆነ ሰው ድምፅ አይኖረውም ፤

ለ/ በሕግ የሰው መብት የተሰጠው ድርጅት ፤ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ የተወሰነለት ድምፅ ብዛት ይኖረዋል ። ለያንዳንዱም ድምፅ አንዳንድ ሰው ይወከላል ።

፪/ በዚህ በ፲፱ኛው አንቀጽ ፤ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) እና በአንቀጽ ፳፫ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በቀር እያንዳንዱ ማኅበርተኛ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምፅ መስጠት ይኖርበታል ።

፲፱/ የአንድ ማኅበርተኛ ድርሻ የተወሰነ ስለመሆኑ ።

አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ማኅበር ውስጥ ማንኛውም ማኅበርተኛ ከተከፈለው ጠቅላላ ካፒታል አንድ አምስተኛ ($^1/_5$) በላይ የሆነ ድርሻ አይኖረውም ።

፳/ ድርሻን ፤ ወይም ጥቅምን ማዛወር የተወሰነ ስለመሆኑ ።

፩/ ማንኛውም ማኅበርተኛ የሚደገርገው የድርሻ ፤ ወይም የጥቅም ማዛወር ፤ ማኅበርተኛው ፤

ሀ/ ድርሻውን ወይም ጥቅሙን በትንሹ ለአንድ ዓመት ጊዜ የያዘ ካልሆነ ፤

ለ/ ድርሻውን ወይም ጥቅሙን ያስተላለፈው ለሌላ ማኅበርተኛ ካልሆነና ፤

ሐ/ ድርሻውን ፤ ወይም ጥቅሙን ማስተላለፉን ከሚቴው የፈቀደ ካልሆነ በቀር ፤ ሊጸና አይችልም ።

www.chilot.me



፪/ በመጀመሪያ ደረጃ ማኅበር ውስጥ ማንኛውም የድርሻ ፤ ወይም የጥቅም ማዛወር የሚፈጸመው በአንቀጽ ፲፱ በተወሰነው መሠረት ነው ።

## ፳፩/ ማኅበርተኛ ሲሞት ጥቅሙን ስለማዛወር ።

፩/ አንድ ማኅበርተኛ ሲሞት ድርሻው ፤ ወይም ጥቅሙ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሟቹ በኑዛዜ ስጦታ ላደረገለት ወራሽ ፤ ወይም ሟቹ የኑዛዜ ፈቃዱን ባልተወ ጊዜ ፤ ያለኑዛዜ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል ። ይኸውም የሚሆነው ሕጋዊ ወራሹ ማኅበርተኛ ሲሆን ፤ ወይም ማኅበርተኛ እንዲሆን ሲፈቀድለት ነው ።

፪/ የሟቹ ሕጋዊ ወራሽ ማኅበርተኛ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ማኅበርተኛ መሆን ያልፈለገ እንደሆነ ወይም ማኅበሩ በማኅበርተኛነት ያልተቀበለው እንደሆነ ፤ የሟቹ ድርሻ ወይም ጥቅም ሂሳብ ይከፈለዋል ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የአንድ ማኅበርተኛ ጠቅላላ ድርሻ ወይም ጥቅም በአንቀጽ ፲፱ መሠረት ከተወሰነው በልጦ የተገኘ እንደሆነ ፤ ብልጫ ሆኖ የተገኘው ሂሳብ ለማኅበርተኛው ይከፈላል ።

፬/ በዚህ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ተወስኖ የተላለፈውን ወይም የተደረገውን ክፍያ የማንኛውም ሌላ የሦስተኛ ሰው ጥያቄ አይሽረውም ።

## ፳፪/ ቀድሞ ማኅበርተኛ ስለነበረ ፤ ወይም በሞት ስለተለየ ማኅበርተኛ ኃላፊነት ።

ቀድሞ ማኅበርተኛ የነበረ ሰው ኃላፊነት ወይም በሞት የተለየ ማኅበርተኛ ሀብትና ንብረት ማኅበርተኛነቱን ካቋረጠበት ወይም ከሞተበት ቀን አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት በማኅበርተኛነቱ ለማኅበሩ ግዴታና ኃላፊነት ተጠያቂ ሆኖ ይቆያል ።

ሆኖም ፤

፩/ በዚህ በተባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማኅበሩ እንዲፈርስ ትእዛዝ የተሰጠ እንደሆነ ፤ የማኅበሩ መፍረስ ሥርዓት እስኪፈጸም ድረስ ኃላፊነቱ ይቀጥላል ወይም ፤

፪/ በማኅበሩ የመጀመሪያ ሂሳብ ቁጥጥር ትርፍ ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ይህ ኃላፊነቱ ይቀራል ።

## ክፍል ፬ የማኅበር አካሎች ።

## ፳፫/ ስለማኅበሩ የበላይ ባለሥልጣን ።

የማኅበሩ የበላይ ባለሥልጣን የማኅበርተኞቹ ጠቅላላ ጉባዔ ነው ። ሆኖም በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ የተፈቀደ ሲሆን ፤ ይህ ሥልጣን ቁጥራቸው አነስተኛ ስሆኑ የማኅበርተኞቹ ወኪሎች ሲበዙና እነዚህም ሰዎች በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ሊሠሩ ይችላሉ ።

## ፳፬/ ስለጠቅላላ ጉባዔ ።

፩/ የማኅበርተኞቹ ጠቅላላ ጉባዔ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል ። ጉባዔውም ፤

ሀ/ የዓመቱን ሪፖርትና የኦዲተሩን ሪፖርት መርምሮ ይወስናል ።

ለ/ ስለተጣራ ትርፍ አደላደል ይወስናል ።

www.chilot.me



ሐ/ ለሚከተለው ዓመት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያዘጋጀውን የሥራ ፕሮግራም መርምሮ ይወስናል ።

መ/ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን አባሎች ይመርጣል ፤

በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚቀርቡለትን ማናቸውንም ሌሎች ጉዳዮች ይወስናል ።

፪/ አስፈላጊ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የማኅበርተኞቹ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲደረግ ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጥሪ ማድረግ ይችላል ።

፳፩/ ስለልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ።

፩/ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ቁጥራቸው በቂ የሆነ ማኅበር ተኞች ወይም ሬጅስትራሩ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲደረግ ጥያቄአቸውን በጽሑፍ ባቀረቡ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጥሪ ያደርጋል ።

፪/ በዚህ በ፳፩ኛ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፤ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሆን ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ ፤ ሬጅስትራሩ ራሱ ጥሪውን ያደር ጋል ። ይኸውም ጉባዔ በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ እንደተጠራ ይቆጠራል ።

፳፪/ ስለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ።

፩/ በእያንዳንዱ ማኅበር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይኖራል ። የኮሚቴውም አባሎች ቁጥርና አመራረጥ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል ።

፪/ ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ የሚሰበሰብበት ጊዜና ሁኔታ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል ።

፫/ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ይወ ሰናል ፤ በተለይም ፤

ሀ/ የስብሰባውን ቃለ ጉባዔና የሥራውንም አመራር በጽሑፍ ይይዛል ።

ለ/ መዛግብትንና ሂሳብን በደንብ በተወሰነው መሠረት ይይዛል ።

ሐ/ ስለማኅበሩ ሥራ የዓመት ሪፖርትና ፤ እንዲሁም የሚከተለውን ዓመት የሥራ ፕሮ ግራም አዘጋጅቶ ለጠቅላላው ጉባዔ ያቀርባል ።

መ/ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጉባዔዎችን ይጠራል ።

ሠ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፩ ፤ እንዲሁም በደንቡና በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከተጣራ ትርፍ ውስጥ ለመጠባበቂያ ገንዘብና ሌላም የመ ዋጮ ገንዘብ እንዲኖር ያደርጋል ።

ረ/ በጠቅላላው ጉባዔ የሚሰጠውን ውሳኔ ሁሉ ይፈጽማል ።

፳፫/ ሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስለመቆጣጠር ።

፩/ ሬጅስትራሩ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ተግባሩን በሚገባ አለመፈጸሙን የደ ገመ ፤ ወይም አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መሥራት ያልቻለ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ፣ ወይም በማ ኅበሩ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ፤ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባሎች ፤ ወይም ወኪሎቻቸው በተወሰነ ቀን ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ ሊልክና ፤ በቀጠሮውም ቀን መዝገቦችንና ሠነዶችን አቅርበው ቀጠሮ ስለ ተደረገበት ጉዳይ እንዲያስረዱ ለማድረግ ይችላል ።

፪/ ሬጅስትራሩ በዚህ አንቀጽ ፳፫ ፤ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አስፈላጊውን ጥሪ አድርጐ ጉዳዩን እስኪሰማ ድረስ በሚፈጀው ጊዜ ምክንያት በማኅበሩ ንብረትና ሀብት ላይ ፤ ወይም በማኅበሩ ጠቅላላ ደህንነት ላይ የማይታረም ጉዳት ይደርሳል

www.chilot.me



## ክፍል ፯ ስለሂሳብ ቁጥጥር ፣ ስለምርመራ ፣ ስለፍተሻ ።

፴፰/ ስለሂሳብ ቁጥጥር ።

፩/ ሬጅስትራሩ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማንኛውንም ማኅበር ሂሳብ እሱ የሚወክለው ሰው እንዲቆጣጠር ያደርጋል ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተቆጣጣሪውን የአገልግሎት ወጪ ማኅበሩ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ፴፰ ፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ ቁጥጥር ማኅበሩ ያልተከፈለ ዕዳ እንዳለበት ይህን ዕዳውንና የዋሬ ገንዘቡን ሂሳብ ፣ የዋስትናውን ሠነዶችና የሀብቱን ዋጋ ፣ ኃላፊነቱንም ጭምር መመርመርና ማረጋገጥ ነው ። ሆኖም የቁጥጥሩ ሥራ በነዚሁ ብቻ አይወሰንም ።

፫/ የኦዲተሩ ሪፖርት በደንብ በሚወሰነው መሠረት ፣ ለሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ይቀርባል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በእንግሊዝኛው ቅጂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ የሚገኘው «--- ሆኖም የቁጥጥሩ ሥራ በነዚሁ ብቻ አይወሰንም ።» የሚለው ዐረፍተ ነገር አይገኝም ።

፴፱/ ስለምርመራ ።

፩/ ሬጅስትራሩ ራሱ ወይም እሱ የሚወክለው ሰው ስለአንድ ማኅበር አቋም ስለሥራው አፈጻጸም ስለገንዘቡ ሁኔታ መመርመር ይችላል ።

፪/ እንዲሁም የዚሁ ዓይነት ምርመራ ፣

ሀ/ ጉዳዩ የሚመለከተው ማኅበር አባል የሆነበት ሁለተኛ ደረጃ ማኅበር ሲጠይቅ ፤

ለ/ ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎች አብዛኛዎቹ ሲጠይቁ ፤

ሐ/ ከጠቅላላው የማኅበርተኞች ቁጥር ከአንድ ሦስተኛ ($^1/_3$) ያላነሱ አባሎች ሲጠይቁ መደረግ አለበት ።

፵/ ስለመዝገብ ፍተሻ ።

፩/ ሬጅስትራሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ራሱ ወይም እሱ የሚወክለው ሰው የማኅበሩን መዛግብቶች እንዲፈተሽ ማድረግ ይችላል ።

፪/ እንዲሁም የዚህ ዓይነት ፍተሻ የሚደረገው በማኅበሩ ላይ ገንዘብ ያለው ሰው ፍተሻው እንዲደረግለት ሲጠይቅና ።

ሀ/ ማኅበሩ ገንዘቡን መክፈል የነበረበት ቀን አልፎ ባለገንዘቡም እንዲከፈለው ጠይቆ በቂ ጊዜ ከሰጠ በኋላ ፣ ያልተከፈለው ለመሆኑ ለሬጅስትራሩ ሲያረጋግጥ ፤

ለ/ ለመዝገቡ ፍተሻ አስፈላጊ የሆነው ወጪ ሬጅስትራሩ በሚወስነው መሠረት አመልካች ሲያስቀምጥ ነው ።

፵፩/ የሂሳብ ቁጥጥር የምርመራንና የመዝገብ ፍተሻን ሥራ ስለሚፈጽም ሰው ሥልጣን ። በአንቀጽ ፴፰ ፣ ፴፱ና ፵ መሠረት የሚሠራ ማንኛውም ሰው በአንቀጽ ፶፪ና በደንብ በሚወሰነው መሠረት ሥራውን ለመፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል ።

www.chilot.me



ሐ/ ስለማንኛውም ሹም አመራረጥ የሚነግ ክርክር ይሆናሉ ፡፡ ሆኖም በነዚህ ብቻ አይወሰንም ፡፡

፺፩/ ክርክርን ስለመጨረስ ፡፡

፩/ ሬጅስትራሩ በአንቀጽ ፺ መሠረት ክርክር ሲቀርብለት ፤

ሀ/ ክርክሩን ራሱ መወሰን ፤ ወይም

ለ/ እሱ ለሚመርጣቸው አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ለሆኑ አስታራቂዎች ውሳኔ እንዲሰጡበት መምራት ይችላል ፡፡

፪/ ሬጅስትራሩ በዚህ አንቀጽ ፺፩ ፣ በንዑስ አንቀጽ ፩/ (ለ) መሠረት ያደረገውን ምርጫ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ሠርዞ እሱ ራሱ ክርክሩን መወሰን ይችላል ፡፡

## ክፍል ፱ ስለማኅበሮች መፍረስና ሂሳባቸውን ስለማጣራት ፡፡

፺፪/ ስለማኅበር መፍረስ ፡፡

፩/ አንድ ማኅበር ፤

ሀ/ እንዲፈርስ ልዩ ውሳኔ ሲያደርግ ፤ ወይም

ለ/ የመጀመሪያ ደረጃ ማኅበር ሆኖ የማኅበረተኞቹ ቁጥር ከዐሥር በታች ሲሆን ፤ በዚህ አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት መፍረስ አለበት ፡፡

፪/ አንድ ማኅበር ፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ፣ ፴፱ ወይም ፵ የሂሳብ ቁጥር ፣ ምርመራ ወይም ፍተሻ ከተደረገ በኋላ ፣ ሬጅስትራሩ ማኅበር ሊፈርስ የሚገባው ሆኖ ያገኘው እንደሆን ፤ ወይም ፤

ለ/ ማኅበሩ ከተመዘገበበት ቀን አንሥቶ ባንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥራውን ያልጀመረ ፤ ወይም ጀምሮ ያቆመ እንደሆነ ፤ ሬጅስትራሩ ማኅበሩን በዚህ አንቀጽ ፺፪ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሊያፈርስ ይችላል ፡፡

፫/ አንድ ማኅበር የሚፈርስ ሲሆን ፣ ሬጅስትራሩ በደንብ በሚወስነው ፎርም መሠረት እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ በጽሑፍ ትእዛዝ ይሰጣል ፡፡ ሆኖም ሬጅስትራሩ የነገሩን ሁኔታ ተመልክቶ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማኅበሩ መፍረስና የሂሳቡ መጣራት ከመፈጸሙ በፊት ትእዛዙ እንዲቀር ማድረግ ይችላል ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ፺፪ ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከቱት ምክንያቶች ፣ አንድ ማኅበር እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ በዚሁ በተባለው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው ትእዛዝ ተፈጻሚ የሚሆነው ትእዛዙ ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ ነው፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ፺፪ ፣ በንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከቱት ምክንያቶች አንድ ማኅበር እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ በዚሁ በተባለው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በተሰጠ ትእዛዝ ላይ ትእዛዙ ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይግባኝ ማለት ይቻላል ፡፡ በተባለው ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ሳይባል የቀረ እንደሆነ ትእዛዙ የሁለቱ ወር ጊዜ ካለቀበት ቀን አንሥቶ ይፈጸማል ፡፡ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ የተባለ እንደሆነ ግን ፤ ይግባኙ ካልጸደቀ በስተቀር ፤ ትእዛዙ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፡፡

፺፫/ ስለሂሳብ አጣሪ ፡፡

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሬጅስትራሩ ትእዛዝ ሲሰጥ ፤ ሂሳብ አጣሪው ይሾማል ፡፡ አስፈላጊ ሆኖም ቢገኝ የሂሳብ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ ከማኅበሩ ሂሳብ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል ፡፡

www.chilot.me



፪/ ሂሳብ አጣሪውም እንደተሾመ የማኅበሩን ማንኛውንም መዛግብት ፣ ሠነዶችና ንብረቱን በሙሉ ፤ እንዲሁም ማኅበሩ ከሌላ ሰው ላይ የሚጠይቀውን ወይም የማኅበሩ የሆነውንና መብቱ የሚመስለውን ሁሉ ይረከባል ። እንዲሁም በማኅበሩ ንብረትና በሚጠይቀው በማኅበሩ መብት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውንና ምቹ ሆኖ ያገኘውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል ።

፫/ አንድ ማኅበር እንዲፈርስ የተሰጠው ትእዛዝ በይግባኝ የተሻረ እንደሆን መዛግብቱ ፣ ሠነዶቹ ፣ ንብረቱና ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ ሁሉ ለማኅበሩ ይመለሳል ።

## ፺፯/ የሂሳብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር ።

፩/ ሂሳብ አጣሪው በሬጅስትራሩ መሪነትና ተቆጣጣሪነት የሂሳብ ማጣራቱን ሥርዓት ከፍጻሚ ለማድረስ አስፈላጊው ሥልጣን ይኖረዋል ። ሥራውን በሚገባ ለመፈጸም አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል ። በተለይም

ሀ/ ከማኅበሩ የሚጠየቀውን ዕዳ መርምሮ በቅድሚያ የሚከፈለውን ይወስናል ።

ለ/ ማኅበርተኛ የቀድሞ ማኅበርተኛ ፣ ወይም በሞት የተለየ ማኅበርተኛ ሀብትና ንብረት ፣ ወይም ሕጋዊ ወራሹ ፣ ወይም ማንኛውም የማኅበሩ ሹም ወይም የቀድሞው ሹም ለማኅበሩ ሀብትና ንብረት ሊያደርጉ የሚገባቸውን መዋጮ ይወስናል ።

ሐ/ የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበስባል ።

መ/ ሬጅስትራሩ በሚፈቅደው ፕላን መሠረት ሀብቱንና ንብረቱን ያከፋፍላል ።

ሠ/ የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ ለመፈጸም አስፈላጊ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ የማኅበሩን ሥራ ያካሄዳል ።

ረ/ በሕግ በሚቀርቡ ክሶች ለማኅበሩ ተወክሎ ይቀርባል ።

ሰ/ ማንኛውም ሰው በማኅበሩ ውስጥ ማኅበርተኛ ፣ የቀድሞ ማኅበርተኛ ወይም በሞት የተለየ ማኅበርተኛ ተጠሪ መሆኑን ይወስናል ።

ሸ/ ለሂሳብ ማጣራት ሥራ አስፈላጊነቱ ማኅበርተኞችን ይሰበስባል ።

፪/ የሂሳብ ማጣራቱ ሥርዓት እንደተፈጸመ ፣ ሂሳብ አጣሪው ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለሬጅስትራሩ ያቀርባል ። የማኅበሩን መዝገቦችና ሠነዶች ሁሉ ሬጅስትራሩ በሚያዘው ሥፍራ ያስቀምጣል ።

## ፺፰/ ማኅበሩን ከመዝገብ ስለመሠረዝ ።

የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ እንደተፈጸመ ማኅበሩ የተመዘገበበት የምስክር ወረቀት ለሬጅስትራሩ ይመለሳል ። ሬጅስትራሩም ማኅበሩን ከመዝገብ ይሰርዝና ማኅበሩም ከመዝገብ ከተሠረዘበት ቀን ጀምሮ የሌለ ይሆናል ።

## ክፍል ፲ ስለውሳኔ አሰጣጥ ፣ ስለይግባኝና ስለአፈጻጸም ።

## ፺፱/ ውሳኔ ስለሚሰጥበት መሠረት ።

በዚህ አዋጅ ውስጥ ግልጽ የሆነ ሌላ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት ስለሚቀርብ ክርክር በፍርድ ፣ ወይም በአስተዳደራዊነት መልክ የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ፣ ትእዛዝ ወይም ብይን በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ከታየ በኋላ መሆን አለበት ።

www.chilot.me



፪/ «የሕብረት ሥራ ዓመት» ሲባል ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ቀን ያለው ጊዜ ማለት ነው ።

፫/ «የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ» ሲባል የማኅበሩን ሥራ እንዲመሩ አደራ የተጣለባቸው ሰዎች ማለት ነው ።

፬/ «ሂሳብ አጣሪ» ሲባል በአዋጁ አንቀጽ ፵፮ መሠረት በሬጅስትራሩ የተሾመ ሰው ማለት ነው ።

፭/ «ማኅበርተኛ» ሲባል በአንድ ማኅበር ውስጥ ማኅበርተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅትና በስም ማኅበርተኛ እንዲሆን የተፈቀደለት ሰው ጭምር ማለት ነው ።

፮/ «ሚኒስቴር» ሲባል የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው።

፯/ «የተጣራ ትርፍ» ሲባል ክፍያ በሙሉ ከተደረገ በኋላ ተርፎ ለማኅበርተኞቹ እንደ የድርሻቸው የሚደለደለው ገንዘብ ማለት ነው ።

፰/ «አዋጅ» ሲባል ስለኅብረት ሥራ ማኅበር በቁጥር ፪፻፵፩/፲፱፻፶፰ ዓ. ም. የወጣው አዋጅ ማለት ነው ።

፱/ «ሬጅስትራር» ሲባል በአዋጁ በአንቀጽ ፭ መሠረት የሚሾም ሰውና የሬጅስትራሩ ሥልጣን ተሰጥቶት የሚሠራ ማንኛውም ሌላ ሰው ጭምር ማለት ነው ።

፲/ «የመተዳደሪያ ደንብ» ሲባል የአንድ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብና ማሻሻያዎችን ሁሉ ጭምር ማለት ነው ።

፲፩/ «ማኅበር» ሲባል በአዋጁ በአንቀጽ ፲ መሠረት የተመዘገበ የኅብረት ሥራ ማኅበር ማለት ነው ።

<u>የተጠቀሰው ሕግ</u>

የፍ. ሕ. ሥ. ሥ. ፳፭/በተ. የ. ፫ (፲፱፻፶፰) ድ. ፶፱ ።

## ፭/ የመተዳደሪያ ደንቦች ዝርዝር ሁኔታዎች ።

፩/ የማኅበር የመተዳደሪያ ደንቦች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝሮች መያዝ አለባቸው ።

ሀ/ የማኅበሩን ስምና አድራሻ ፤

ለ/ የማኅበሩ ሥራ የሚካሄድበትን ሥፍራ ፤

ሐ/ የማኅበሩን ግብ ፤

መ/ ገንዘብ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ፤

ሠ/ የማኅበርተኞቹ የኃላፊነት ዓይነትና ልክ ፤

ረ/ ማኅበሩ ሊበደር የሚችለውን ገንዘብ ልክና ለዚህም ገንዘብ ስለሚከፈለው ወለድ መጠን ፤

ሰ/ ከማኅበርተኞች ስለሚሰበሰበው የመግቢያና ሌሎች ክፍያዎች ፤

ሸ/ የማኅበሩ ገንዘብ በሥራ ላይ የሚውልበት ዓላማ ፤

ቀ/ ስለማኅበርተኛነት መብትና ኃላፊነት እንዲሁም ማኅበርተኛ ለመሆን ስለሚያበቁ ሁኔታዎች ፤

በ/ ማኅበርተኞች ከማኅበር ስለሚወገዱበት መንገድ ፤

ተ/ ስብሰባ የሚደረግበትና ማስታወቂያ የሚወጣበት ሁኔታ ፤

www.chilot.me



ቸ/ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎችና እንዲሁም ሌሎች ሹማምንት ስለሚሾሙበትና ስለሚሻሩበት ሁኔታ ፤ ስለሥልጣናቸውና ስለተግባራቸው ፤ እንዲሁም በሥራ ላይ ስለሚቆዩበት ጊዜ ፤

ኀ/ ንግድ ፤ ግዥ ፤ ሽያጭ ፤ ተቀማጭ ንብረት ፤ መበደርና ማበደር እንደዚሁም ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ስለሚመሩበት ሁኔታ ፤

ነ/ ስለተጣራ ትርፍ አከፋፈል ፤

ኘ/ በሬጅስትራሩ የተወሰኑትን ጉዳዮች ማዘጋጀትና ማቅረብ ፤

አ/ «የትምህርት ማስፋፊያ መዋጮ» ስለመፍጠርና ፤

ከ/ ሹም ወይም ሹማምንት በሠነዶች ላይ እንዲፈርሙና በማኅበሩ ስም እንዲከሰሱና እንዲከሱ እንዲሁም ሌሎች ሕግ ጠቀስ ጉዳዮችን እንዲከታተሉ ሥልጣን ስለመስጠት ።

፪/ የማኅበር የመተዳደሪያ ደንቦች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝሮች መያዝ ይችላሉ ።

ሀ/ ከማኅበር መውጣት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ፤

ለ/ ማኅበርተኞች ከማኅበር ሲወጡ ፤ ማኅበርተኞች ለመሆን በማይችሉበትና በሞቱ ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ ፤

ሐ/ የአንድ ማኅበርተኛ ድርሻ ወይም ጥቅሙን ለማዛወር ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ፤

መ/ ሠራተኛ ስለሚቀጠርበት ዘዴ ፤ ስለሥራ ሁኔታዎችና ማኅበሩ ደመወዝ ስለሚከፍላቸው ሹማምንትና የሠራተኞች ደመወዝ ስለመወሰን ፤ ማሻሻል ወይም ማስተካከልና እንዲሁም ሊወሰድባቸው ስለሚገባው የቅጣት ሥርዓት ፤

ሠ/ ለማኅበርተኞችና ለማኅበሩ ሠራተኞች ስለሚከፈለው ጉርሻ ልክና ስለአከፋፈሉም ሁኔታ ፤

ረ/ ለማኅበሩ አገልግሎቱን ለሰጠ ማኅበርተኛ ስለሚከፈለው አበል ልክና ስለአከፋፈሉም ሁኔታ ፤

ሰ/ የመተዳደሪያ ደንቦችን ለማሻሻል ፤ ማኅበሮችን ለመከፋፈል ፤ ለማቀላቀልና ለማፍረስ ስለሚደረጉት ልዩ ውሳኔዎችና እንዲሁም ልዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ስለሚያስፈልጉ ሌሎች ጉዳዮች የድምፅ ብልጫ ወይም ምልአተ ጉባኤ ስለመወሰን ፤

ሸ/ ለማኅበርተኞች ብድር ወይም በቅድሚያ ገንዘብ ስለሚሰጥበት ሁኔታ በተለይም ፤

፩/ ብድር ወይም በቅድሚያ የሚሰጥ ገንዘብ የሚሰጥበትን ምክንያት ፤

፪/ ለአንድ ማኅበርተኛ በብድር የሚሰጠው ገንዘብ ልክ ወይም ሰብልን በማስያዝ በቅድሚያ የሚሰጠው ገንዘብ በአካባቢው ገበያ ዋጋ መጠን ከመቶ ምን ያህል እንደሚሆን ፤ ወይም በጠቅላላው በብድርና በቅድሚያ ገንዘብ ሊሰጥ ስለሚቻልበት ፤

፫/ ስለማኅበርተኞች በሚሰጠው ብድር ላይ ስለሚከፈለው ወለድ ልክና

፬/ ብድርንና በቅድሚያ የሚሰጥ ገንዘብን በማይገባ ሥራ ላይ ማዋል ስለሚያስከትለው መቀጮ ፤

ቀ/ ብድሩ ወይም በቅድሚያ የተሰጠው ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ስለሚራዘምበት ወይም ስለሚታደስበት ሁኔታ ፤

www.chilot.me



በ/ የመተዳደሪያ ደንቡን ተላልፎ በተገኘ ማኅበርተኛ ላይ ስለሚጣልበት የመቀጫ ሁኔታ ፤

ተ/ ማናቸውንም የማኅበሩን ዕዳ ያለመክፈል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት ።

፫/ በአንቀጽ ፫ ፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተመለከቱት ዝርዝሮች ሌላ ለማኅበሩ አቋምና ለሥራው አመራር አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንቦችን ውስጥ ለማግባት ይቻላል ።

## ፮/ ለማስመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ።

ለሬጅስትራሩ የሚቀርበው የመመዝገቢያ ማመልከቻ ከዚህ ደንብ ጋር በአባሪ (ሀ) በተያዘው የኅ.ሥ.ማ.ቅጽ ፩ መሠረት መሆን አለበት ።

## ፯/ ስለመመዝገቢያ የምስክር ወረቀት ።

ሬጅስትራሩ አንድ ማኅበር ሲመዘገብ መመዝገቡን በማረጋገጥ በአባሪ (ለ) በተያዘው የኅ.ሥ.ማ.ቅጽ ፪ መሠረት የምስክር ወረቀት ይሰጣል ።

## ፰/ የማኅበር መዝገብ ።

፩/ የማኅበሮች የመተዳደሪያ ደንቦችና ምዝገባን የሚመለከቱ ዝርዝር ሁኔታዎች የሚሰፍሩበት «የማኅበር መዝገብ» ተብሎ የሚጠራ መዝገብ ሬጅስትራሩ ይይዛል ወይም በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ እንዲያዝ ያደርጋል ፤

፪/ በማኅበር መዝገብ ውስጥ የሚሰፍሩት አዲስ ጉዳዮች ሁሉ በሬጅስትራሩ ወይም በእርሱ መሪነት ከሰፈሩ በኋላ ሬጅስትራሩ ይፈርምባቸዋል ፤

፫/ በማኅበር መዝገብ ውስጥ በሚደረገው ማናቸውም ለውጥ ወይም እዝል ወይም ስርዝ ሬጅስትራሩ ምልክት ማድረግ አለበት ።

## ፱/ የመተዳደሪያ ደንቦችን ስለማሻሻል ።

፩/ በአዋጁ ፣ በዚህ ደንብና በመተዳደሪያው ደንብ በተመለከተው መሠረት አንድ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል ይችላል ፤

፪/ ከያንዳንዱ ማሻሻያ ሁለት ግልባጭ ፤ ማሻሻያውን ለማጽደቅ ስብሰባ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአሥራ አምስት ቀኖች ውስጥ በአባሪ (ሐ) የኅ.ሥ.ማ. ቅጽ ፫ መሠረት ለሬጅስትራሩ መላክ አለበት ፤

፫/ አንድ ማሻሻያ የሚደረገው የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚያሳልፈው ልዩ ውሳኔ ብቻ ነው ።

## ፲/ ስለማኅበርተኝነት ፈቃድ ።

ማናቸውም ማኅበር አለበቂ ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ማኅበርተኛ ሊሆን የሚችለውን ማንኛውንም ሰው ማኅበርተኛ እንዳይሆን ሊከለክለው አይችልም ።

## ፲፩/ ለማኅበርተኝነት ብቁ ስለአለመሆን ።

፩/ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉድለቶች የፈጸመ ማናቸውም ሰው ማኅበርተኛ ሊሆን አይችልም ።

፪/ አንድ ማኅበርተኛ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉድለቶች ፈጽሞ ቢገኝ ጉድለቱን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ማኅበርተኛ መሆን ይቀራል ።

www.chilot.me



፲፪/ ጠቅላላው ጉባዔ ከመደረጉ በፊት ማኅበርተኞችን ስለመቀበል ።

ማናቸውም ማኅበር ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ በፊት በአሉት አሥራ አምስት (፲፭) ቀናት ውስጥ አዲስ ማኅበርተኞች መቀበል የለበትም ።

፲፫/ ዕዳውን ባልከፈለ ማኅበርተኛ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ ።

፩/ ማንኛውም ማኅበርተኛ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው ጊዜ ወይም እስከ ሦስት ወር ድረስ ፤ ከሁለቱ አንስተኛ በሆነው ጊዜ ውስጥ የማኅበሩን ዕዳ ሳይከፍል ቢዘገይ የማኅበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ወይም በሌላ ማኅበር ወኪል ለመሆን አይችልም ፤

፪/ ማንኛውም ማኅበርተኛ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ክፍት ቦታ ተሹሞ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ዕዳውን ከፍሎ የሚጨርስበት ጊዜ ቢያልፍ ከዚሁ ቀን አንስቶ አባልነቱ ይቀራል ።

፲፬/ ወራሽ ስለመሰየም ።

፩/ ማንኛውም ማኅበርተኛ በሞተ ጊዜ ድርሻው ወይም በማኅበሩ ካፒታል ውስጥ ያለው ጥቅም እንዲዛወር ወይም የዚሁ ዋጋ እንዲከፈል ወይም ማናቸውም ከማኅበሩ የሚደርሰው የገንዘብ ክፍያ እንዲደረግ ወራሽ ወይም ወራሾችን ሊሰይም ይችላል ። ይህም ማኅበርተኛ ሰያሚውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመሻር ወይም ለመሰወጥ ይችላል ፤

፪/ ማኅበርተኛው የሚሰይማቸው የወራሾች ቁጥር ማኅበርተኛው በማኅበሩ ውስጥ ካሉት ድርሻዎች ቁጥር መብለጥ የለበትም ፤

፫/ ይህም ስያሜ ዋጋ እንዲኖረው ማኅበርተኛው በጽሑፍ አስፍሮ ቢያንስ ሁለት ምስክሮች ባሉበት ፈርሞ ለዚሁ ጉዳይ በተያዘው በማኅበሩ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት ።

፲፭/ ጠቅላላ ጉባዔ ።

፩/ የማኅበርተኞቹ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ በንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) (መ) እና (ሠ) የተመለከተው ሥልጣን ይኖረዋል ፤

፪/ የቁጥጥሩ ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንደደረሰው በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመለከተው ጠቅላላ ጉባዔ ይደረጋል ፤

፫/ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ በፊት ቢያንስ የአሥራ አምስት (፲፭)ቀን ማስታወቂያ መስጠት አለበት ፤

፬/ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ «ምልአተ ጉባዔ» በመተዳደሪያ ደንቦች በተወሰነው መሠረት ሆኖ ጉባዔው በሬጅስትራሩ ጥሪ መሠረት የተደረገ እንደሆነ በዚሁ ጉባዔ ላይ በተገኙት ማኅበርተኞች ብቻ ምልአተ ጉባዔው እንደተሟላ ተቆጥሮ ሥራ ሊጀምር ይችላል ።

፲፮/ በጉባዔ ድምፅ ስለመስጠት ።

በጉባዔ ላይ ለተገኙት ማኅበርተኞች ለውሳኔ የሚቀርበው ማናቸውም ጉዳይ በአዋጁና በዚህ ደንብ ወይም በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያልተገለጸ ከሆነ በጉባዔው ላይ የተገኙት ማኅበርተኞች በድምፅ ብልጫ ውሳኔ ይሰጡበታል ። ድምፁ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል ።

www.chilot.me



፲፯/ ስለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎች ምርጫ ።

፩/ አንድ ማሕበር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎችን ለመምረጥ ማኅበርተኞችን በተለያዩ ቡድኖች በክፍለ ሀገር ወይም በሌላ ሁኔታ ሊደለድላቸው ይችላል ፤

፪/ የዚህ ዓይነቱ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ከያንዳንዱ ክፍል የሚመረጡትን ወኪሎች ብዛት ወይም ልክ ይወስናል ። በተጨማሪም ወኪሎች ፤

ሀ/ በሙሉ ማኅበርተኞች ወይም

ለ/ ወኪሎቹ ከተመረጡበት ክፍል ብቻ በሆኑ ማኅበርተኞች ሊመረጡ የሚችሉ መሆናቸውን ይወስናል ።

፲፰/ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ስለሚፈጠረው ክፍት የሥራ ቦታ ።

በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ክፍት የሥራ ቦታ ሲፈጠር እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ የሚያገለግል አባል ለመሾም ኮሚቴው ሥልጣን ይኖረዋል ።

፲፱/ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ብቁ ስላለመሆን ።

፩/ ማንኛውም ሰው ፤

ሀ/ በአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከማኅበሩ የወሰደውን ማናቸውንም ብድር ያልከፈለ ወይም

ለ/ በአባልነቱ ምክንያት ከሚኖረው ግንኙነት በስተቀር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከማኅበሩ ጋር በተደረገው ውል ወይም ማኅበሩ በሚሸጠው ወይም በሚገዛው ንብረት ወይም በማናቸውም በማኅበሩ ሥራ ጥቅም ያገኘ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆኖ አይሾምም ፤

፪/ አንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ጉድለቶች ቢፈጽም ይሻራል ።

፳/ ስለመጠባበቂያ ሂሳብ ።

አንድ ማኅበር በማናቸውም ዓመት ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ውስጥ ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ያላነሰ በመጠባበቂያ ሂሳቡ ውስጥ ገቢ ያደርጋል ።

ይህም ሂሳብ የሚጠራቀመው ማኅበርተኞቹ እንደየድርሻቸው የከፈሉትን የማኅበሩን ካፒታል ወይም ከዚህ የሚበልጥ በመተዳደሪያው ደንብ ውስጥ የተወሰነውን ገንዘብ ያህል እስኪሆን ድረስ ነው ።

፳፩/ ማኅበር ሲፈርስ የመጠባበቂያውን ሂሳብ ስለማከፋፈል ።

፩/ የሚፈርስ ማኅበር ሂሳብ በሚጣራበት ጊዜ የመጠባበቂያ ሂሳቡ በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንቦችን መሠረት ከተጠራቀሙት ሌሎች ሂሳቦች ጋር ሆኖ ከማኅበሩ ሐብትና ንብረት ላይ ተቀንሰው ሳይከፈሉ ለቀሩት ዕዳዎች መክፈያ እንዲሆን የሂሳብ አጣሪው ከዚህ በታች በተመለከተው ተራ መሠረት ይመድበዋል ።

ሀ/ የማኅበሩን ዕዳዎች ፤

ለ/ የማኅበሩን የተከፈለ ካፒታል ፤

ሐ/ ለወጣው ካፒታል በዓዋጁ በአንቀጽ ፴፩ ከተመለከተው ወለድ ለማይበልጥ ክፍያ ፤

www.chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ክፍያዎች ከተደረጉ በኋላ የሚተርፈው ገንዘብ የፈረሰው ማኀበር ማኀበርተኞች በጠቅላላ ጉባዔ በሚወስኑት መሠረት ለሕዝብ አገልግሎት ይውላል ፤ ወይም ለሌላ ማኀበር የመጠባበቂያ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ ይሰጣል ።

፳፪/ ስለኅብረት ሥራ የትምህርት መዋጮ ።

ማናቸውም ማኀበር ለኅብረት ሥራ ማስተማሪያ የሚውል መዋጮ ያደርጋል ። ይህም መዋጮ ሬጅስትራሩ በየጊዜው በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት ከማኀበሩ የተጣራ የዓመት ትርፍ ከመቶ አምስት (5%) ያልበለጠ ይሆናል ። በዚህም ሁኔታ የተጠራቀመው መዋጮ በብሔራዊ የኅብረት ሥራ ድርጅት ወይም የዚህ ዓይነት ድርጅት ከሌለ ሬጅስትራሩ በሚሾመው በኅብረት ሥራ ትምህርት ኮሚቴ አማካይነት በሥራ ላይ ይውላል ።

፳፫/ ያልተደለደለ ትርፍን ስለማከፋፈል ።

በአዋጁ ፤ በዚህ ደንብና በመተዳደሪያ ደንቦች በተወሰነው መሠረት ያልተደለደለ ማናቸውም ትርፍ ወደ የማኅበሩ የመጠባበቂያ ሂሳብ ገቢ ይሆናል ።

፳፬/ ገንዘብ በሥራ ላይ ስለማዋልና ስለማጠራቀም ።

፩/ የባንክ አገልግሎቶች በሚገኙበት ቦታዎች ሁሉ ማኀበሩ ማናቸውንም ገንዘቡንና የመጠባበቂያውንም ገንዘብ ጭምር ባንክ ማስቀመጥ አለበት ፤

፪/ ማኀበሩ ማናቸውንም ገንዘቡንና የመጠባበቂያውንም ገንዘብ ጭምር ከዚህ በታች ለተመለከቱት ሥራዎች ብቻ ማዋል ይችላል ።

ሀ/ በሌላ ማኀበር ድርሻዎች ወይም መያዣዎች (ሴኩሪቲስ) እና

ለ/ ስለዋናው ገንዘብና ስለወለድ ሙሉ ዋስትና ባላቸው የመንግሥት መያዣዎች (ሴኩሪቲስ) ።

፳፭/ ስለመበደር ።

፩/ ማናቸውም ማኀበር በጠቅላላ ጉባዔ ከማኀበርተኞች ወይም ማኀበርተኞች ካልሆኑ ሰዎች በመበደር ወይም በመቀበል ሊገባ የሚችለውን ከፍተኛ የዕዳ መጠን በየጊዜው ይወስናል ፤

፪/ ማናቸውም ማኅበር በዚህ አንቀጽ ፳፭ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከተወሰነው ዕዳ በላይ ኃላፊነት የሚያስከትል ብድር ወይም ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል አይችልም ።

፳፮/ ማኅበሩ ስለሚይዛቸው ሂሳብና ሌሎች መዛግብት ።

ሬጅስትራሩ በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ማናቸውም ማኅበር የማኅበሩን ሥራ የሚያመለክቱ ሂሳቦችና መዛግብት መያዝ አለበት ።

፳፯/ ሬጅስትራሩ የማኅበሮችን ሂሳብና መዛግብት ለማስተካከል ስላለው ሥልጣን ።

ሬጂስትራሩ በጽሑፍ በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት ማናቸውም ማኀበር ከዚህ በላይ በአቀጽ ፳፮ በተመለከተው መሠረት ሊይዝ የሚገባውን ሂሳብ ወይም መዛግብት ሬጅስትራሩ በሚሰጠው መምሪያና በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በከፊል ወይም በሙሉ እስተክክሎ መያዝ አለበት ። ማናቸውም ማኅበር ይህን ሳይፈጽም ቢቀር ሬጅስትራሩ ሂሳቡንና መዛግብቶቹን የሚያስተካክል አንድ የበታች ሹም ይወክላል ። ይህም ሲሆን ሬጅስትራሩ ሥራው የፈጀውን ጊዜ ገምቶ ለወከለው የበታች ሹም የሚከፈለውን አበል በመወሰን ይህንኑ አበል ማኀበሩ ለሚኒስቴሩ እንዲከፍል ያዛል ።

www.chilot.me



፳፰/ ማኅበሮች ስለሚአቀርቡአቸው የጽሑፍ መግለጫዎችና መረጃዎች ።

፩/ ማናቸውም ማኅበር ሬጅስትራሩ በሚወስነው መሠረት በእያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ዓመት ውስጥ ፤

ሀ/ የዓመቱን ገቢና ወጪ የሚያሳይ መረጃ ፤

ለ/ የትርፉንና የኪሳራውን ሂሳብ ፤

ሐ/ የሂሳብ ሚዛን ፤ (ባላንስ ሺት)

መ/ የሚቀጥለውን ዓመት በጀት እና

ሠ/ ሌሎችንም ሬጅስትራሩ የሚጠይቀውን የጽሑፍ መግለጫዎችና መረጃዎች ሁሉ ማዘጋጀት አለበት ።

፪/ ሀ/ ሬጅስትራሩ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ማናቸውም ማኅበር በዚህ አንቀጽ ፳፰ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን የጽሑፍ መረጃዎችን ግልባጭ በየዓመቱ ለሬጅስትራሩ ማቅረብ አለበት ፤

ለ/ የሂሳብ ተቆጣጣሪው የጽሑፍ መረጃዎችን ከመረመረ በኋላ ፤ በተቻለ መጠን የጽሑፍ መረጃዎች ከቀረቡበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ የሂሳብ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት ፤

ሐ/ ሬጅስትራሩ በሚያዘውና በሚወስነው መሠረት ማኅበሩ የሂሳብ ማረጋገጫውን የምስክር ወረቀትና የጽሑፍ መረጃዎችን ማሳተም አለበት ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ዓመታዊ የጽሑፍ መረጃዎች ሌላ ሬጅስትራሩ በሚሰጠው መምሪያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥና ለይቶ ለሚወስነውም ጊዜ ማናቸውም ማኅበር ተጨማሪ መረጃዎች ለሬጅስትራሩ ማቅረብ አለበት ።

፬/ ማናቸውም ማኅበር በዚህ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) የተዘረዘሩትን የጽሑፍ መረጃዎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያላቀረበ እንደሆነ ሬጅስትራሩ አስፈላጊውን የጽሑፍ መረጃዎች የሚያሰናዳ የበታቹን ሹም ይወክላል ። ይህም ሲሆን ሬጅስትራሩ ሥራው የፈጀውን ጊዜ ገምቶ ለተወከለው ሹም የሚከፈለውን አበል ለመወሰን ይህንኑ አበል ማኅበሩ ለሚኒስቴሩ እንዲከፍል ያዛል ።

፳፱/ በመዛግብት ውስጥ የሠፈሩትን ግልባጮች ስለማረጋገጥ ።

፩/ ማኅበሩ የተለመዱ ሥራውን ሲያካሄድ በመዛግብት ውስጥ ያሠፈራቸው ጽሑፎች ግልባጭ የሚረጋገጠው የማኅበሩ ማኅተም ተደርጐበት ፤

ሀ/ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ወይም ጸሐፊ ሲፈርምበት ፤ ወይም ፤

ለ/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፩ መሠረት የሂሳብ አጣሪ የተሾመ እንደሆን የሂሳብ አጣሪው ሲፈርምበት ነው ።

፪/ የተረጋገጡ የጽሑፍ ግልባጮች የሚሸጡበትን ዋጋ ሬጅስትራሩ በየጊዜው ይወስናል ።

፴/ ስለሠነድ ፍተሻ ።

ማንኛቸውም ማኅበርተኛ ወይም ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሠነዶች ከሬጅስትራሩ ጽ/ቤት ገብቶ በነፃ ሊፈትሽና ካስፈለገውም ከዚህ በታች የተመለከተውን ዋጋ በመክፈል የተረጋገጡ የጽሑፍ ግልባጮች ለማግኘት ይችላል ።

www.chilot.me



ብር ሣንቲም ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩/ | የመመዝገቢያ ማመልከቻ ... ... ... ... ... ... | 0.25 | እያንዳንዱ |
| ፪/ | የመመዝገቢያ የምስክር ወረቀት ... ... ... ... ... | 1.00 | » |
| ፫/ | የማኅበር የመተዳደሪያ ደንቦች ... ... ... ... ... | 0.50 | በገጽ |
| ፬/ | የማኅበር የመተዳደሪያ ደንቦች ማሻሻያ ... ... ... ... | 0.50 | » |
| ፭/ | ማኅበር የሚፈርስበት ትእዛዝ ... ... ... ... ... | 0.50 | » |
| ፮/ | የማኅበር የሂሳብ ቁጥጥር ማስታወሻ ... ... ... ... | 0.50 | » |
| ፯/ | ዓመታዊ የሂሳብ ሚዛን ... ... ... ... ... ... | 1.00 | » |
| ፰/ | በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ መሠረት በማኅበር ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ያደረሰውን ለማስከፈል የሚሰጥ ትእዛዝ ... ... ... | 1.00 | |

## ፵፩/ መንግሥት ለማኅበሮች ስለሚያደርገው ዕርዳታ ።

፩/ ሚኒስቴሩ ተገቢ መሆኑን ሲያምንበት ፤

ሀ/ አንድ ማኅበር ለሚሸጠው ዕጣና በዕጣውም ላይ ተጠራቅሞ ለሚከፈለው ክፍያ እስከ ሰባ አምስት በመቶ (75%) ድረስ ለመክፈል ዋስትና መስጠት፤

ለ/ ለማኅበርተኞች የቀለጠፈና በመጠነኛ ዋጋ አገልግሎት ለሚሰጥ ማኅበር ዕርዳታ ወይም ድጋፍ ወይም በቅድሚያ የሚሰጥ ገንዘብና ብድርን የመሳሰሉ የገንዘብ ዕርዳታ ማድረግ ፤

ሐ/ ማኅበሩ ተገቢ መስሎ ሲታየው በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስመልሰው የአክሲዮን ዕጣ መግዛት ፤

መ/ ለማኅበርተኞች የቀለጠፈና በመጠነኛ ዋጋ አገልግሎት ሊሰጥ ለሚችል ማኅበር በሚኒስቴሩ እጅ ከሚገኘው ወይም ከሌላ መንግሥት ከሚያዝበት መሬት እንዲያገኝ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) መሠረት የሚገኘውን መሬት የስም ዋጋ በማስከፈል ወይንም በነፃ ለማኅበሩ እንዲሰጠው ለማድረግ ይቻላል ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ለአንድ ማኅበር የተሰጠ መሬት በምንም ሁኔታ ከማኅበሩ ንብረት ውስጥ ሆኖ አይቆጠርም ። እንደዚሁም ዓይነቱን መሬት ብድር ለማግኘት ወይም ለሌላ ዕዳ ማስያዝ አይቻልም ። ማኅበሩ በሚፈርስበት ጊዜ በሽያጭ ዋጋ ለመንግሥት የተከፈለውን ገንዘብ ለማኅበሩ መልሶ መሬቱ ወደ መንግሥት መዛወር አለበት ።

## ፵፪/ የማኅበሩ አድራሻ ስለመለወጥ ።

፩/ ማናቸውም ማኅበር የተመዘገበ አድራሻውን መለወጡንና አዲሱንም አድራሻውን ለማጽደቅ የሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ አድራሻውን ለመለወጥ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለሬጅስትራሩ ማስታወቅ አለበት ።

፪/ ሬጅስትራሩ በዚህ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ማስታወቂያ ሲደርሰው ማኅበሩ ያስታወቀውን አዲሱን አድራሻ መዝግቦ ይህንኑ ለማኅበሩ ያስታውቃል ።

፫/ ማናቸውም የማኅበር አድራሻ ለውጥ በዚህ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ለሬጅስትራሩ ካልተገለጸ አድራሻው እንደተመዘገበ አይቆጠርም ።

## ፵፫/ ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ ።

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

www.chilot.me



የኅ.ሥ.ማ. ቅጽ ፤

## አባሪ «ለ»

የመመዝገቢያ ቁ. ....................................................................

ንጉሠ ነገሥት

የኢትዮጵያ



መንግሥት

### የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

### የኅብረት ሥራ ማኅበር የምስክር ወረቀት

ስለኅብረት ሥራ ማኅበር በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፩ አንቀጽ ፲ መሠረት ዛሬ................ቀን ፲፱...................ዓ. ም.

የ.......................................................................... ኅብረት ሥራ ማኅበር ኃላፊነቱ...............................ማኅበር ተመዝግቦአል ።

ሬጅስትራር ፤

የኅ.ሥ.ማ.ቅጽ ፫

## አባሪ «ሐ»

### ለሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

### የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ማስታወቂያ ።

እኛ.................................................................... ፕሬዚዳንትና ጸሐፊ

፩/ ተያይዞ የሚገኘው የደንብ ማሻሻያ ...................................... ቀን በተደረገው ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ መሆኑን ፤

፪/ በዚሁ ቀን የማኅበርተኞች ቁጥር..............ሲሆን ከነዚህ................ የተገኙ መሆናቸውን ፤

፫/ ......................ማኅበርተኞች የደንቡን መሻሻል በመደገፍ ድምፅ የሰጡ መሆናቸውንና

፬/ ስለጉባኤው መሰብሰቢያና ስለሚሻሻለው ደንብ...............፲፱............... በ................................................................................ ለአባሎች ማስታወቂያ የተላለፈ መሆን እናረጋግጣለን ።

ቀን............................... ፕሬዚዳንት ..............

ጸሐፊ ....................

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ምዕራፍ ፰ ።

## በአሠሪዎችና በሠራተኞች ስለሚሰጡ ማስታወቂያዎች ።

፲፫/ በአሠሪዎች ስለሚሰጥ ማስታወቂያ ።

ማናቸውም ሰው ፤

ሀ/ ቁጥራቸው ከአሥር የሚበዛ ሠራተኞች የሚገኙበት አዲስ የኢንዱስትሪ ወይም የን ግድ ሥራ ለማቋቋም ወይም ለጊዜው ያሉትን የኢንዱስትሪ ወይም የንግድ ሥራ ዎች ለማስፋፋት ያሰበ እንደሆነ ፤

ለ/ የኢንዱስትሪውን ወይም የንግዱን ሥራ የኢኮኖሚ ሁኔታ ወይም ስፍራውን ለመለ ወጥ ሥራውን ለጊዜው ለማቆም ወይም ጨርሶ ለመዝጋት ያሰበ እንደሆነ ፤

ሐ/ ሥራ ለማቋረጥ ፤ ሥራ ለማቆም ወይም በጠቅላላው ሥራን ለመዝጋት ያደረሰ ወይም የሚያደርስ የሠራተኛ ክርክር የተነሣ ወይም የሚነሣ መሆኑ የታወቀ እንደሆነ ፤

መ/ ከገጠር ማናቸውንም ሰው ወይም ሰዎች በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለመቅጠር ያሰበ እንደሆነ ፤

ሳይዘገይ መብቱ ለሚፈቅድለት የሠራተኛ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ማስታወቅ አለበት ።

፲፬/ በሠራተኞች ስለሚሰጥ ማስታወቂያ ።

ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ የሚያስብ ወይም በዚህ ትእዛዝ በ፲፫ኛው አንቀጽ በተዘ ረዘሩት ጭምር በማናቸውም ምክንያት ከሥራ ውጭ ለመሆኑ ማስታወቂያ የተሰጠው ወይም ከሥራው የተወገደ ማናቸውም ሠራተኛ መብቱ ለሚፈቅድለት የሠራተኛ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ለማስታወቅ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፱ ።

## የውጭ አገር ሰዎች በምን አኳኋን መሥራት እንደሚፈቀድላቸው ።

፲፭/ ስለሥራ ፈቃድ ።

ሀ/ ማናቸውም የውጭ አገር ሰው ከሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ደንበኛ የሥራ ፈቃድ ካልያዘ በቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በማናቸውም የግል እንዱስትሪ ፣ ንግድ ፣ እርሻ ወይም በሌሎች የሥራ ድርጅቶች ሊቀጠር አይችልም ።

ለ/ በዚህ ትእዛዝ በ፲፯ኛው አንቀጽ የተመለከተው ተጠብቆ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተስማምቶበት በዚህ ትእዛዝ በ፲፰ኛው አንቀጽ እንደተመለከተው የሕዝባዊ ኑሮ እድገት የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሥራ ፈቃድ ይሰጣል ። በተባለው ደንብ በተለይ ከዚህ የሚከተሉት ይኖሩበታል ።

፩/ በመንግሥት ስምምነት ወይም በማናቸውም የኢንተርናሽናል ውል ወይም ስምምነት መሠረት በማንኛቸውም የግል የሥራ ድርጅቶች ውስጥ ስለሚቀ ጠሩ ሰዎች ማንኛቸውም ሚኒስቴር ወይም የመንግሥታችን መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በቀጥታ ፈቃድ መስጠት ፤

www.chilot.me



፪/ **አጭር አርእስት ።**

ይህ ደንብ «ስለውጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የወጣ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፫/ **ስለ ደንቦች መሻር ።**

በዚህ ደንብ ስለተመለከቱት ጉዳዮች ከዚህ በፊት ሲሠሩባቸው የቆዩት ደንቦች ሁሉ በዚህ ተሽረዋል ።

፬/ **ደንቡ ስለሚጸናበት ወሰን ።**

ይህ ደንብ ትእዛዙ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ለሥራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት በሚመጡት የውጭ አገር ዜጎች ላይ የጸና ይሆናል ።

ሆኖም ፤

፩/ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መ/ቤቶች ፡ ማዘጋጃ ቤቶች ወይም እነዚህን በመሳሰሉ የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ ወይም ፤

፪/ የዲፕሎማቲክ ፡ የቆንስል ፡ ወይም የማናቸውም የኢንተርናሺናል ድርጅት አባል ወይም ሠራተኛ ሆኖ ለማገልገል ወደ ኢትዮጵያ በሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ።

፭/ **ትርጓሜ ።**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልሰጠው በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩/ «አሠሪ» ሲባል በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፪ሺ፭፻፲፪ በተመለከተው መሠረት የሥራ ውል በማድረግ ያገለግሎት ዋጋ ሊከፍል ግዴታ የገባ ማናቸውም ሰው ፤ ወይም ሰዎች ወይም ሕጋዊ አቅዋም ያለው ድርጅት ማለት ነው ።

፪/ «የውጭ አገር ዜጋ» ሲባል ፤ በሕጉ መሠረት የኢትዮጵያ ዜግነት የሌለው ሰው ማለት ነው ።

፫/ «የሠራተኛ ጉዳይ መ/ቤት» ሲባል ፤ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. በወጣው ትእዛዝ በ፳፫ኛው አንቀጽ (ለ) መሠረት አዲስ አበባ ላይ የተቋቋመውን የሠራተኛ ጉዳይ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትና ሌሎችንም በዚሁ ትእዛዝ መሠረት የተቋቋሙትን የሠራተኛ ጉዳይ ጽሕፈት ቤቶች ማለት ነው ።

የተጠቀሰው ሕግ

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) አን. ፪ሺ፭፻፲፪ ።

## ክፍል ፪ ፤ መሠረታዊ ውሳኔዎች ።

፮/ **የሥራ ፈቃድ በቀጥታ ስለ መስጠት ።**

ከማናቸውም የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሚኒስቴር ፡ ወይም መሥሪያ ቤት ፤

፩/ መንግሥት ባደረገው ስምምነት መሠረት በማናቸውም የግሉ ድርጅት ውስጥ ወይም ፤

www.chilot.me



## ክፍል ፫ ፤ ስለ ሥራው አፈጻጸም ።

### ፲፱/ ስለ ማመልከቻ አቀራረብ ።

ማናቸውም አሠሪ በድርጅቱ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ለመቅጠር በፈለገ ጊዜ ፤ ለሚቀጠረው ሰው የሥራ ፈቃድ ማመልከቻውን ለሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አበለት ።

### ፳/ ስለሚፈለጉ መረጃዎች ።

፩/ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት እንዲችል የውጭ አገር ዜጋ ለመቅጠር የሥራ ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ማናቸውም አሠሪ ፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና ሌላም አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ሁሉ ከማመልከቻው ጋር ለሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት ።

ሀ/ ለማስመጣት የተፈለገውን የውጭ አገር ዜጋና የጥገኞቹን ሙሉ ስም ፤ ዕድሜ ፤ ጾታና ዜግነት ፤

ለ/ ፈቃድ ስለተጠየቀበት ሥራ ፤ ለሠራተኛው በየወሩ ስለሚከፈለው ደመወዝ ፤ ሠራተኛው ድርጅቱን ለማገልገል ስለሚቆይበት ጊዜ ጭምር ዝርዝር መግለጫ ፤

ሐ/ እንዲቀጠር ስለተፈለገው የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ልምምድ ዝርዝር መግለጫ ፤

መ/ የድርጅቱ አድራሻ ፤ የተቋቋመበት ሥፍራ ፤ ሕጋዊ አቋቋምና የሥራው ዓይነት ፤

ሠ/ የተባለውን ሥራ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ሠራተኞች መካከል ሊይዙት የማይችሉበትን ምክንያት ፤

ረ/ በድርጅቱ በልዩ ልዩ ሥራ ተቀጥረው የሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች ቁጥርና በተለይም ጉዳዩ የሚመለከተው የውጭ አገር ዜጋ በተፈለገበት የሥራ ክፍል ተቀጥረው የሚሠሩትን የውጭ አገር ሰዎች ቁጥርና ማመዛዘኛ (ፕሮፖርሽን) ፤

ሰ/ ካፒታልን በሥራ ላይ ስለማዋል ጉዳይ የሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራውን ፕሮግራም ያጸደቀበት እንዳለ መረጃውን ፤

ሸ/ ለተባለው ሥራ ኢትዮጵያውያንን ለማሠልጠን የታቀደ ፕላን መኖርና አለመኖሩን ፤

ቀ/ በማመልከቻው ላይ የቀረቡት መረጃዎች በሙሉ እውነትና ትክክል መሆናቸውን አሠሪው በጽሑፍ ማረጋገጥ አለበት ።

#### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ቀ) የእንግሊዝኛ ትርጉም «አሠሪው እንደሚያውቀውና እንደሚያምነው» የሚል ተጨማሪ ሐረግ ይገኝበታል ።

### ፳፩/ በቅጾች ስለ መገልገልና ስለ ተጨማሪ መግለጫዎች ።

፩/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳ መሠረት መረጃዎችን ለማቅረብ አሠሪው የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሚያወጣቸው ቅጾች (ፎርሞች) ይጠቀማል ።

፪/ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት እንዲችል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ መረጃ አሠሪው እንዲያቀርብለት ለማድረግ ይችላል ።

www.chilot.me



፲፬/ ከሌሎች ባለሥልጣኖች ጋር ስለ መመካከር ።

የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ስለ ቀረበለት የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ በበለጠ ለመረዳት መመካከር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሚኒስትሮች ፣ መሥሪያ ቤቶችና እንዲሁም ከሌሎች ባለሥልጣን ድርጅቶች ጋር መመካከር አለበት ።

፲፭/ ውሳኔ ስለ ማስታወቅ ።

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ስለ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ውሳኔና ለውሳኔውም ድጋፍ የሆኑት ዝርዝር መረጃዎች በሙሉ በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው ።

፪/ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ውሳኔውን ለአሠሪው መግለጽና ውሳኔውም የሥራውን ፈቃድ የሚያስጥ ሲሆን ፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለአገር ግዛት ሚኒስቴር የይለፍ ክፍል ጽሕፈት ቤት ማስታወቅ አለበት ።

፫/ የሥራ ፈቃዱም የሚሰጠው በቀጥታ ለተጠየቀለት የውጭ አገር ዜጋ መሆን አለበት ።

፲፮/ የሥራ ፈቃድ ስለ ማደስ ።

፩/ ለአንድ የውጭ አገር ዜጋ የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ ለማሳደስ ሲፈለግ ፣ አሠሪው የሠራተኛው የሥራ ፈቃድ ጊዜ ከማለቁ አስቀድሞ ከሦስት ወር በፊት ማመልከቻውን ለሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት ።

፪/ እንዲሁም አሠሪው ፈቃድ የተሰጠበትን የአንድ የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ዓይነት ለመለወጥ በፈለገ ጊዜ ፣ የሥራ ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከቻውን ለሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት ።

ክፍል ፬ ፣ ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ።

፲፯/ ግዴታዎች መፈጸማቸውን ስለ ማረጋገጥ ።

፩/ አሠሪው የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ባቀረበ ጊዜ ፣ የሰጠው መግለጫ ትክክለኛ መሆኑን ፣ ወይም የገባውን ግዴታ በሥራ ላይ ማዋል አለማዋሉን ለማረጋገጥ ፣ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በማናቸውም ጊዜ ከአሠሪውም ለመጠየቅ ይችላል ።

፪/ አሠሪው የተጠየቀውን መረጃ ባያቀርብ ወይም የሰጠው መግለጫ ትክክለኛ ሳይሆን ቢቀር ፣ ወይም የገባውን ግዴታ በተግባር ላይ ያላዋለ ሆኖ ሲገኝ ፣ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሰጠውን የሥራ ፈቃድ ሊሠርዝ ይችላል ።

፫/ የሥራ ፈቃድ ሲሠረዝ ትእዛዙ ፣ በጽሑፍ ከመሆኑም በላይ ፣ እንዲሠረዝ ያበቁትን ምክንያቶች ከነማስረጃዎቹ የያዘ መሆን አለበት ።

፬/ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሠረዘውን የሥራ ፈቃድ ለአሠሪው ፣ ፈቃዱ ለተሠረዘበት የውጭ አገር ዜጋ ፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ላገር ግዛት ሚኒስቴር የይለፍ ክፍል ጽሕፈት ቤት ማስታወቅ አለበት ።

፲፰/ ስለ ይግባኝ ።

የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አሠሪው ሲቃወም ፣ ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሁለት ሳምንት ውስጥ ይግባኙን ለሚኒስትሩ ለማቅረብ ይችላል ።

www.chilot.me



## ምዕራፍ አንድ ፣ ጠቅላላ ።

## ክፍል አንድ ፣ ትርጉም ።

### አንቀጽ ሁለት ።

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጥ የሚያስፈልግ ሆኖ ካልተገኘ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

ሀ/ «ብይን» ማለት የሥራ ክርክርን በመወሰን የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ ማለት ነው ።

ለ/ «ቦርድ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የሠራተኛና የአሠሪ ጉዳይ ቦርድ ማለት ነው ።

ሐ/ «የኅብረት ስምምነት» ማለት በዚህ አዋጅ በተጻፈው መሠረት የኅብረት ክርክር ለማድረግ በተፈቀደላቸው ወገኖች መካከል የተወሰኑትን የሥራ ሁኔታዎች የሚያስከብር ማናቸውም ስምምነት ማለት ነው ።

መ/ «የኅብረት ክርክር» ማለት የኅብረት ስምምነት ከመፈጸሙ ወይም ከመሻሻሉ በፊት የሚደረግ የስምምነት ንግግር ማለት ነው ።

ሠ/ «ማስታረቅ» ሲባል የሥራው ክርክር የሚመለከታቸውን ወገኖች ለማቀራረብና ለማስማማት ቦርዱ ወይም ማናቸውም ሌላ ሦስተኛ ወገን የሚፈጽመው ተግባር ነው ።

ረ/ «ሠራተኛ» ማለት በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ በ፪ሺ፭፻፲፪ኛው ቁጥር እንደተመለከተው ፤ የሥራ ውል ግዴታ የገባ ማናቸውም ሰው ማለት ነው ። ይኸውም በሥራ ክርክር ወይም አንድ አሠሪ በሚያደርገው ተገቢ ያልሆነ የሥራ አፈጻጸም ምክንያት ከሥራ ውጭ ሆኖ ሌላ በቂና ተመሳሳይ ሥራ ያላገኘውን ማናቸውንም ሰው ይጨምራል ።

ሆኖም ፦

፩/ በአንድ አሠሪ ስም ፣ ሥራ አስኪያጅ ፣ ዲሬክተር ፣ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪል ሆኖ የተቀጠረ ማናቸውም ሰው ወይም በአሠሪው ስም ይህንን የመሳሰለ ሥራ የሚሠራውን ሰው ፤

፪/ የቤት አሽከርን ፤

፫/ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጥረው ከሚሠሩት ሰዎች በተቀር ከአሥር የማያንሱ ቀዋሚ ሠራተኞች በሚገኙበት እርሻ ውስጥ የሚሠራ የእርሻ ወይም የከብት እርባታ ሠራተኛን ፤

፬/ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥት ሠራተኞች የ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. ትእዛዝ በአንቀጽ ፫ እንደተወሰነው የመንግሥት ሠራተኛን አይጨምርም ። ስለሆነ ግን መንግሥት ወይም የመንግሥት የአስተዳደር ወይም የቴክኒክ መሥሪያ ቤቶችን በሚያስተዳድሩአቸው እንዱስትሪዎች ፣ ንግድ ቤቶች ወይም ለትርፍ በሚሠሩ ሌሎች የሥራ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሰዎች ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም እንደ መንግሥት ሠራተኞች አይቆጠሩም ።

ሰ/ «አሠሪ» ማለት በዚህ አዋጅ እንደተወሰነው ሠራተኛን ቀጥሮ የሚያሠራ ማናቸውም ሰው ማለት ነው ። ይኸውም መንግሥት ወይም የመንግሥቱ የአስተዳደር ወይም የቴክኒክ መሥሪያ ቤቶች የሚያስተዳድሩአቸውን ሌሎችን የሥራ ድርጅቶች ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአንድ አሠሪ ጥቅም ወይም ወኪል በመሆን የሚሠራውን ማናቸውንም ሰው ይጨምራል ።

www.chilot.me



ቀ/ «የአሠሪዎች ማኅበር» ማለት ይህ አዋጅ በሚመለከታቸው የሥራ ድርጅቶች ውስጥ የሠራተኛ ሁኔታዎችን ለመወሰንና እንዲሁም የአባሎቹን የኤኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ ኑሮና የሞራል ጥቅም ለማጥናት ፣ ለመጠበቅና ለማስፋፋት አሠሪዎች ተካፋይና አባል የሆኑበት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚገባ የተመዘገበ ድርጅት ማለት ነው ።

በ/ «የሠራተኛ ማኅበር» ማለት በሠራተኛ ላይ ስለሚደርስ የመብት መጓደል ወይም የሠራተኛ ሁኔታዎችን ስለማሻሻል ከአሠሪዎች ጋር የሚነጋገር ሠራተኞች ተካፋይና አባል የሆኑበትን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚገባ የተመዘገበ ድርጅት ማለት ነው ። ይኸውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ የተቋቋሙትንና በማኅበር አንድ የሆኑትን ብዙዎችን የሠራተኞችን ማኅበሮች ይጨምራል ።

ተ/ «ጠቅላላ የሠራተኛ ማኅበር» ማለት የማኅበሩ አባልነት ለአንድ የሥራ ድርጅት ሠራተኞች ብቻ ያልተወሰነ ማኅበር ማለት ነው ።

ኀ/ «የሠራተኛ ሁኔታዎች» ማለት ስለ ሠራተኛ አቀጣጠር ፤ ይኸውም ስለ ደመወዝ ፣ ስለ ካሣ ዓይነት ፣ ስለ እረፍትና ስለ ሕመም ፈቃድ ፣ ስለ እረፍት ጊዜ ፣ ስለ አደጋ መጠባበቂያ ዘዴዎች ፣ በሥራ ምክንያት በሚመጡ በሽታዎችና አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ስለሚከፈለው ካሣ ፣ ስለ ማኅበራዊ ደኅንነትና እነዚህን ስለመሳሰሉት የሠራተኛ ሁኔታዎች በአሠሪዎችና ሠራተኞች መካከል ያለው ጠቅላላ ግንኙነት ማለት ነው ።

ነ/ «የሥራ ክርክር» ማለት

፩/ ስለ ሠራተኞች ሁኔታ ስምምነት ወይም አያያዝ ወይም ፤

፪/ ስለ ሠራተኞች ሁኔታ ለመነጋገር ፤ ስምምነቱን ለመወሰን ፤ ለመጠበቅ ፤ ወይም የሠራተኞችን ሁኔታ በማሻሻል ረገድ የአሠሪዎች ወይም የሠራተኞች ወኪል ለመሆን መብት አለን ስለሚሉ ሰዎች ተገቢነት ወይም ሥልጣን የሚነሣ ማናቸውም ክርክር ማለት ነው ።

አ/ «ሥራ መዝጋት» ማለት አንዳንድ የሥራ ሁኔታዎችን እንዲቀበሉ ለማስገደድ በማለት አንድ አሠሪ ሠራተኞችን በሙሉ ወይም በከፊል ለጊዜው ሥራ መከልከል ማለት ነው ።

ከ/ «ሚኒስትር» እና «ሚኒስቴር» ማለት የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርና የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው ።

ወ/ «ድርጅት» ማለት የአሠሪዎች ማኅበሮችና የሠራተኞችም ማኅበሮች ማለት ነው ።

ዐ/ «መጠባበቂያ ገንዘብ» ማለት በችግር ጊዜ ለአባሎች መርጃ እንዲሆን በማሰብ ማናቸውም አሠሪ ወይም ማናቸውም ድርጅት የሚያጠራቅመው ገንዘብ ማለት ነው ።

ዘ/ «ሥራ ማቋረጥ» ማለት በአንድ የሥራ ክርክር ምኞታቸው እንዲፈጸም ለማድረግ ብዙ ሠራተኞች ተስማምተው ለጊዜው የሚያደርጉት ሥራ ማቋረጥ ማለት ነው ።

የ/ ከሥራ ማቋረጥ ጋር የተያያዘ ሲሆን ፤ «ተመሳሳይ ተግባር» ማለት ማናቸውንም የሥራ ውጤት ለመቀነስና የሥራ ድርጅቱንም ለማደናቀፍ ብዙዎች ሠራተኞች ተስማምተው የሚያደርጉት ማናቸውም ሥራ ማቋረጥ ማለት ነው ።

ደ/ «ተገቢ ያልሆነ የሥራ አፈጻጸም» ማለት ፤

፩/ ስለ ሠራተኛ ወይም ስለ ሠራተኛ ማኅበር ሲሆን ፤

፪/ በዚህ አዋጅ የተወሰኑትን ግዴታዎች ወይም ተግባሮች አልፈጽምም ማለት ወይም ከመፈጸሙ ችላ ማለት ፤

፫/ ሀ/ በሠራተኛ ማኅበር ሳይሆን በማናቸውም ሰው ወይም ሰዎች የተቋቋመና የተደራጀ ፤

www.chilot.me



## አንቀጽ አምስት ።

## ስለቦርዱ አባሎች ።

ሀ/ በቦርዱ ውስጥ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በኛ የሚሾሙ አምስት (፭) አባሎች ይገኙበታል ። ከእነዚህም አንዱ የቦርዱ ሊቀ መንበር ይሆናል ። በተጨማሪም ቁጥራቸው በቂ የሆነ ምክትል አባሎች ይሾማሉ ።

ለ/ የቦርዱ አባሎችና ምክትል አባሎች የሚሆኑት ሰዎች መልካም ስም ያላቸውና አድልዎ የሌላቸው ሆነው በሠራተኛ (ሌበር) ጉዳይ ረገድ ልምድ ላላቸው ሰዎች ምርጫ ይሰጣል ። የቦርዱ አባሎችና ምክትል አባሎቹ ሆነው የሚሾሙ ዕጩዎች እንዲያቀርቡ ለአሠሪዎች ማኅበሮችና ለሠራተኞች ማኅበሮች ጥያቄ ሊደረግላቸው ይቻላል ።

ሐ/ የቦርዱ አባሎችና ምክትል አባሎች በከፊል ጊዜ ያለ ደመወዝ ያገለግላሉ ። ሆኖም በቦርዱ ስብሰባ ለተገኙበት ጊዜ ሚኒስትሩ አበል ሊወስንላቸው ይችላል ።

መ/ የቦርዱ አባሎችና ምክትል አባሎች ለሦስት ዓመት ጊዜ ይሾማሉ ፤ ይሁን እንጂ በሚቀጥለው በያንዳንዱ ዓመት በጊዜው በአገልግሎት ላይ ካሉት ከሦስት አንድ እጅ የማይበዙት አባሎችና ምክትል አባሎች የአገልግሎታቸው ጊዜ በማናቸውም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲያልቅ የመጀመሪያው ሹመት ሲሰጥ የአንድ (፩) ፣ የሁለት (፪) እና የሦስት (፫) ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ተለይቶ መታወቅ አለበት ፤ አባሎችና ምክትል አባሎች እንደገና ለመሾም ይቻላል ።

ሠ/ ሚኒስትሩ ከአባሎቹ ማንኛውንም ለማሻርና ሳልተፈጸመው የአገልግሎት ዘመን በርሱ ምትክ ሌላ ለማሾም የሚችለው የተባለው አባል የተሰጠውን ሥራ ችላ ያለ ወይም በሥራ ላይ ሳለ ሕገ ወጥ የሆነ ሥራ ሲሠራ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በመጀመሪያ ፳፩/፲፰ (፲፱፻፶፬) ድ. ፵፬ ሆኖ ወጣ ፤ በ፳፫/፫ (፲፱፻፷፯) አ. ፪፻፲ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ስድስት ።

## ስለ ሠራተኞች ።

ሚኒስትሩ ለቦርዱ አንድ ጸሐፊ ይሾማል ። እንዲሁም ሥራውን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ሠራተኞች ለቦርዱ ይመድብለታል ። እነርሱም ደመወዝ የሚከፈላቸው ከሚኒስቴሩ ነው ።

# ክፍል ፪

## የአፈጻጸም ደንብ ።

## አንቀጽ ሰባት

## ስለ ስብሰባ ።

ሀ/ ሊቀ መንበሩ ወይም እርሱ በሌለ ጊዜ ተጠባባቂ ሊቀ መንበር ሆኖ እንዲሠራ እርሱ የመረጠው አንድ ሌላ የቦርዱ አባል የቦርዱ ሰብሳቢ ይሆናል ። ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ሌላ አባል ያልተመረጠ እንደሆነ ፤ በቦርዱ ውስጥ የበለጠ የአገልግሎት ቅድሚያ ያለው አባል እንደ ተጠባባቂ ሊቀ መንበር ሆኖ ይሠራል ።

ለ/ በማናቸውም የቦርዱ ስብሰባ አንድ አባል ያልተገኘ እንደሆነ ሊቀ መንበር ሆኖ ስብሰባውን የሚመራው ሰው በስብሰባው ባልተገኘው አባል አንድ ምክትል አባል ለመተካት